## መመሪያ ቁጥር 77/2018
## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት ሀብትን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል መሠረታዊ ጉዳይ በመሆኑ፣ የዕቃዎች እና የአገልግሎቶች ግዥ እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ከመንግስት ጠቅላላ ሀብት ከፍተኛውን የወጭ ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ የክልሉ የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር በአዋጅ እንዲመራ ሲደረግ የዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሆነውን የግዥ መመሪያ ከአዋጁ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግስት ግዥ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም ከማድረግ በተጨማሪ የግዥ አፈፃፀም ላይ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን የመልካም አስተዳደር መገለጫ በመሆኑ፣ እንዲሁም በመንግሥት ግዥ መመሪያ ውስጥ የግዥ ሥራ መጓተትን የሚያስከትሉትንና ግልጽ ባለመሆናቸው ምክንያት የግዥ አፈፃፀምን የሚያዛቡትን እንዲሻሻሉ ለማድረግ፣

የመንግስት ግዥ በክልል፣ ዞኖች፣ በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች ለሚከናወኑ ለኢኮኖሚ ልማት ተግባሮች ማስፈጸሚያ አጋዥ መሆን ስለአለበትና በተበታተነ መልኩ የሚገኙ ልዩ ልዩ የግዥ መመሪያዎችን በአንድነት ቃኝቶና ሥራን እንደገና ከማደራጀት የጥናት ሠነድ ጋር አጣጥሞ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 አንቀጽ 62 ንኡስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የግዥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 77/2018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "ዕቃ" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ የሚገኝ ጥሬ ዕቃ፣ ምርት፣ መሣሪያ፣ ሸቀጥ፣ ለገበያ የተዘጋጁ ሶፍት ዌር፣ እንስሳ እንዲሁም ከሚገዛው ዕቃ ጋር ግንኙነት ያለው እና ከዕቃዎቹ ዋጋ ያልበለጠ ዋጋ ያለው የተከላ፣ የትራንስፖርት፣ የጥገናና ሌላ ተመሳሳይነት ያላቸውን አገልግሎቶች ይጨምራል፡፡

2. "አገልግሎት " ማለት ከዕቃ፣ ከግንባታ ሥራ እና ከምክር አገልግሎት ውጪ ያለ ሲሆን የጥገና፣ የጥበቃ፣ የፅዳት አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣የውኃ አቅርቦት እና የመሳሰሉትን ማናቸውም አገልግሎቶች ግዥ ይጨምራል፡፡
3. "የግንባታ ዘርፍ" ማለት ከሕንፃ፣ ከመንገድ ወይም ከሌሎች የመሠረተ ልማት ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚከናወን አዲስ የግንባታ፣ የመልሶ ግንባታ፣ የማፍረስ ፣ የጥገና፣ የማደስ ሥራ እንዲሁም ተጓዳኝ የሆነና ከዋናው ሥራ ያልበለጠ ዋጋ ያለው አገልግሎት ሲሆን፣ የመገንባት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ ሥራውን የማንቀሳቀስ እና የማስተላለፍ ውሎችን ይጨምራል፡፡
4. "የምክር አገልግሎት" ማለት አማካሪዎች ያላቸውን ሙያዊ ክህሎት በመጠቀም የሚሰጡት የጥናት፣ የዲዛይን፣ የግንባታ ቁጥጥር የተለያዩ ፕሮጀክቶችን የማደራጀት፣ ለደንበኞች ምክር የመስጠት፣ ሥልጠና የመስጠት እና ዕውቀትን የማስተላለፍ የአማካሪነት ባህሪ ያለው ሆኖ የአእምሮ አገልግሎት ነው፡፡
5. "ግዥ" ማለት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክር አገልግሎት እና ሌሎች አገልግሎቶችን በግዥ፣ በኪራይ ወይም በማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ውል መሠረት ማግኘት ነው፡፡
6. "ግዥ ፈጻሚ አካል " ማለት ግዥ የሚፈጽምና ንብረትን የሚያስተዳድር የመንግስት መ/ቤት ወይንም ከተማ አስተዳደርና ማዘጋጃ ቤት ነው።
7. "የመንግስት መ/ቤት " ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤት ነው፡፡
8. "ሎት (ምድብ)" ማለት የተለያዩ አቅርቦቶች ሆነው ተዛማጅነት ወይንም ተቀራራቢ ባህርይና ጠቀሜታ ያላቸውና በአብዛኛው አንድ አይነት የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ በተሰጣቸው አቅራቢዎች በአንድ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ የአቅርቦቶች ስብስብ ወይም ምድብ ነው።
9. "የመንግሥት ገንዘብ" ማለት ከክልሉ መንግስት ግምጃ ቤት ወይም የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ካገኘው ድጎማ ወይም የውጭ እርዳታና ብድር ለግዢ ፈጻሚ አካላት የተመደበ ገንዘብ ወይም የግዢ ፈጻሚ አካላት የውስጥ ገቢ ነው፡፡
10. "የመንግሥት ግዥ" ማለት በመንግስት መ/ቤቶች በመንግሥት ገንዘብ የሚከናወን ግዥ ነው፡፡
11. "አቅራቢ" ማለት ለመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር አገልግሎት ለመስጠት ውል የገባ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡
12. "ዕጩ ተወዳዳሪ" ማለት በመንግሥት ግዥ እንዲሳተፍ የተጋበዘ ወይም ለመካፈል ያመለከተ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡
13. "ተጫራች" ማለት የመጫረቻ ሃሣብ ያቀረበ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡
14. "ጨረታ" ማለት የጨረታ ማስታወቂያው ይፋ ከሆነበት ወይም የጨረታ ግብዣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ውል እስኪፈረም ድረስ ያለውን የግዥ አፈጻጸም ሂደትን የሚገልጽ ነው።

15. "የጨረታ ሠነድ" ማለት ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በግዥ ፈጻሚ አካላት ተዘጋጅቶ የሚሰጥ ሠነድ ነው፡፡

16. "የመጫረቻ ሰነድ" ማለት በግዥ ፈጻሚ አካላት ለግዥው ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መነሻነት ተጫራቹ በግዥው ለመሳተፍ የሚያቀርበው ሰነድ ነው፡፡

17. "ጠቅላላ ዋጋ" ማለት ለአንድ ግዥ አፈጻጸም ታክስን ጨምሮ ማናቸውም ሌሎች ወጪዎችን በማካተት በግዥ ፈጻሚው አካል ለሚፈጸም ግዥ የሚከፈል ዋጋ ነው።

18. "የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ" ማለት ዕቃው፣አገልግሎቱ፣ የግንባታ ሥራው ወይም የምክር አገልግሎቱ ሊያሟላ የሚገባውን ጥራት፣ ዓይነትና ደረጃ የሚገልጽ ሰነድ ነው።

19. "መደበኛ የጨረታ ሠነድ " ማለት የመንግስት መሥሪያ ቤቶች አጠቃላይ ይዘቱ አንድ ወጥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ የጨረታ ሠነድ በቀላሉ ማዘጋጀት እንዲችሉ እንደግዥው ዓይነት በቢሮው የተዘጋጀ ሠነድ ነው።

20. "የቅድሚያ ክፍያ " ማለት የዋጋ ልውውጥ ያልተደረገበት በግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ለአቅራቢው በቅድሚያ የተከፈለ እና ተቀባዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚተካው ክፍያ ነው ።

21. "የጨረታ ማስከበሪያ" ማለት ተጫራቹ ጨረታውን ቢያሸንፍ ውሉን የሚፈርም ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን ጨረታውን ላወጣው የመንግሥት መ/ቤት የሚሰጠው የጨረታ ዋስትና ነው፡፡

22. "የውል ማስከበሪያ" ማለት አቅራቢው በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለማካካስ እንዲቻል በአቅራቢው ስም ለውል ሰጪ ግዥ ፈጻሚ አካል የሚሰጥ ዋስትና ነው ።

23. "የአካባቢ ማስታወቂያ" ማለት በጋዜጣ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ለመጠቀም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ በግዥ ፈጻሚ አካላት በቋሚ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ ላይ የሚለጠፍ የጨረታ ማስታወቂያ ነው።

24. "የግዥ መመሪያ" ማለት በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጁ በተደነገገው መሠረት በቢሮው የሚወጣ መመሪያ ነው፡፡

25. "በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ዋስትና " ማለት ከኢንሹራንስ ድርጅት የሚሰጥ የዋስትና ዓይነት ሲሆን ዋስትናው በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ዋስትና ሰጭው አካል የዋስትና ግዴታውን የሚወጣው ወይም የሚያከብረው ደንበኛው/አቅራቢው/ የውል ግዴታውን ያልተወጣበትን ምክንያት ግዥ ፈጻሚው አካል ከውሉ አኳያ አሳማኝ ምክንያቶችን አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ የሚከፈል ዋስት ነው።

26. "በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ዋስትና" ማለት ከባንክ የሚሰጥ የዋስትና ዓይነት ሲሆን ተፈጻሚነቱም ውል የያዘው ወይም የፈረመው አቅራቢ እንደውሉ ግዴታውን አልተወጣም ብሎ ግዥ ፈጻሚው አካል ሲያምን ዋስትናውን ለሰጠው ባንክ የተሰጠውን ገንዘብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲከፈለው ሲጠይቅ የሚከፈል ዋስትና ነው።

27. "ልዩ ግዥ" ማለት ክልላዊ ጠቀሜታ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በቢሮው ኃላፊ ውሳኔ በጥቅል የሚፈጸሙ ከፍተኛ ግዥዎች ወይም የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ያላቸውን ተመሳሳይ የግዥ

ፍላጎት እንዲሁም አንድ የመንግስት መ/ቤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚኖረውን የግዥ ፍላጎት ለማሟላት የሚፈጸም ግዥ ነው።

28. "የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢ" ማለት በማዕቀፍ ስምምነት ዕቃ ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለማቅረብ ውል የገባ አቅራቢ ነው ።

29. "የማዕቀፍ ስምምነት" ማለት ወደፊት በሚፈጸም ዝርዝር ውል ለሚከናወን አቅርቦት መሠረት በመሆን የሚያገለግል፣ በነጠላ ዋጋ እና በሌሎች የውል ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተፈረመ አጠቃላይ የሆነ የግዥ ስምምነት ነው።

30. "ቢሮ፣ ዞን፣ ወረዳ እና የቢሮ፣ የዞን፣ የወረዳ ኃላፊ" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ የዞንና የወረዳ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ፣ ጽ/ቤት እና የእነዚሁ ኃላፊ ነው፡፡

31. "ከተማ አስተዳደር " ማለት በህግ በታወቀ ወሰን ተደራጅቶ የአንድን ከተማ ነዋሪ ህዝብ የፖለቲካ ፣ የአስተዳደር፣ የልማት አገልግሎት አሰጣጥ ስልጣንና ኃላፊነት በመረከብ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው።

32. "ማዘጋጃ ቤት" ማለት የተሟላ የከተማ አስተዳደር ባልመሰረቱ ከተማዎች ውስጥ ሥልጣንና ኃላፊነት በመረከብ የሚመራ የአካባቢ አስተዳደር ነው።

33. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

34. "የሥራ ሂደት "ማለት የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም ግዥ እንዲፈጽሙ በልዩ ሁኔታ የተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደቶች ማለት ነው።

35. " አዋጅ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 179/2003 ነው ።

36. "ክልል" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ነው።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙና ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በክልሉ መንግሥት በጀት በሚተዳደሩ መ/ቤቶች ግዥ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም:-

   ሀ/ ቢሮው አግባብ ካላቸው የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በክልላዊ ደህንነት ጉዳዮች ምክንያት ግዥ በተለየ ዘዴ እንዲፈፀም ዉሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቢሮዉ ግዥዎች በቁጠባና ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችል የግዥ ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

   ለ/ ግዥ ፈፃሚ አካላት ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ወጭ በመሸፈን ከሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ ይህ መመሪያ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የከተማ አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች ግዥ ላይም ተፈፃሚ ይሆናል።

## 4. የመንግሥት ግዥ መርሆዎች

ማንኛውም ግዥን ለማስፈፀም የተሰጠ ሥልጣን እንዲሁም የግዥ አፈፃፀም የሚከተሉትን መርሆዎች ከግብ ማድረስ ይኖርበታል ፣

1. በግዥ አፈፃፀም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት፣ ይህም ማለት ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣
2. በአዋጁ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በዜግነት ወይም ከመወዳደሪያ መስፈርቶች ጋር ባልተያያዙ ሌሎች ምክንያቶች በመንግስት ግዥ እንዳይሳተፍ አለመከልከልን ወይም አድልዎ አለማድረግን፣
3. ግዥ ፈጻሚ አካላትን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት መደገፍ፣
4. ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠውን ውሣኔ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ ማድረግ፣
5. ከግዥ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ውሣኔዎች እና የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚያስከትሉት ተጠያቂነት መኖሩን ማረጋገጥ፣
6. በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ልዩ አስተያየት መሰረት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚደግፉ የሀገር ውስጥ አምራቾችን፣ ኩባንያዎችን፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን፣ ታክስና ወጪ አስተዳደርን ማበረታታት።

## 5. በውጭ ዕርዳታና ብድር የሚከናወኑ ግዥዎች አፈፃፀም ሥርዓት

በመንግሥት መ/ቤቶች የሚከናወን ማንኛውም ግዥ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን መርሆዎች እና የአፈፃፀም ሥርዓቶች መከተል ይኖርበታል። ሆኖም ዕርዳታ ሰጪዎች እና አበዳሪዎች ከመንግሥት ወይም ሥልጣን ከተሰጣቸው የመንግሥት አካላት ባደረጉት የውል ስምምነት መሠረት ከአፈፃፀም ሥርዓቶች አንዳንዶችን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ከተመረጠው አገር እንዲሆን መፍቀድን ጨምሮ የመለወጥ መብታቸውን መጠቀም ይችላሉ።

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ በውጭ ብድርና እርዳታ የሚከናወኑ ግዥዎችን የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ የግዥ ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት የክልሉን ግዥና ንብረት አስተዳደር ከሚከታተለው ገንዘብና ኢ/ል/ቢሮ ጋር የግዥ አፈጻጸሙ ስለሚከናወንበት ሁኔታ በጋራ

መምከርና ክክልሉ የግዥ መመሪያ በተለየ መፈጸም የሚያስችል ልዩ መመሪያ ከአለም ስለዚሁ መመሪያ የጋራ ስምምነት ተይዞ ወደ አፈጻጸም መግባት አለበት።

# ክፍል ሁለት

# የግዥ ዕቅድ

## 6. የግዥ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

1. ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤትና በሥሩ የተደራጁ አካላት የልማት ዕቅድ ማስፈጸሚያ የሚሆን በጀት ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ከዚሁ ጎን ለጎን የግዥ ዕቅድ መዘጋጀት አለባቸው ፤
2. መሥሪያ ቤቶች ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ፕሮግራሞቻቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን የግዥ ፍላጎት በጀት ጸድቆ በደረሳቸው እስከ 30 ባሉት ተከታታይ ቀናት ቀድመው ያዘጋጁትን በመከለስ ግዥን ለመፈፀም ኃላፊነት ለተሰጠው አካል መላክ አለባቸው፤
3. ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚፈጽሙት ማናቸውም ግዥ ዕቅድን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የሚዘጋጀው ዕቅድም የሚከተሉትን ዓላማዎች ከግብ ማድረስ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡
   - 3.1. በአዋጁ አንቀፅ 5 ላይ የተመለከቱትን የመንግስት ግዥ መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግ፤
   - 3.2. ግዥ ፈጻሚ አካላትን የሥራ ፕሮግራም ለማሳካት፣
   - 3.3. የመንግስት መ/ቤቶች የቁጥቁጥ ግዥን በመከላከል አሰራሩ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን፣
   - 3.4. በግዥ አፈጻጸም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በቅድሚያ በመገንዘብ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ለማስቻል፡፡
4. ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የግዥ ዕቅድ አዘጋጅቶና አጸድቆ የግዥ ጥያቄውን የግዥ ተግባር ለሚፈፅመው የሥራ ሂደት በወቅቱ ባያቀርብ ለሚከሰተው የግዥ መጓተት ኃላፊነቱን እራሱ ይወስዳል።

## 7. የግዥ ፍላጎትን መለየት፣ ማሰባሰብና ማደራጀት

1. ማናቸውም ግዥ ፈጻሚ አካል የግዥ ፍላጎት በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች መከተል አለበት።
   - 1.1. ፍላጎቱ በግዥ ፈጻሚው ውስጥ ባለ እና ጥቅም ላይ ባልዋለ ሌላ ሐብት ወይንም ንብረት ሊሟላ የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፣
   - 1.2. ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ ምርት ወይንም አገልግሎት ሊሟላ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣
   - 1.3. የግዥ ፍላጎቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ እሴቶችን ያላካተተና መሥሪያ ቤቱን ለአላስፈላጊ ወጪ የማይዳርግ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.4. በተለይ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ታስበው የሚከናወኑ ግዥዎች በሚሆኑበት ጊዜ የግዥ ፍላጎቱ ወደፊት የሚፈጠርን የፍላጎት ዕድገት ያገናዘበ መሆኑን፣

1.5. አስገዳጅ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ፍላጎቱ ገበያ ላይ በሚገኝ መደበኛ አቅርቦት ወይም ስታንዳርድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.6. ማንኛውም የግዥ ፍላጎት የሚያቀርብ የሥራ ሂደት ወይንም ሴክተር መ/ቤት የሚገዛለትን ዕቃ የንግድ ምልክት ጠቅሶ ማቅረብ የሌለበት መሆኑን፣

1.7. የግዥ ፍላጎቱ የማህበረሰቡን የአካባቢ ደህንነት እና ጥበቃ የማይጎዳ መሆኑን ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ ማረጋገጥ፣

1.8. አዲስ የግዥ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ንብረቱ እንዲገዛላቸው የሚጠይቁ አካላትና የግዥ ባለሙያዎች ግዥው ከመታቀዱ ወይም ከመገዛቱ በፊት የተጠየቀው እቃ በመጋዘን ውስጥ የሌለ መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት በመስሪያ ቤቱ ከሚገኙ የሥራ ሂደቶች እና በጥል ከሚያስተዳድሯቸው ሴክተሮች የግዥ ፍላጎቶችን በማሰባሰብ ዓመታዊ የግዥ ፍላጎታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን መፈጸም አለባቸው፣

2.1. በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ተጠቃሚዎች የግዥ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያቀርቡ መጠየቅ፣

2.2. ከተጠቃሚዎች የቀረበውን ፍላጎት በዓይነት፣ብዛት፣ የጥራት ደረጃ እና የሚገኝበትን ቦታ መለየት፣

2.3. መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሠጣቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራና አገልግሎቶችን መለየት፣

2.4. የቀረበው ፍላጎት በቂ አቅራቢ ያለው ወይም የሌለው መሆኑን ማጣራት፣

2.5. በመስሪያ ቤቱ በተደረገ ጥናት ወይም ከሌሎች ምንጮች በተገኘ የገበያ መረጃ ለግዥው የሚያስፈልገውን የዋጋ ግምት ማወቅ፣

2.6. ለተሰበሰበው የግዥ ፍላጎት በቂ በጀት መኖሩን ማረጋገጥ፣

2.7. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጠቃሚዎቹ መዘጋጀቱን ወይም ወደፊት የሚዘጋጅ መሆኑን ማጣራት፣

3. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከተጠቃሚዎች የተሰባሰበውን ፍላጎት እና ከገበያ ጥናት የሚገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እና የሚከተሉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ግዥውን ማደራጀት አለባቸው።

3.1. በአዋጁ አንቀጽ 42 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ግዥ በአንድ ላይ የሚፈጸምበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከ50% በላይ ድርሻ ያለውን የግዥ አይነት መሠረት በማድረግ መፈጸም፣

3.2. አንድ አይነት እና ተመሳሳይ ፍላጎቶች በአንድ ላይ ማሰባሰብ፣

3.3. በአንድ ላይ ለሚፈፀሙ ግዥዎች በቂ አቅራቢ በገበያ ላይ መኖሩን ወይም ግዥው በሚኖረው የአቅራቢ አይነት በተለያየ ምድብ (ሎት) በመከፋፈል በቂ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ማረጋገጥ፣

3.4. ግዥው ለአፈጻጸም አመቺ እና አደናቃፊ ሁኔታዎች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ፣

3.5. ለአገር ውስጥ አምራቾች የመወዳደር እድል በሚሰጥ መልኩ ግዥ እንዲደራጅ ማድረግ፣

## 8. የግዥ ዘዴን መምረጥ

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት በግዥ ዕቅድ ዝግጅት ወቅት በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ለእያንዳንዱ የግዥ አይነት ከተፈቀዱት የግዥ ዘዴዎች ውስጥ አግባብነት ያለውን መምረጥ እና በዕቅዱ ላይ ማመልከት አለባቸው፡፡

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ ዕቅዱን በሚያዘጋጁበት ወቅት የሚታወቁ የግዥ ፍላጎቶች በግዥ ዕቅዱ ውስጥ መካተታቸውን እና ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ መመረጡን ማረጋገጥ አለባቸው፣

## 9. የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን መወሰን

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ እቅድ ማዘጋጃ ቅፅ በመጠቀም ለየግዥው ዋና ዋና ተግባራት የሚከናወንበትን ጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እና ሌሎች እንደ ግዥው ሁኔታ ተገቢ የሆኑ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

   1.1. ግዥው በሚከናወንበት ጊዜ ከግዥ ፈጻሚው የሥራ ፕሮግራም ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣

   1.2. በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦት የሚኖርበትን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆኑን፣

   1.3. በግዥ መመሪያው አንቀፅ 14.9 ላይ በተገለፀው መሰረት ዝቅተኛ የጨረታ መቆያ ጊዜን የጠበቀ እና ሰፊ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ተጨማሪ ጊዜ የሰጠ መሆኑን፣

   1.4. በተለይ ውስብስብ ለሆኑ እና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ላላቸው ግዥዎች በቂ የሰነድ ማዘጋጃ፣ መገምገሚያ እና ማፅደቂያ ጊዜ የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለየግዥ ዓይነቱ የሚወሰነው ጊዜ የግዥ አፈጻጸም ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ከሚያስፈልገው ጊዜ የረዘመ እንዳይሆን ተገቢ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

## 10. የግዥ ዕቅድ ይዘት

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 7 እስከ 10 የተከናወኑ ተግባራትን መሰረት በማድረግ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 1 ላይ ባለው ቅፅ በመጠቀም የግዥ ዕቅዳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ በዚህ መሰረት የሚዘጋጀው ዕቅድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

   1.1 . የግዥውን ምድብ እና ቁጥር፣

   1.2 . የግዥውን መግለጫ፣

1.3. የግዥውን መጠን፣

1.4. የግዥው ዝርዝር አፈጻጸም የሚከተላቸው አሠራሮች፣

1.5. ግዥውን ለማጠናቀቅ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚፈፀሙበትን ጊዜ፣

1.6. ለግዥው የሚያስፈልገውን በጀት መጠንና የፋይናንስ ምንጭ፣

1.7. ለግዥው ተስማሚ የሆነ ውል ዓይነት፣

1.8. በግዥ አፈጻጸም ሂደቱ የሚሳተፉ ዋና ዋና አካላትን የተሳትፎ ሁኔታ፣

1.9. ሌሎች እንደ መ/ቤቱ ባህርይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን፣

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት ለግዥ ዕቅድ ዝግጅት በግብአትነት የተጠቀሙባቸውን ዋና ዋና መረጃዎች ምንጭ እና ሌሎች የግዥ ዕቅዱን ለተጠቃሚ የበለጠ ግልፅ ያደርጋሉ ብለው የሚያስቧቸውን መረጃዎች ከግዥ እቅድ ቅፁ ጋር በአባሪነት ማያያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

## 11. የግዥ ዕቅድ የሚፀድቅበትና የሚሻሻልበት ሁኔታ

1. የግዥ አፊሰሮች ከየሥራ ሂደቱ ወይም ከየመሥሪያ ቤቱ ፍላጎትን በመሠብሰብ ያዘጋጁትን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ለመ/ቤቱ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ቀርቦ ከታየ በኋላ በማኔጅመንት ቀርቦ መፅደቅ አለበት።

2. የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ የመ/ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሠረት መመራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት አፈጻጸሙን መከታተል አለበት፣

3. በመ/ቤቱ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት /አስተባባሪ/ የፀደቀውን ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ቅጅ ለአፈጻጸም እንዲያመች በመ/ቤቱ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶችና ለፑል ተጠቃሚ መ/ቤቶች መላክ አለበት፣

4. በግዥ ፈጻሚ አካላት የተዘጋጀው ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ተቀባይነት አግኝቶ በማኔጅመንቱ ከጸደቀ በኋላ የሥራ ሂደቶች የግዥ አፈጻጸሙን መከፋፈል ወይም በዕቅዱ ከተገለጸው አሠራር ውጭ መፈጸም አይችሉም::

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈጻሚ አካላት አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደ ተጨማሪ በጀት፣ የበጀት እጥረት እና የመሳሰሉ ችግሮች በሚገጥማቸው ጊዜ የግዥ ዕቅዳቸውን ሊያሻሽሉ ወይም ሊከልሱ ይችላሉ::

6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 በተገለጸው መሠረት የተሻሻለውን የግዥ ዕቅድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ለአፈጻጸም አመችነት ሲባል በመ/ቤቱ ለሚገኙ የሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶች መላክ አለባቸው፣

7. ከላይ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6 የተገለጹትን በአግባቡ መፈጸም እንዲቻል የግዥ ፍላጎት የሚያቀርቡ የሥራ ሂደቶች ወይንም መሥሪያ ቤቶች የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር

የሥራ ሂደት በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በወቅቱ የግዥ ፍላጎታቸውን የማቅረብ ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

# ክፍል ሦስት

# የግዥ ዘዴዎችና አፈፃፀማቸው

## 12. የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች

1. በአዋጁ አንቀፅ 20 መሠረት የሚከተሉት 6 የግዥ ዘዴዎች ተፈቅደዋል። እነርሱም፣
   1.1. ግልፅ ጨረታ፣
   1.2. ውስን ጨረታ፣
   1.3. በዋጋ ማቅረቢያ (በፕሮፎርማ) የሚፈፀም ግዥ፣
   1.4. በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ፣
   1.5. በመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ እና
   1.6. የሁለት ደረጃ ጨረታ ናቸው።
2. በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈጻሚ አካላት ማናቸውንም ግዥ በግልፅ ጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው።
3. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከግልጽ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው::
4. በአዋጁ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም ግዥ ፈጻሚ አካል የጨረታ ሰነድ ከመዘጋጀቱ በፊት በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚያስረዳ መግለጫ ቃለ ጉባኤ ተይዞ በመፈራረም መረጃው ለሚፈልገው አካል ዝግጁ መሆን አለበት ::
5. ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ አፈጻጸማቸውን መረጃ የሚገልጽ መዝገብ በማዘጋጀት በአግባቡ መመዝገብ አለባቸው፤ ምዝገባውም ቢያንስ የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል።
   1.1 በሥራ ላይ የዋለውን የግዥ ዘዴ የተመረጠበትን አግባብ ባጭሩ፣
   1.2 የተገዛውን ዕቃ፣አገልግሎት እና የግንባታ ሥራ ዓይነት፣ብዛትና የገንዘብ መጠን፣
   1.3 የተገዛበት ቀን፣ ወርና ዓ/ም፣
   1.4 የቀረበ ቅሬታ ካለ የቅሬታው ምንጭ እና የተሰጠ ምላሽ፣

## 13.የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ አፈፃፀም

ግዥ ፈጻሚ አካላት በግልፅ ጨረታ ዘዴ ግዥን ለመፈፀም በቢሮው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም እና ከዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩትን አፈጻጸሞች በቅደም ተከተል መፈጸም አለባቸው።

### 13.1. ቅድመ-ሁኔታዎች

ግዥ ፈጻሚ አካላት በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ግዥን ለመፈፀም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

1. የሚፈለገውን ግዥ በአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ሊሟላ መቻሉን እና ግዥው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 ለዓለም አቀፍ ጨረታ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በታች ሲሆን፣ ወይም
2. የግዥ መጠኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ ሁለት ላይ ከተገለጸው የገንዘብ ገደብ በላይ ቢሆንም ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገኝ መሆኑ፣

### 13.2. የግልጽ ጨረታ ጥሪ

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ለማድረግ በቂ ለሆነ ጊዜ የጨረታ ጥሪው ይፋ መደረጉን ማረጋገጥ አለባቸው። የጨረታው ጥሪው ቢያንስ ሰፊ ተነባቢነት ባለው በአንድ ጋዜጣ አንድ ጊዜ ታትሞ መውጣት ወይም ይፋ መደረግ አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና በዌብ ሳይት እንዲሁም በአካባቢ ማስታወቂያው በተጨማሪ እንዲገለፅ ማድረግ ይገባል።
2. የጨረታው ጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ሊይዝ ይገባል።
   - 2.1 የጨረታውን ጥሪ በማስታወቂያ እንዲወጣ ያደረገው የግዥ ፈጻሚውን አካል ስምና አድራሻ፣
   - 2.2 የሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ዓይነት፣ ብዛት እና ርክክቡ የሚፈፀምበትን ቦታ ወይም የግንባታ ሥራውን ዓይነት እና የሚከናወንበትን ቦታ ወይም የምክር የአገልግሎቱን ዓይነት እና የሚካሄድበትን ቦታ፣የጨረታው ተሳትፎ ዜግነትን ሳይመለከት ለማንኛውም አቅራቢ ወይም ሥራ ተቋራጭ ክፍት መሆኑን እና ይህም የማይለወጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ፣
   - 2.3 በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባውን መሥፈርት፣ የጨረታው ሠነድ የሚገኝበትን አኳኋን እና ቦታ፣
   - 2.4 የጨረታውን ሠነድ ለመውሰድ ሊከፈል የሚገባ ዋጋ ካለ በምን አገር ገንዘብ እንደሚከፈል እና የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ዓይነት፣ መጠንና የአከፋፈሉን ዘዴ፣
   - 2.5 የመጫረቻ ሠነዱ ገቢ የሚደረግበትን ቦታ፣ የመጀመሪያና የመጨረሻ ቀን፣ ጨረታው የሚከፈትበትን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣
   - 2.6 መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን ይህም ሲባል ጨረታው በመሰረዙ ተጫራቾች በጨረታው ለመወዳደር ላወጡት ወጪ መ/ቤቱ ኃላፊነት የማይወስድ መሆኑን፣
   - 2.7 ለተጫራቾች መገለፅ እንዳለባቸው በመ/ቤት የታመነባቸው ሌሎች ጉዳዮች፣

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም በአካባቢ ማስታወቂያ ብቻ መጠቀም የሚፈቀደው በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ ከታች ከተመለከተው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ሲሆን ነው።

3.1 የክልል ሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ የዞን፣የወረዳና የከተማ አስተዳደር የሚገኙ ጽሎች፣ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ተቋማት (ሆስፒታሎች፣ የምርምር ማዕከላት፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ማረሚያ ቤቶች) የገንዘብ መጠን እስከ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ አምሳ ሽህ ብር )

3.2 በዞንና ወረዳ አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ ሌሎች የክልል ተጠሪ መ/ቤቶች እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሽህ ብር)፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ግዥ በአካባቢ ማስታወቂያው መጠቀም ይችላሉ።

4. ግዥ ፈጻሚ አካላት የአካባቢ ማስታወቂያ በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፤

4.1 በግዥ አፈጻጸም ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘትን ማረጋገጥ፣

4.2 የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥው መጠነኛ የሆነና በአካባቢው ብዙ አቅራቢ ያለው መሆኑ ሲታመንበት፣

4.3 ለአፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ለሦስተኛ ወገን ግልፅና የማያሻማ መሆን ይኖርበታል፣

5. ግዥ ፈጻሚ አካላት ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ማስታዎቂያውን ከመለጠፍ በተጨማሪ በየመሥሪያ ቤታቸው ቁልፍ ያላቸው ቋሚ የማስታወቂያ ሰሌዳ በማዘጋጀት መጠቀም አለባቸው፡፡ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶችም ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመመካከር ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች የአካባቢ ማስታወቂያ ለመለጠፊያ የሚያገለግሉ ቁልፍ ያላቸው ቋሚ የማስታወቂያ ሰሌዳ ማዘጋጀት አለባቸው።

6. የሚወጣው የአካባቢ ማስታወቂያ በአካባቢው ለሚገኘው ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማድረስ እንዲለጠፍ ማድረግ ያስፈልጋል፣

## 13.3. የጨረታ ሠነድ

### 13.3.1. መደበኛ የጨረታ ሰነድ ስለመጠቀም

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ለሚያዘጋጁት የጨረታ ሰነድ በቢሮው የተዘጋጀውን መደበኛ የጨረ ሰነድ መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ከዚህ በ ች በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 13.3.2.እስከ 13.3.6 የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት የጨረ ሰነድ በሚያዘጋጁበት ወቅት በቢሮው ከተዘጋጀው መደበኛ የጨረታ ሠነድ ውስጥ በተጫራቾች መመሪያ እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ሳያደርጉ በሌሎች የሰነዱ ክፍሎች ላይ እንደግዥው አይነትና ባህርይ ማሻሻያ በማድረግ ሠነዱን ማዘጋጀት አለባቸው::

3. የጨረታ ሰነድ በዋናነት በግዥ ኦፊሰሮች የሚዘጋጅ ሲሆን በጨረታ ግምጋሚው ደረጃ ለሚፈጸም ግዥ የሚዘጋጀው ማንኛውም የጨረታ ሰነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ አለበት፣

4. እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም ግዥ ሲፈፀም ተመሳሳይ የሆኑ ዕቃዎችን በአንድ ምድብ (ሎት) በማድረግ ውድድሩ በጥቅል ዋጋ ቢሆን ተመራጭ ይሆናል።

### 13.3.2. የተጫራቾች መመሪያ

1. ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል የመደበኛ የጨረታ ሠነዶች አንዱ ክፍል ሆኖ የተዘጋጀውን የተጫራቾች መመሪያ እና የዚሁ አካል የሆነውን የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጐ ለተጫራቾች መስጠት አለበት፡፡ በግዥ ፈጻሚ አካላት የሚዘጋጀው የተጫራቾች መመሪያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆኑን መ/ቤቶቹ ማረጋገጥ አለባቸው።

1.1. የሚገዛውን ዕቃ ወይንም የግንባታ ስራ፤ የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ፤ የመ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ እንዲሁም የግዥውን የበጀት ምንጭ፣

1.2. ማንኛውንም ጨረታ ለመገምገም በሥራ ላይ የሚውሉትን ዘዴዎች እና ለዚሁ ግምገማ የሚያገለግሉትን መስፈርቶችና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን የነጥብ ድርሻ፡እንዲሁም ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ እጩ ተወዳዳሪዎች በግምገማው እኩል ቢሆኑ አሸናፊውን ተጫራች ለመለየት የመወዳደሪያ ሐሳብ የሚቀርብበት ሁኔታና መስፈርቶች፣

1.3. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ የዕቃውን ዓይነት፣ የአምራቹን ስም፣ የተመረተበትን አገር፣ የሞዴሉን ቁጥር፣ የተመረተበትን ዓመት የሚያጠቃልል ዝርዝር እና፣

1.4. አቅራቢዎች ሕጋዊና በዘመኑ የታደሰ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ፣ ከመንግሥት የሚጠበቅባቸውን የዘመኑን ግብር የከፈሉ ስለመሆናቸውና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተቀበሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለባቸው፣

1.5. የወጣው ጨረታ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሽህ ብር/ ዋጋ እና በላይ እንደሚሆን ሲገመት ከተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ነፃ ከሆኑ አቅርቦቶች ወይም እንዳይሰበሰብባቸው በተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ አዋጅ የተፈቀደላቸው ካልሆኑ በስተቀር በግዥው የሚሳተፍ ማንኛውም የአገር ውስጥ ተጫራች በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እንዳለባቸው፤

1.6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1.5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግዥው መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ አስመጭዎች፣ የኮምፒዩተር እና ተዛማጅ እቃ አቅራቢዎች፣ ወርቅ ቤቶች፣ ከደረጃ 1-9 ያሉ የሥራ ተቋራጮች እና ሌሎች በመመሪያ ግዴታ የተጣለባቸው በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆን ግዴታ ነው።

1.7. ቫት የሚጠየቀው የአንዱ ወይም በምድብ/ሎት/ የሚገዛው ዕቃ ዋጋ ብር 100,000.00 /መቶ ሺህ ብር/ እና ከዚያ በላይ ለሚፈፀሙ ግዥዎች ነው፡፡

1.8. በማንኛውም ግዥ ለዕቃዎች ከብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ በላይ እና ለአገልግሎት ከብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ በላይ ለሚሆኑ ግዥዎች አቅራቢው ከሚፈጸምለት ክፍያ ላይ 2% የቅድመ ግብር ተቀንሶ የሚቀር መሆኑን።

1.9. የመጫረቻ ሰነዱ በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ መቅረብ እንዳለበት። በጥንቃቄ ታሽጎ እስከቀረበ ድረስም በሰም ታሽጎ ያለመቅረቡ ከጨረታ ውጭ እንደማያስደርግ፣

1.10. ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ሰነድ ይዘት ምን መሆን እንዳለበት፤ በምን ቋንቋ መዘጋጀት እንዳለበት፤ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለፁ እና በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች እና ቅፆች አይነት እና ብዛት፣

1.11. የውጭ አገር ተጫራች በሚሆኑበት ጊዜ እንደ አግባብነቱ በተቋቋሙበት አገር የተሰጣቸውን የኩባንያ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም ፈቃድ ማቅረብ እንዳለባቸው፣

1.12. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ስማቸውን፣ ፊርማቸውን እና ሙሉ አድራሻቸውን ማስፈር እና የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት /ያለባቸው/ መሆኑን፣

1.13. የጨረታ ሳጥኑ የሚገኝበት ቦታ፣ የጨረታው ማቅረቢያ ጊዜ የሚያበቃበትን ቀን፣ ሰአት፣ የጨረታ አዘጋግ ስርአቱን፤ ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተቀባይነት እንደማይኖረው የሚገልፅ መግለጫ ፣ ጨረታው የሚከፈትበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣

1.14. የጨረታ መዝጊያው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል እንደማይችሉ የሚያመለክት መግለጫ፣

1.15. ጨረታውን ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ እንደሚሆኑ ለወደፊቱም በመንግሥት የግዥ ጨረታ እንዳይሳተፉ እንደሚደረግ እና ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና እንደሚወረስ የሚያመለክት መግለጫ፣

1.16. የዕቃዎቹ ናሙናዎች በጨረታው እንዲቀርቡ የሚያስፈልጉ ከሆነ ተፈላጊዎቹ ናሙናዎች የሚቀርቡበትን እንደአስፈላጊነቱ በተጫራቾች የሚታዩበትን ጊዜ እና ቦታ እንዲሁም ናሙናዎቹ በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚመለሱ ወይም ሊመለሱ የማይችሉ መሆናቸውን፤

1.17. የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲሁም የርክክቡን ቦታና ጊዜ፣

1.18. ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው፣

1.19. በውል አፈጻጸሙ ወቅት የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ መቻል ያለመቻሉን እና የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚፈቀድ ከሆነ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሁኔታ፣

1.20. የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ እና የሥራ አፈፃፀም ዋስትና /የውል ማስከበሪያ /መጠን እንዲሁም እነዚህ ዋስትናዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ ፣

1.21. በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለአገር ውስጥ ምርትና ኩባንያዎች የተፈቀደውን ልዩ አስተያየት ዝርዝር አፈጻጸም የሚያመለክት መግለጫ፣

1.22. ተጫራቹ ስለማጭበርበር እና ሙስና /ጉቦ መስጠትን እና መቀበልን ጭምር/ በኢትዮጵያ ሕጐች የተደነገገውን የሚያከብር መሆን እንዳለበት፣

1.23. ግዥ ፈጻሚው አካል ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሰነዱ ከተገለጸው የአቅርቦት መጠን ላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው በውድድሩ የተገኘው ዋጋ ሳይቀየር እስከ 20% (ሃያ በመቶ) ለመቀነስ ወይም ለመጨመር እንደሚችል፣

1.24. ጨረታው በአንድ ወይም በሁለት ኢንቨሎፕ ወይም ፖስታ ታሽጎ የሚቀርብ ስለመሆኑ፣ አንድ ወጥ የሆኑ ዋና እና ቅጂ ሠነዶች መቅረብ እንዳለባቸው፣ የቅጂዎቹ ብዛት፣ ሠነዶቹ ሥልጣን ባለው አካል የተፈረመባቸው ሊሆኑ እንደሚገባ እና ማህተም እንደሚያስፈልጋቸው፣ ደጋፊ ማረጋገጫዎች፣

1.25. በጨረታ ሰነዱ ግልፅ ያልሆኑ ጉዳዮች ማብራሪያ የሚጠየቅበትን አድራሻ፣ ጊዜ እና ማብራሪያ መጠየቅ እንደሚችል የሚገልፅ መግለጫ፣

1.26. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.22 በተደነገገው መሠረት የቅድሚያ ክፍያ የሚሰጥ ከሆነ የቅድሚያ ክፍያውን መጠን ቅድሚያ ክፍያ ለመውሰድ ዋስትና የሚያስፈልግ መሆኑና የዋስትናውን ዓይነት፣

1.27. መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣

1.28. ተጫራቾች በጨረታው የአፈጻጸም ሂደት ቅሬታ ካላቸው በግዥ አዋጁ አንቀጽ 56፣ 57 እና 38 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 38 መሠረት አቤቱታ ማቅረብ መብት እንዳላቸው

2. በመደበኛ የጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ይዘት ላይ ምንም አይነት ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም። በተጫራቾች መመሪያ ላይ የሚደረጉት ለውጦች የሚመለከቱት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ነው።

### 13.3.3. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ

1. በባህሪያቸው ውስብስብ በሆኑና ከፍተኛ ወጪን በሚጠይቁ ግዥዎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያሟላ ዝርዝር ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የዚህ ዓይነቱ ዝርዝር በተለይም በተፈጥሮአቸው ውስብስብ እና ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቁ የዕቃና አገልግሎት ግዥዎችን በተመለከተ መሠረታዊ ነው። ስለዚህ የጠቀሜታ ዝርዝር /ስፔስፊኬሽን/ በመባል የሚታወቀው በተጠቃሚዎች ፍላጐት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የሚፈለገውን ለማሟላት ያላቸውን ተፈጥሮ፣ የሚያስገኙትን ውጤት፣ በመ/ቤቱ ውስጥ ሊያስገኙ የታሰበውን ጠቀሜታ የሚጠይቀውን የቴክኒክ ብቃት፣ የአሠራር ባህሪያቸውን እና የታቀደላቸውን ሥራ ለማከናወን ያላቸውን የብቃት ደረጃ የሚያካትት ዝርዝር መግለጫ የሚይዝ እና ውድድርን የሚደግፍ ሆኖ መዘጋጀት አለበት።

2. የተጠቃሚው ፍላጐት ወይም የዕቃው ጠቀሜታ ዝርዝር መታወቅ ከሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች መካከል የሚከተሉት ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

   2.1 የሚፈለገውን ጠቀሜታ ለማስገኘት ያላቸውን ብቃትና ወጪ ለተደረገው ገንዘብ ተመጣጣኙን ማስገኘታቸውን ማረጋገጥ ያስችላል፣

   2.2 ጨረታውን ለማዘጋጀት እና ጨረታው ከወጣ በኋላም ግምገማውን ለማከናወን መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ የጠቀሜታና የቴክኒክ ዝርዝሮች እንዲኖሩት ይረዳል፣

   2.3 የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የውሉ አንድ ክፍል በመሆን የጨረታ አሸናፊውን የሥራ አፈፃፀም ለመቆጣጠርና የአቅርቦትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያስችላል።

3. የሚፈለገው ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ የግንባታ ሥራ ወይም አገልግሎት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ዝርዝር እስከተቻለ ድረስ ግዥው እንዲፈፀምለት በሚፈልገው የሥራ ሂደት ወይም ስለሚፈፀመው ግዥ በቂ እውቀት ባላቸው የመ/ቤቱ ባለሙያዎች መዘጋጀት አለበት። ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ እና ውስብስብ በሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር አዘገጃጀት ላይ አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ከመ/ቤቱ ውጪ ያሉ ለሙያው ቀረቤታ ያላቸውን ባለሙያዎችን ድጋፍ ሊጠይቁ ወይም አማካሪ ቀጥረው ሊያሰሩ ይችላሉ።

4. የዕቃና አገልግሎት ዝርዝር /የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ/ በሚዘጋጅበት ጊዜ የተወሰነን አምራች፣ የንግድ ምልክት ወይም አገልግሎት ሰጪ ማመልከት የለበትም። ሆኖም፣

   4.1. ፍላጎትን በትክክል ሊገልፅ የሚችል መግለጫ ማዘጋጀት አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

   4.2. ግዥው ለተለየ ፕላንት ወይም መሣሪያ የሚያስፈልጉትን መለዋወጫዎች የሚመለከት ሲሆን፣ ወይም

   4.3. የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችለው አንድ አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ የአምራቹን ወይም የአገልግሎት ሰጪውን ስም በመጥቀስ "ወይም ተመሳሳይ" የሚል ሐረግ እንዲታከል ማድረግ ያስፈልጋል።

5. የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን ደረጃዎች በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት ይችላል።

6. የሚዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መ/ቤቱ ላለው ወይንም ወደፊት ሊፈጠር የሚችል ፍላጎትን ለማርካት የሚያስችሉ የጠቀሜታ እሴቶችን ለመግለፅ የሚያስችል እና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ እሴቶችን ያላካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

7. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች የተሟላና ትክክለኛ የመወዳደሪያ ሃሣብ እንዲያዘጋጁ በሚያስችል ዓይነት ተሟልቶ እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ የጨረታው ሰነድ አንድ ክፍል መሆን አለበት።

### 13.3.4. ለግዥ ስለሚቀርብ ናሙና

1. የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወይንም ከተዘጋጀው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በተጨማሪነት ግዥው በተሻለ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የናሙና ምልከታ ሲኖረው መሆኑ ሲታመንበት ግዥ ፈጻሚው አካል በተጨማሪነት ናሙና ሊያቀርብ ወይንም እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል።
2. ግዥ ፈጻሚው አካል ናሙና ራሱ አቅርቦ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ናሙና ዓይነት ምርት እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፣
   1.1. በግዥ ፈጻሚው አካል የሚቀርበው ናሙና በአንድ አምራች ወይም የንግድ ምልክት በተሠራ ዕቃ የተወሰነ መሆን የለበትም። እስከተቻለ ድረስ ተቀባይነት ያላቸው ናሙናዎች አይነት ለእይታ እንዲቀርቡ ሆኖ የሌሎች ከቀረቡት ናሙናዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጥራት ደረጃ ያለው ዕቃ ማቅረብ ንደሚችሉ ተጫራቾች ንዲያውቁት ማድረግ ይገባል።
   1.2. ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙናውን በግልፅ የሚያዩበት ቦታ ላይ መደረጉን እና ተገቢ እስከሆነ ድረስ ስለናሙናው መግለጫ የሚሰጥ ባለሙያ መመደቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
   1.3. ግዥ ፈጻሚው አካል ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዕይታ ካቀረበው ናሙና በተጨማሪ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ የሚያዘጋጅ ከሆነ የሚዘጋጀው መግለጫ እስከተቻለ ድረስ የቀረበውን ናሙና የሚገልፅ መሆን ያለበት ሲሆን የቀረበው ናሙና ካለው የቴክኒክ ባሕርይ ውጪ ያለ ባሕርይ በቴክኒክ መግለጫው ውስጥ እንዲካተት ሊደረግ አይገባም።
3. በተሰጣቸው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ መሰረት ዕጩ ተወዳዳሪዎች ናሙና እንዲያቀርቡ በሚፈለግበት ወቅት፣
   3.1. የሚቀርቡት ናሙናዎችን አይነት፣ ብዛት፣ የሚቀርቡበት ጊዜ እና አኳኋን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል።
   3.2. ናሙናዎች ጨረ ው ከመከፈቱ በፊት መቅረብ ያለባቸው ሲሆን ዕጩ ተወዳዳሪው ናሙናውን በወቅቱ ልኮ በማጓጓዝ ሂደት ከዕጩ ተወዳዳሪው ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት ቢዘገይ ግዥ ፈጻሚው አካል የግዥውን አፈፃፀም አይጎዳም ብሎ እስካመነ ድረስ ተጨማሪ የናሙናው የማቅረቢያ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል።
4. ተጫራቾች የተሟላ ናሙና በአካል ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን እና የማይችሉበትንም ምክንያት ግዥ ፈጻሚው አካል ሲቀበለው ስለናሙናው ያላቸውን መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ ሊፈቀድ ይችላል። ይህም የናሙናውን ፎቶግራፍ ወይም የተገኘውን የናሙና ክፍል ማቅረብን ይጨምራል። ሆኖም በዚህ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻለው አፈፃፀሙ የተሻለውን ተጫራች በመምረጥ ሒደት ልዩነት የማያመጣ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

5. ግዥ ፈጻሚው አካል በተጫራቾች የቀረቡ ናሙናዎችን በጥንቃቄ የመያዝ እና የመፈተሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ያቀረቡት ናሙና በሚመረመርበት ወቅት በራሱ ተፈጥሮ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ካሣ አይከፈላቸውም። ከምርመራ በኋላ ከአሸናፊው ናሙናዎች በስተቀር ተጫራቾች ያቀረቡትን ናሙና የጨረታ ውጤት ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ60 ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ እንዲወስዱ ተገልጾላቸው ጠይቀው ካልወሰዱ ለመንግሥት በውርስ ገቢ ይደረጋል።
6. በግዥ ፈጻሚው አካል የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር የአሸናፊውን ተጫራች ናሙና ግዥው እስከ ሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ በናሙናነት በሚመለከተው የንብረት ክፍል ሰራተኛ በጊዜያዊነት ተይዞ መቆየት ያለበት ሲሆን ናሙናውም በርክክብ ወቅት ለማነፃፀሪያነት እንዲያገለግል ይደረጋል፡፡

### 13.3.5. የጨረታ ቅጽና የዋጋ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

ግዥ ፈጻሚ አካላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተጫራቾች የሚሞላ የጨረታ ሃሣብ ማቅረቢያ ቅፅና የዋጋ ሠንጠረዥ በጨረታው ሠነድ ውስጥ እንዲካተት ያደርጋሉ። በዚህም ጊዜ፣

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ለጨረታ በሚያዘጋጁት የጨረታ ሠነድ ውስጥ እንደግዥው ባህርይ መ/ቤቱ ያዘጋጀውን በተጫራቾች ሊሞላ የሚገባውን የጨረታ ቅፅ፣ ዋጋና ተያያዥ ጉዳዮችን ማቅረቢያ ቅጽ ወይም ሠንጠረዥ እና እንደግዥው ዓይነት እና ሁኔታ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ውስጥ መካተታቸው ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመንባቸው ሌሎች ቅፆችን ማካተት አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "1" መሠረት በግዥ ፈጻሚ አካላት የሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ እንደአስፈላጊነቱ ዋጋን፣ ታክስን እና ሌሎችን ለይቶ የሚያመለክትና የጨረታ ግምገማን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት።
3. የሚዘጋጀው የጨረታ ቅፅ በተቻለ መጠን ዕጩ ተወዳዳሪው ግልፅ የሆነ የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርብ የሚያስችል፤ የጨረታ አካሄዱን መረዳቱን የሚያረጋግጥ፤ ጨረታውን የሚያደናቅፍ ተግባራት እንዳይፈፀም እና ላቀረበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

### 13.3.6. የውል ሁኔታዎች

የውሉ ሠነድ የሥራውን ስፋት፣ መቅረብ ያለባቸውን ዕቃዎች እና መሰጠት ያለባቸውን አገልግሎቶች፣ የግዥ ፈጻሚውን አካል እና የአቅራቢውን ወይም የሥራ ተቋራጩን መብትና ግዴታ እንዲሁም ግዥ ፈጻሚው አካል የግንባታ ሥራ ባለሙያ ወይም አማካሪ ቀጥሮ ከሆነ የእነዚህን ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ የሚያሳይ መሆን አለበት። ከውሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች በተጨማሪ ከሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት የተለየ ባህሪይ ጋር የሚሄዱ ልዩ ሁኔታዎችን እና ፕሮጀክቱ የሚከናወንበትን ቦታ የሚያመለክት መሆን አለበት፣ በዚህ መንገድ የሚዘጋጁት

ውሎች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ከሕግ አኳያ አዋጭነታቸውን ለማረጋገጥ የአካባቢውን የፍትህ አካላት የህግ ሙያዊ አስተያየት ማካተት ይገባል። የሚዘጋጀው የውል ሰነድ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

1. ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል የመደበኛ የጨረታ ሠነድ ክፍል ሆነው የተዘጋጁትን አጠቃላይ እና ልዩ የውል ሠነድ ቅጇዎች የጨረታው ሰነድ ክፍል አድርጎ ለተጫራቾች መስጠት አለበት::
2. በመደበኛ ጨረታ ሠነዱ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሻሻያ ሊደረግባቸው አይችልም :: ልዩ የውል ሁኔታው ግን እንደ መ/ቤቱ ግዥ ባህርይና ዓይነት ማሻሻል ይቻላል::
3. በዚህ ንዑስ አንቀጽ "1" እና "2" የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚያዘጋጁት ልዩ የውል ሁኔታ እንደግዥው አይነት ሊለያይ ቢችልም የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት::
   3.1. የተጫራቹንና የግዥ ፈጻሚን አካል ግዴታና ሃላፊነትን በግልጽ ያመላከተና በመ/ቤቱ ላይ የሚጣሉ ግዴታዎች ህጋዊ መሠረት ያላቸውና ሊፈጸሙ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
   3.2. እንደአስፈላጊነቱ የውሉ አፈጻጸም የሚከተላቸውን ዋና ዋና ሂደቶች፣ የማስረከቢያ ጊዜ፣ አስተሻሸግ፣ የዋጋ ማስተካከያ፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የርክክብ እና የፍተሻ ስነ-ስርአት፤ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አተገባበር በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 14.4. በጨረታ ሠነድ ላይ ስለሚደረግ ማብራሪያ ወይም ማሻሻያ

1. በአዋጁ አንቀጽ 24 መሠረት ግዥ ፈጻሚ አካላት ከማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የሚቀርብ የማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄን ተቀብለው ምላሽ መስጠት አለባቸው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የሚከተለውን ሳያሟላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ መሥሪያ ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም::
   2.1 በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሰረት ጨረታ በአየር ላይ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ ለ30 ተከታታይ ቀናት ለሆነ ውስብስብ የአገር ውስጥ ግዥ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ20ኛው ቀን በኋላ ለቀረበ ጥያቄ፣
   2.2 ለዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ25ኛው ቀን በኋላ ለቀረበ ጥያቄ፣
   2.3 ጨረታ በአየር ላይ የሚቆይበት ዝቅተኛ ጊዜ 15 ተከታታይ ቀናት ብቻ ለሆኑ ውስብስብ ላልሆኑ ግዥዎች ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከ10ኛው ቀን በኋላ ለቀረበ ጥያቄ፣
3. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል በግዥ ፈጻሚው አካል በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት የማሻሻያ ሃሳብ ያቀረበውን አካል ማንነት መግለጽ ሳያስፈልግ የጨረታ ሠነዱን ማሻሻል ይችላሉ:: የተሻሻለው ወይም ማንኛውም የጨረታ ሠነዱን ይዘት የሚቀይር ሰነድ፤ ማሻሻያ በሚል የጨረ ታውን ሠነድ ለገዙና በቀጣይ ለሚገዙ ተጫራቾች ሁሉ በእኩል ጊዜ የተስተካከለው ሰነድ ወይም ደብዳቤ እንዲደርስ መደረግ አለበት::

4. ግዥ ፈጻሚ አካላት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ በተገለፀው መሰረት በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ ሲያደርጉ እና ጨረታውን ለመዝጋት በቀረው ጊዜ ውስጥ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተደረገውን ማሻሻያ አካተው የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት እንደማይችሉ ሲገመት የጨረታ መዝጊያ ቀኑን ማራዘም ይኖርባቸዋል፡፡

5. ግዥ ፈጻሚው አካል አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን በመሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀ የጨረታ ሠነድ ላይ የጨረታ ሠነድ የገዙትን ተጫራቾች በሙሉ የማብራሪያና የማሻሻያ ገለጻና ውይይት ለማድረግ ሊጠራ ይችላል፡፡ የሚደረገው ውይይትም በቃለጉባዔ መያዝ ይኖርበታል።

6. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሠነዳቸውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ማሻሻያውን ማካተት እንዲችሉ በተደረገው የጨረታ ሠነድ ማሻሻያና ማብራሪያ ውይይት ላይ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ ቅጂ ለሁሉም የጨረ ውን ሠነድ ለገዙ ዕጩ ተጫራቾች እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## 13.5. የጨረታ ቋንቋ

1. በአዋጁ አንቀጽ 15 መሠረት የሚዘጋጀው የጨረታ ማስታወቂያ፣ የጨረታ ሠነድ እና ጨረታው የሚካሄድበት ቋንቋ፣
   1.1. የአገር ውስጥ ተጫራቾች ብቻ ለሚሳተፉበት ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በአማርኛ ቋንቋ ይሆናል፡፡ ሆኖም መ/ቤቱ የተሚላ ውድድር እንደሚኖር በማረጋገጥና የጨረታ ቋንቋው በእንግሊዝኛ መሆኑ የተሻለ ውድድርና ጠቀሜታ እንዳለው ሲያምን የጨረታ ማስታወቂያው፣ የጨረታ ሠነዱ፣ እና የጨረታው ሂደት በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል፡፡
   1.2. ለዓለም ዓቀፍ ግልጽ ጨረታ ማስፈጸሚያ የሚዘጋጀው ማናቸውም ሰነድ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ይሆናል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕጩ ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዶቻቸውና ደጋፊ ማስረጃዎቻቸው በጨረታ ሠነዱ ጨረታው እንዲካሄድበት ከተፈቀደው ውጭ በሌላ ቋንቋ የተዘጋጀ በሚሆንበት ጊዜ የጨረታ ሠነዱን በሕጋዊ ተርጓሚ ከተተረጎመ ቅጂ ጋር አንድ ላይ በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ግዥ ፈጻሚ አካላት በተጫራቹ የቀረበው ሠነድ በመጀመሪያ በተዘጋጀበት እና ለጨረታው በተፈቀደው ቋንቋ ትርጉም መካከል ልዩነት እንዳለው ሲያረጋግጥ ልዩነቱ በጨረታው ይዘት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ያመጣል ብሎ ካመነ ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 13.6. የጨረታ ዋጋና የዋጋ ማስተካከያ

13.6.1. የግዥ ፈጻሚው አካል ከተጫራቾች የሚሰጡ የመጫረቻ ዋጋዎች በሌላ ተጫራች ዋጋ ላይ ያልተመሰረቱ እና በጨረታው እና በውል አፈፃፀሙ ወቅት የማይለዋወጡ ፅኑ ዋጋ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

13.6.2. በዚህ አንቀጽ፩ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተገለፀው ቢኖርም፣ ግዥ ፈጻሚው አካል የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ ለግንባታ ስራዎች ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት 12 /አስራ ሁለት/ ወራት በኋላ እና በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ውሉ ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት 3 /ሰስት/ ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል። ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው፣

1. በውል ስምምነቱ መሰረት የግንባታ ስራውን ለማጠናቀቅ 12 /አስራ ሁለት ወራት/ እንዲሁም በማዕቀፍ ስምምነት ጊዜ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ 6 /ስድስት/ ወራት የሚፈጅ አቅርቦት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣
2. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን፣
3. የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም የጠቋሚ ዋጋ መረጃ መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣
4. በዚህ አንቀጽ፩ በንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው ቢኖርም የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መስጠት ባልቻሉባቸው ስብስቦች ላይ ግዥ ፈጻሚው አካል የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይገባል ብሎ ሲያምን ለውጥ የሚደረግባቸውን ስብስቦች በያዘው ምድብ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል የዋጋ መረጃ ከታወቀ የአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ማግኘት ሲቻል ይሆናል፣

### 13.6.3. ለግንባታ ሥራ ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፣

በአንቀጽ 13.6.2 የተገለጹት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ከግንባታ ስራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ ከዚህ በታች የተገለጹትን አሠራሮች ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት ይኖርበታል፦

1. ለግንባታ ሥራው የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ግብዓቶችና በእያንዳንዱ ዋና ግብዓት ሥር ሊካተቱ የሚችሉ ዕቃዎችን ስብስብ መለየት፣
2. በሥራቸው የተለያዩ ዕቃዎች ስብስቦችን የያዙት ዋና ዋና ግብዓቶች፣ ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ ግብዓቶች ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ በማስላት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን እና የማይደረግባቸውን መወሰን፣
3. ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሥራ ላይ ያለው የዋጋ ኢንዴክስ /ጠቋሚ አሃዝ በቀመሩ መሠረት የዋጋ ማስተካከያውን ለማስላት በመነሻነት ይወሰዳል፣

4. ተቋራጩ የግንባታ ሥራውን በውል ስምምነቱ መሠረት መፈጸም ሲገባው በወቅቱ ባይፈጽምና በወቅቱ ያልፈጸመበት ምክንያት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 44 ከአቅም በላይ ተብለው ከተዘረዘሩት ችግሮች ካልሆኑ በስተቀር ዘግይተው ለሚከናወኑ ሥራዎች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው ሥራዎቹ መፈጸም በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል::

5. የዋጋ ማስተካከያው ጥያቄ በአንቀጽ 14..6 .2 ላይ የተገለጸውን ድንጋጌ ተከትሎ በሚቀርብበት ወቅት በተለይ ለግንባታ ሥራ ግዥ የዋጋ ልዩነቱ የሚሰላው በሥራ ላይ ያለውን ወቅታዊ የዋጋ ኢንዴክስ ጠቋሚ አሃዝን በመጠቀም በቀመሩ መሠረት ይሆናል፣

13.6.4. በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ

ግዥ ፈጻሚ አካት በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈፀም ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል፣

1. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን አለበት::
2. በማዕቀፍ ስምምነት መሠረት ተፈፃሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከ3 /ሶስት/ ወራት በኋላ ሊሆን ይገባል::
3. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በኮንትራት ውል ስምምነቱ ላይ መገለፅ አለበት::
4. ግዥ ፈጻሚው አካል በውሉ ላይ በተገለፀው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈፃሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ በክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት::
5. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሠረት ማቅረብ ሲገባው በወቅቱ ላላቀረባቸው እና ዘግይተው ለቀረቡ አቅርቦቶች የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ የሚቻለው አቅርቦቶቹ መቅረብ በነበረባቸው ወቅት በነበረው ዋጋ መሠረት ብቻ ይሆናል::

13.6.5. ለምክር አገልግሎት ግዥ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ፣

1. በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መ/ቤቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል::
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአሥራ አምስት ከመቶ ሊበልጥ አይችልም::

13.6.6. ግዥ ፈጻሚው አካል የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶች ለተካተቱበት ግዥ በሚያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ማመልከት ይኖርበታል፣

1. የዋጋ ማስተካከያውን ተግባራዊ ለማድረግ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ያለባቸውን የመረጃ አይነት፣
2. የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው የሚቀርብባቸውን ሁኔታዎች፣ የአቀራረብ ዘዴውን እና ከዋጋ ማስተካከያ ጥያቄው ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማስረጃዎችን አይነትና መጠን፣
3. ሌሎች ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ይጠቅማሉ ተብሎ የሚታመንባቸውን መረጃዎች እና ተጫራቾች ሊከተሉት ይገባል የሚላቸውን አሰራሮች፣

13.6.7. ግዥ ፈጻሚው አካል በጨረታ ግምገማ ወቅት ተጫራቾች ለዋጋ ማስተካከያ ዓላማ የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች መቀበላቸውን እና ያቀረቧቸው ማስረጃዎችም ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

13.6.8. ግዥ ፈጻሚው አካል እና በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች በሚያደርጉት የውል ስምምነት ላይ የሚከተሉት እና ሌሎች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ሁኔታዎች በግልፅ እንዲካተቱ መደረግ ይኖርበታል፣

1. የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግላቸውን ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱ ዕቃዎችን ወይም አቅርቦቶችን ዝርዝር እና የማስተካከያውን አፈፃፀም፣
2. ለዋጋ ማስተካከያው አፈጻጸም ግዥ ፈጻሚው አካል እና አቅራቢው የተስማሙበት የሰነድ አይነት እና ምንጭ፣
3. ለዋጋ ማስተካከያ የሚቀርበው ማስረጃ በውሉ ላይ በተገለፀው መሠረት መሆን እንዳለበት እና ከሌላ ምንጭ የሚመጣ መረጃ ተቀባይነት እንደማይኖረው፣
4. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት በወቅቱ ስራውን ወይም አቅርቦቱን ማከናወን ባለመቻሉ የሚፈጠር የዋጋ መናር ማስተካከያ የማይደረግበት ስለመሆኑ፣

13.6.9. የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋው 25% (ሃያ አምስት ከመቶ) በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን ተረድቶ ተገቢውን ውሳኔ መወሰን እንዲችል የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

13.6.10. ግዥ ፈጻሚው አካል የዋጋ ማስተካከያ ለተፈቀደበት ማንኛውም ግዥ ከአቅራቢው የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ባይቀርብም የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብለት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው በውል ስምምነቱ በተፈቀዱ ግብአቶች ላይ የዋጋ መቀነስ መኖር አለመኖሩን የማጣራትና የዋጋ ቅናሽ ካለም አስልቶ ከቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ ከቀነሰ በኋላ መክፈል ይኖርበታል።

## 13.7. የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

1. ግዥ ፈጻሚው አካል የመጫረቻ ሠነድ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ፀንቶ መቆየት ያለበትን ጊዜ በጥንቃቄ በመወሰን በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ማካተት ይኖርበታል። የመጫረቻ ሰነድ

ወይም የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደ ግዥው አይነት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጊዜውን ለመወሰን ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ. የግዥው ውስብስብነት እና ግዥውን ለመገምገም ሊወስድ የሚችለውን ጊዜ፣

ለ. በጨረታው ሊሳተፉ የሚችሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት፣

ሐ. የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ተመሳሳይ ግዥዎችን በመገምገም ያለው ልምድ፣

መ. ግዥው በገበያ ላይ ያለው የዋጋ ተለዋዋጪነት ግምት ውስጥ ማስገባት፣

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተገለፀው መሰረት የሚወሰነው የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ግዥ ፈጻሚው አካል ግዥውን ለመገምገም፣ ግዥውን ለማፀደቅ፣ አቤቱታ ቢነሳ ለማስተናገድ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል እስከሚገባ ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ በተገለፀው መሰረት የተለየ ሁኔታ መኖሩን መ/ቤቱ ካላመነ በስተቀር የመጫረቻ ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታውን ለመገምገም በርካታ ጊዜ ለሚወስዱ ውስብስብ ግዥዎች ጨረታው ከተከፈተበት ዕለት ጀምሮ ከ60 ቀናት እንዲሁም በርካታ ቀናት ለማይወስዱ ውስብስብ ላልሆኑ ግዥዎች ከ40 ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡

4. ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ ሂደታቸውን የመጫረቻ ሰነዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር ውል መፈራረም ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የግዥ ሂደቱ ሳይጠናቀቅ ለግዥው የቀረበው የመጫረቻ ሠነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃ መሆኑን ግዥ ፈጻሚው አካል ሲረዳ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የመጫረቻ ሰነዳቸው ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለተጨማሪ ቀናት እንዲያራዝሙለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 ላይ በሰፈረው መሰረት የሚጠየቀው ተጨማሪ ቀናት መ/ቤቱ የቀረውን የግዥ ሒደት ለማጠናቀቅ የሚበቃውን ያህል ቀናት ብቻ መሆን ያለበት ሲሆን ተጫራቾች በማንኛውም ምክንያት የመጫረቻ ሰነድ የሚፀናበትን ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆኑ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙትን ዋስትና መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ውድድር እንዲገለሉ ይደረጋል፡፡

6. የቀረበላቸውን የመጫረቻ ሠነድ የመቆያ ጊዜ ማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች መቀበላቸውን እና ጊዜውን በመጥቀስ በጽሑፍ ማረጋገጥ ያለባቸው ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታም ለዚህ ጨረታ ያስያዙት የጨረታ ዋስትና መቆያ ጊዜ አብሮ እንዲሻሻል ማድረግ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 በተገለጸው መሠረት የጨረታ ዋስትናውን ያላሻሻለ ተጫራች የመጫረቻ ሠነዱን የመቆያ ጊዜ ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውድድር ውጭ እንዲሆን ይደረጋል::

## 13.8. ጨረታ በአየር ላይ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ስለመወሰን

1. ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ መወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን የሚከተሉትን መሠረት አድርጎ ይወስናል፡፡

1.1 ዕጩ ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሠነዱን ለማግኘት፣ ተቀባቀይነት ያለው የመጫረቻ ሠነድ ለማዘጋጀት መረጃ ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን እና ሌሎች ለጨረታው የሚፈለጉ ከአምራቹ የሚሠጥ ውክልና እና የመፈረም ሥልጣን ማረጋገጫ እና የመሳሰሉትን ለማውጣት የሚፈጅባቸውን ጊዜ፣

1.2 ግዥው በዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የሚፈፀም ሲሆን የመጫረቻ ሠነዱን የጨረታ ማቅረቢያው ቦታ ድረስ ለመላክ የሚያስፈልገውን ጊዜ፣

1.3 በተለይ የግንባታ ሥራ ግዥ በሚሆንበት ጊዜ የግንባታ ቦታ ጉብኝትና ከጨረታ በፊት ለሚደረግ ቅድመ ጨረታ ውይይት የሚፈልገውን ጊዜ፣

## 13.9. ጨረታ በአየር ላይ የሚቆይበት አነስተኛ ጊዜ እና ድጋሚ ጨረታ ስለማውጣት

1. ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረታ ሰነድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የመጫረቻ ሰነድ ወይም የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 14.8. የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰን አለበት። ይሁን እንጅ ጨረታው የሚቆይበት አነስተኛ ጊዜ ቢያንስ ፡-

1.1 ለብሔራዊ /ለአገር ውስጥ/ ግልጽ ጨረታ ግዥው ውስብስብ የሆኑ ግንባታና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው የምክር አገልግሎት ግዥ ሲሆን 30 ተከታታይ ቀናት፣ ውስብስብ ላልሆኑ 21 ተከታታይ ቀናት፣ ውስብስብ የሆኑ ለዕቃዎችና ሌሎች አገልግሎት ግዥዎች 30 ተከታታይ ቀናት ውስብስብ ላልሁኑ ለዕቃዎችና ሌሎች አገልግሎት ግዥዎች 15 ተከታታይ ቀናት፤

1.2 ለብሔራዊ /ለአገር ውስጥ/ ውስን ጨረታ ግዥው ውስብስብ የሆነ ግንባታና ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለው የምክር አገልግሎት ግዥ ሲሆን 30 ተከታታይ ቀናት፣ ውስብስብ ያልሆነ ግንባታና የምክር አገልግሎት ግዥ ሲሆን 21 ተከታታይ ቀናት፣ ውስብስብ ለሆኑ ዕቃዎችና ሌሎች አገልግሎት ግዥዎች 30 ተከታታይ ቀናት ውስብስብ ላልሆኑ ዕቃዎችና ሌሎች አገልግሎት ግዥዎች 15 ተከታታይ ቀናት መሆን አለበት/ጨረታ በአየር ላይ መቆያ አነስተኛ ጊዜ በአባሪ ቁጥር 8 ላይ ተያይዟል/።

1.3 ለዓለም አቀፍ ውስብስብ ግዥዎች 45 ተከታታይ ቀናት ውስብስብ ላልሆኑ ግዥዎች 35 ተከታታይ ቀናት መሆን አለበት፤ (ውስብስብና ውስብስብ ያልሆነ የሚለው በአባሪው ቁጥር 3 ላይ ተያይዟል)

2. ድጋሚ ጨረታ ማውጣት የሚፈቀደው ፣

2.1 በጨረታው ሰነድ የቀረበው ዋጋ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አለመሆኑ ማለትም ከፍተኛ ወይም የተጋነነ ዋጋ መሆኑ ሲታወቅ፣

2.2. የቀረበው አንድ ተጫራች ብቻ ሲሆንና ይኸው ተጫራች በብቸኝነት እንዲቀርብ ያስቻለው በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ሥርዓቶች ያልጠበቀ አሠራር /ሁኔታ/ መኖሩ ሲረጋገጥ ነው፣

2.3 ድጋሚ ጨረታ በሚወጣበት ወቅት ጨረታው በአየር ላይ ቆይታው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሠረት ተፈጻሚ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚው አካል የቀረበው አንድ ተጫራች የመወዳደሪያ ሃሣብ አጥጋቢና ዋጋውም ያልተጋነነ የገበያ ዋጋ መሆኑን እንዲሁም የሌሎችን ተወዳዳሪዎች ተሣትፎ የሚገድቡ ምክንያቶች ያለመኖራቸው ይህም ሲባል ጨረታው በጋዜጣ ታትሞ መውጣቱ በትክክል ከተረጋገጠ በኋላ የቀረበውን አንድ ተጫራች አሸናፊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 13.10. የጨረታ ሰነድ ሽያጭ

1. ለማንኛውም ጨረታ የተዘጋጀው የጨረታ ሠነድ የመሸጫ ዋጋ በአዋጁ አንቀጽ 24 መሠረት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት በግዥ ፈጻሚ አካላት የሚወሰን ይሆናል፤

1.1. የጨረታ ሰነድ መሸጫ ዋጋ ግዥ ፈጻሚው አካል ለግዥው በርካታ ተወዳዳሪዎችን እንዳያገኝ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

1.2 ግዥ ፈጻሚ አካላት ለማንኛውም የጨረታ ሠነድ የዋጋ ተመን በሚወስኑበት ወቅት ትርፍን ማዕከል ያላደረገና ለሰነድ ዝግጅቱ የወጣውን ወጪ ለመተካት ብቻ ያለመ መሆን ይኖርበታል፡፡

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ሠነዱ በነፃ እንዲሠጥ ወይም ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ ከወጣው ወጪ ባነሰ ለተጫራቾች እንዲሸጥ ሊፈቅዱ ይችላሉ፤

2.1. በጨረታው በቂ ተወዳዳሪ አለመኖር ወይም፣

2.2. ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት በጣም አነስተኛ ነው ብሎ መ/ቤቱ ሲያምን ወይም፣

2.3. ለጨረታ ሠነድ ዝግጅቱ የወጣው የወጪ ግምት ከፍተኛ በመሆኑ ወጪውን ሙሉ በሙሉ ተጫራቾች እንዲሸፍኑ ቢደረግ የጨረታ ሰነዱ የመሸጫ ዋጋ ከፍተኛ ስለሚሆን በቂ ተወዳዳሪ እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል ብሎ ሲያምን፣

2.4. ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ የተደረገ እና በመጀመሪያው ጨረታ ለመሳተፍ ሰነድ የገዙ እጩ ተወዳዳሪዎችን እንደገና እንዲገዙ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑ በመ/ቤቱ ሲታመን፣

3. የጨረታ ሠነዱ ጨረታው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚዘጋበት ጊዜ ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት በጨረታ ማስታወቂያው በተገለጸው አኳኋን ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝግጁ መሆን አለበት።

4. ግዥ ፈጻሚ አካላት የጨረታ ሰነድ በሚሸጡበት ጊዜ በጨረታው የሚወዳደረውን ሰው ወይም ድርጅት ሙሉ ስም አድራሻ የስልክና የፋክስ ቁጥር በትክክል መዝግበው መያዝ አለባቸው።

5. ቀደም ሲል በመንግሥት በወጡ ጨረታዎች የገባውን ግዴታ ሣያከብር በመቅረቱ፣ ስልጣን ባለው አካል የታገደ ማለትም በቢሮው ዌብ ሳይት ጥቁር መዝገብ የተመዘገበ ከሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረታ ሰነድ መሸጥ የለበትም።

## 13.11. የመጫረቻ ሰነድ መረከብ

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን የሚያስገቡበት የጨረታ ሳጥን ማዘጋጀት አለባቸው:: የጨረታ ሳጥኑም የጨረታ ጥሪው ላይ በተገለፀው ቦታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመዝጊያ ሰዓት ድረስ ክፍት ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፡፡
2. የጨረታ ሳጥን ደህንነት የተጠበቀ መሆን ስለአለበት ጨረታው እስከሚከፈት ድረስ ቁልፉ በቃለ-ጉባኤ እየተደገፈ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ እና ሌሎች ግዥ እንዲፈፅሙ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደት ባለቤቶች ወይም አስተባባሪዎች ተይዞ መቆየት ይኖርበታል።
3. እስከተቻለ ድረስ ማንኛውም የመጫረቻ ሰነድ ለጨረታው በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ሆኖም ለግዥው የሚቀርበው የመጫረቻ ሠነድ በሳጥን ውስጥ ሊገባ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ ከግዥ ኦፊሰሮች መካከል አንዱ በዙር እየተመደበ የጨረታ ጥሪ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ በተጫራቾች የሚቀርብን የመጫረቻ ሰነድ መረከብ ይኖርበታል፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ በተገለጸው መሰረት ግዥ ፈጻሚው አካል ለሚረከበው የመጫረቻ ሰነድ መረከቡን የሚያረጋግጥ የተጫራቹን ስም፣ የተረከበበትን ቀንና ሰዓት የሚገልፅና በፊርማ የተደገፈ የመተማመኛ መረጃ በጽሁፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት ገቢ የተደረጉ የመጫረቻ ሰነዶች ደህንነት መጠበቁን ግዥውን ለመፈጸም የተመደበው የግዥ ኦፊሰር ወይም የሥራ ሂደት ፈጻሚ ወይም የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
5. ከመጫረቻ ሠነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የደረሰ የመጫረቻ ሰነድ እሽጉ ሳይከፈት ወዲያውኑ ለተጫራቹ ተመላሽ መደረግ አለበት

## 13.12. የጨረታ አከፋፈት

1. ጨረታው የሚከፈተው በጨረታው ጥሪ ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ከሆነ በማሻሻያ ሰነዱ ላይ በተገለፀው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በግልፅ ይሆናል። ጨረታው በጨረታ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን ተጫራቹ ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልፅ መከፈት አለበት። ሆኖም ተጫራቹ በራሱ ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ባይገኝ የጨረታውን መከፈት የማያስተጓጉለው ከመሆኑም በተጨማሪ በጨረታ ሂደቱ ለተላለፉ ውሣኔዎች ተገዥ ይሆናል፣ በጨረታ አከፋፈት ሂደት ላይ መገኘት የሚፈልግ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሐን ድርጅት ወኪል ወይም ሌላ ፍላጎት ያለው ሰው በታዛቢነት መገኘት ይችላል። በተለይም ግዥ ፈጻሚ አካላት ትልልቅ ግዥዎችን በሚፈጽሙበት

ወቅት የጨረታ ሂደቱን ግልጽነት ለማሳወቅ መገናኛ ብዙሀንን መጋበዝ ይችላሉ፡፡ እስከተቻለ ድረስ የውስጥ ኦዲት ተወካይ ጨረታው ሲከፈት መገኘት አለበት።

2. ጨረታውን ከሚከፍቱ የግዥ ጨረታ ኮሚቴ ሰብሳቢው ወይም ከግዥ ኦፊሰሮች ወይም ፈፃሚ ባለሙያዎች አንዱ፣

2.1 ጨረታው በአንድ ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የተጠየቀ ከሆነ ግዥፈጻሚው አካል እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ያቀረበውን የመጫረቻ ሠነድ በመክፈት የተጫራቹን ስም፣ ለጨረታው ያቀረበውን ዋጋ፣ የዋጋ ቅናሽ ካለ መጠንና ሁኔታውን፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም ማናቸውም ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንጻራዊ ደረጃቸውን ለማወቅ ይረዳቸዋል ብሎ የሚያስባቸውን ማንኛውንም ሌሎች መረጃዎች በንባብ ማሰማት አለበት፡፡

2.2 ጨረታው በሁለት ኤንቬሎፕ እንዲቀርብ የሚጠየቀው የጨረታ ሂደቱን የሚገመግሙት ባለሙያዎቹ ብዙ ቢሆኑ በአንድ ሰነድ ብቻ ለመገምገመ አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመንበት ኦሪጅናልና ተጨማሪ ኮፒ መጠየቅ ይቻላል፤

ሀ/ ከላይ በተገለጸው ሁኔታ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን ኦሪጅናልና ኮፒ እንዲያቀርቡ በተጠየቁት መሠረት ኦሪጅናሉና ኮፒው በእለቱ ተከፍቶ በየገጹ ተፈርሞበት ለግምገማ ሥራ የሚያገለግል ሲሆን ገዥ የሚሆነው ግን ኦሪጅናሉ ይሆናል። ኦሪጅናልና ኮፒ እንዲቀርብ መጠየቁ ከላይ ለተገለጸው ዓላማና ጠቀሜታ እንጂ ኮፒ አለማቅረብ እንደ ጨረታ መመዘኛ ለመጠቀም አይደለም። ለማንኛውም ጨረታ የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሠነዶች ለየብቻቸው ታሽገው እንዲቀርቡ የተጠየቀ ከሆነ በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ስርዓት ወቅት የቴክኒክ ዶክመንቱን የያዘው ኤንቬሎፕ ኦሪጅናሉና ኮፒው እንዲከፈት ተደርጎ የተጫራቹን ማንነት ጨምሮ በወቅቱ ሊገለጹ የሚችሉ ነጥቦች በንባብ በማሰማት ሰነዱ ላይ ገጽ በገጽ በመፈራረም የቴክኒክ ግምገማውን ለሚያከናውነው አካል የገጹን ብዛት በመጥቀስ በሸኝ ደብዳቤ መስጠት አለባቸው፡፡

ለ/ የሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች የዋጋ ኤንቬሎፕ ግን ሳይከፈት አንድ ላይ ታሽጎ በእሽጉ ላይ የጨረታው መለያ እና የዋጋ ኤንቬሎፖች መሆኑ ተገልጾ እና ጨረታውን የከፈቱት የመ/ቤቱ ባልደረቦች ተፈራርመውበት ሁለተኛው ዙር የጨረታ መክፈቻ ሥነ-ስርዓት እስከሚካሄድ ድረስ የታሸገው ፖስታ እንዳስፈላጊነቱ በተመረጠው የግዥ ኦፊሰር ወይም በግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤቱ ወይም አስተባባሪው እጅ በጥንቃቄ ተይዞ መቆየት ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ስልጣን በተሰጠው አካል ከፀደቀ በኋላ ውጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በደብዳቤ መገለጽ ይኖርበታል፡፡

መ/ የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉ ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡ ተጫራቾቹም አቤቱታ ካላቸው አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ አቤቱታ የሚቀርብበት እና የሚመረመርበት ስርዓት በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 39 እስከ 41 የተገለፁትን ሁኔታዎች ተከትሎ ይሆናል፡፡

ተመዝጋቢዎች በሚወዳደሩበት ጊዜ የሚያስይዙት የጨረታ ማስከበሪያ አጠቃላይ የተወዳደሩበትን ዋጋ ማለትም ቫትን ጨምሮ መሆን አለበት።

2. የጨረ ው ማስከበሪያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከተፈቀደላቸው የ ወቁ ባንኮች የሚሰጥ ንደተጫራቹ ምርጫ / ሲ.ፒ.ኦ/ C.P.O /ወይንም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስት ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሆኖ የጠቅላላ ግዥውን ግምታዊ ዋጋ መሠረት በማድረግ ከ0.5% /ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ/ ያላነሰና ከ2% /ከሁለት በመቶ/ ያልበለጠ የጨረታ ማስከበሪያ የገንዘብ መጠን ተወስኖ በጨረታ ጥሪው እና ሰነዱ ውስጥ መገለፅ ይኖርበታል:: በዚህ መሠረት የሚወሰነው የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከብር 500,000.00 የበለጠ መሆን የለበትም። ይህም የጨረታ ማስከበሪያ በገንዘብ ያዥ መያዝ ይኖርበታል።

3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ እንዲያስይዙ በሚጠየቁበት ጊዜ የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክና በዋጋ በሚል በተለያዩ ፖስታዎች እንዲያቀርቡ የተጠየቀ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያውን ሲ.ፒ.ኦ (C.P.O ) ኦሪጅናሉን ወይም በጥሬ ገንዘብ የተያዘ ከሆነ የደረሰኙን ፎቶ ኮፒ ከፋይናንስ ወይም ዋጋ ማቅረቢያ ፖስታው ውስጥ አስገብተው እንዲያቀርቡ አስቀድሞ ሊገለጽላቸው ይገባል።ሌሎች የብቃት ማረጋገጫዎች ግን ከቴክኒክ ፖስታው ጋር ወይንም በሌላ ፖስታ ሊቀርቡ ይችላሉ።

4. ለግንባታ ዘርፍ ሥራ የሚያዘው የጨረታ ማስከበሪያ አቅራቢው ሞልቶ ባቀረበው ጠቅላላ ዋጋ ሳይሆን የቀረበው ዋጋ የሂሳብ ስሌት (አርቲሜቲክ ቼክ) ከተደረገ በኋላ የሚገኘውን ጠቅላላ ዋጋ መሠረት በማድረግ ሲሆን በዚህ መሰረት 95 % እና በላይ ያቀረቡ ተወዳዳሪዎች የማነስ ልዩነቱን ቢበዛ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲያስይዙ በማድረግ ማወዳደር የሚቻል ሲሆን ተጠይቆ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነና ከ95% ያነሰ የጨረታ ማስከበሪያ ያቀረበ ከጨረታ ውድድር ውጭ ይደረጋል።

5. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ የጨረታው ዋጋ ፀንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 20 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል::

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለጸው መሠረት ግዥ ፈጻሚ አካላት የጨረታ ማስከበሪያ መጠን ለመወሰን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል::

   ሀ. የሚገዛው ግዥ የዋጋ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭ መሆን፣

   ለ. በጨረታው የሚሳተፉ በቂ ተወዳዳሪዎች መኖር፣

   ሐ. ተጫራቾች እንዲያቀርቡ የሚጠየቀው ዋስትና በጨረታው እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደማይሆን፣

   መ. አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚገፋፋ፣

   ሠ. አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ተጫራች ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ዋስትናው በግዥ ፈጻሚው አካል ላይ የደረሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚመጥን መሆኑን፣

7. የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ባንኮች የተሠጠ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በአገር ውስጥ ባንኮች ማረጋገጫ ያገኘና በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆን ይኖርበታል::

3.2. ግዥ ፈጻሚው አካል ካስቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪነት የሚቀርብ እሴት ተጨማሪ ፋይዳ ማስገኘት አለማስገኘቱን ወይም ተጨማሪው እሴት ለመ/ቤቱ የሚሠጠውን ጥቅም ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት፣

3.3. የሚገዛው ዕቃ/አገልግሎት ደረጃ ያልወጣለትና ተጨማሪ ፋይዳ ከመፍጠር አንፃር ስፔሲፊኬሽኑን በተለያየ ደረጃ ሊያሟሉ የሚችሉ ተቀራራቢ ዕቃዎች መኖር አለመኖራቸውን፣

3.4. ዕቃው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሆኖ የአቅርቦቱ ምንጭ በመለያየቱ ምክንያት የተለያየ የመጠቀሚያ፣ የመጠበቂያና የመያዣ እንዲሁም የማስወገጃ ወጪ የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን፣

4. ግዥ ፈጻሚው አካል ተጫራቾች ያቀረቡትን ሠነድ በንዑስ አንቀፅ 3 በተገለፁት መስፈርቶች መሰረት በመገምገም አሸናፊ የሚሆነው ተጫራች ከተለየ በኋላ የአሸናፊው ተጫራች ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ በድሕረ ግምገማ መረጋገጥ አለበት ብሎ ሲያምን ይህንኑና ለድሕረ ግምገማ ዓላማ የሚጠቀምበትን መስፈርት በቅድሚያ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመልከት ይኖርበታል።

5. በንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ለማወዳደሪያነት የሚመረጡት መስፈርቶች ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ለመወሰን አስተዋፅኦ የሚኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ እና የግዥውን ጠቀሜታ ለመወሰን ባላቸው አስተዋፅኦ ደረጃ መሰረት አንፃራዊ ክብደት እንዲሰጣቸው መደረግ ይኖርበታል።

6. ግዥ ፈጻሚ አካላት ለሚገዙት ዕቃ የቴክኒክ መመዘኛ ያስፈልጋል ብለው ሲያምኑ ለቴክኒክና ለዋጋ የሚሰጠውን የነጥብ ድርሻ አስቀድመው በጨረታ ሰነዱ ላይ ማካተት አለባቸው፣

7. ተጫራቾችን ከጨረታ ውጭ ሊያደርጉ የሚችሉ ለመገምገሚያ መስፈርት የሚሆኑ መሠረታዊ ነጥቦችን /Rejection Criteria/ በጨረታ ሰነዱ ላይ በግልፅ ተካተው ተጫራቾች እንዲያውቋቸው መደረግ አለበት። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ተጫራቾችን መሰረታዊ ነገሮችን አላሟሉም በሚል ከጨረታ ውጭ ማድረግ አይፈቀድም።

## 13.15. ጨረታን መገምገምና ማወዳደር

### 1. የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ

1.1. አቅራቢዎች በመንግሥት ግዥ ተሳታፊ ሲሆኑ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልተው መገኘታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ሀ/ ወቅታዊ የታደሰ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን፣

ለ/ የሚጠበቅባቸውን የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን፣

ሐ/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው መሆኑን፣

መ/ ግዥው ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ሲሆን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13.3.2 ንዑስ አንቀጽ 1.6 እና1.7 መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረባቸውን፣

1.2. ግዥ ፈጻሚው አካል ጨረታውን የተሟላ ነው ብሎ ሊቀበል የሚችለው በተጫራቹ የቀረበው መጫረቻ ሠነድ በመክፈቻ ስነ ስርዓቱ ወቅት የተከፈተ እና በጨረ ሰነዱ ላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ነጥቦች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

1.3. የቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ ግምገማውን ለማከናወን እና ለማወዳደር የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ግዥ ፈጻሚ አካላት አቅራቢዎች ባቀረቡት የመጫረቻ ሰነድ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡት ሊጠይቅ ይችላል፣ ሆኖም የዋጋ ለውጥን ወይም ያልተሟላ ጨረታን እንዲያሟላ ማድረግን ጨምሮ መሠረታዊ ነገሮች ላይ ለውጥ በሚያስከትሉ ጉዳዮች ማብራሪያ መጠየቅ፣ ሃሣብ ማቅረብ ወይም መቀበል አይቻልም፡፡

1.4. ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "1.3" የተመለከተው ቢኖርም የሥራ ሂደቱ በምርመራው ወቅት የተገኙ የሂሣብ ስህተቶችን ማረም ይችላል፡፡ እንደዚህ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች መ/ቤቱ በአፋጣኝ ለአቅራቢው ማሣወቅ አለበት፡፡ ተጫራቹ በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ ከጨረታው እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

1.5. በተጫራቹ የቀረበው የመጫረቻ ሠነድ ሊሟሉ የሚገባቸውንና ግዥ ፈጻሚው አካል ያስቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ወይም ቅድመ ሁኔታዎች አለማሟላታቸው ከተረጋገጠ ወደ ዝርዝር ግምገማ እንዲያልፉ አይደረግም፡፡

1.6. በጨረታ ሰነዱ ከተዘረዘሩት ባህሪዎች፣ የውል ቃሎች፣ ሁኔታዎች እና ሌሎችም ተፈላጊ ነጥቦች ጋር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖረውም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እና ልዩነት እስከሌለው ድረስ ወይም የጨረታውን ቁም ነገር ሣይለውጥ ሊታረም የሚችል ጥቃቅን ስህተት ወይም ግድፈት ቢኖረውም መ/ቤቱ ጨረታውን እንደተሟላ አድርጐ ሊቀበል ይችላል። ሆኖም ማናቸውም ልዩነት እስከተቻለ ድረስ በገንዘብ ተገልጾ በጨረታው ግምገማ እና ውድድር ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት፡፡

1.7. ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ከዚህ በ ች የተዘረዘሩትን የማያሟሉ ተጫራቾችን ወደ ዝርዝር ግምገማ ማሳለፍ የለበትም፣

ሀ/ በጨረ ው የተወዳደረው አቅራቢ መ/ቤቱ የሚፈልገውን አነስተኛውን የቴክኒክ /የጥራት/ መመዘኛ እና ሌሎች መሰረታዊ መስፈርቶችን ያላሟላ በመሆኑ ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፣

ለ/ በዚህ አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1.4 መሠረት የተደረገውን የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል አቅራቢ ሲሆን፣

ሐ/ ተጫራቹ የተጠየቀውን የጨረ ማስከበሪያ ያላስያዘ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ያልሆነ ከሆነ፣

2. ዝርዝር ግምገማ ማድረግና አሸናፊውን መለየት

1. ግዥ ፈጻሚው አካል አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ በመጀመሪያ ደረጃ ለግምገማ የተቀበላቸውን የመጫረቻ ሰነዶች እና በጨረታ ሰነዱ ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተጠቅሞ ዝርዝር ግምገማ

ያደርጋል፡፡ በጨረታ ሠነዱ ውስጥ ከተገለጸው መስፈርት ውጭ ግምገማ ማድረግ አይፈቀድም፡፡ በአዋጁ በአንቀጽ 13 የተፈቀደው ልዩ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ በጨረታ ሰነዱ በተገለጸው መሠረት መ/ቤቱ አሸናፊውን ተጫራች ለመምረጥ ከሚከተሉት የግምገማ ስርዓቶች በአንዱ መጠቀም ይኖርበታል:-

ሀ/ በአንድ ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የቴክኒክ ግምገማ መመዘኛዎችን ወይም የተጠየቁ መስፈርቶችን ማሟላቱ የተረጋገጠ እና አነስተኛ ዋጋ ያቀረበን ተጫራች፣ ወይም

ለ/ በሁለት ኤንቬሎፕ የቀረበን ጨረታ የግዥውን የጠቀሜታ እሴት የሚወስኑ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ በቴክኒክ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ያሟላና በፋይናንስ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች በመምረጥ ይሆናል፡፡

2. ዝርዝር ግምገማ በሚደረግበት ወቅት ተጫራቾች የሰጡት በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የዋጋ ቅናሽ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

3. እንደ አስፈላጊነቱ የተመረጠው ተጫራች ህጋዊነት፣ የፋይናንስ ና የቴክኒክ አቋም በመጫረቻ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው መሰረት ብቃት ያለው መሆኑ በድሕረ ግምገማ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

4. ግዥው በዓለም አቀፍ የጨረ ዘዴ የሚፈፀም ሆኖ ለግምገ ማ ዓላማ ሲባል በተለየ ሁኔታ እንዲቀርብ በጨረታ ሠነዱ ካልተገለጸ በስተቀር በተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋና የጨረታ ግምገማው ክስን ማካተት ይኖርበ ል፡፡

5. በዚህ ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት በሚደረግ ግምገማ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ተጫራቾች እኩል ነጥብ ቢያመጡ በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለሐገር ውስጥ ምርት ወይንም አገልግሎት ግዥ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

6. ከላይ በንዑስ 1. ("ሀ" እና "ለ") ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል ነጥብ ያመጡ ወይንም እኩል ተመራጭ የሆኑ ተጫራቾች በሚኖሩበት ጊዜ አሸናፊውን ለመለየት ፣

ሀ/ እኩል የሚወጡ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸው መስፈርቶች ቁጥር ከሦስት ያልበለጠ እና በአኃዝ ሊገለፅ የሚችል ሆኖ መስፈርቶቹ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተለይ በጨረታ ዝርዝር መግለጫው ላይ አስቀድሞ መገለፅ ይኖርባቸዋል፣

ለ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች እኩል መሆናቸው ሲረጋገጥ ይኸው ተገልፆላቸው መጀመሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፁት መስፈርቶች መሠረት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፣

ሐ/ እኩል የወጡት ተጫራቾች ያቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሀሣብ ተገምግሞ የተሻለ ሐሳብ ያቀረበው ተጫራች የጨረታው አሸናፊ ተደርጎ ይመረጣል፣

መ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ ፊደል "ሐ" የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ እኩል የወጡት ተጫራቾች የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ ባለማቅረባቸው ወይም ባቀረቡት የመጨረሻ የመወዳደሪያ ሐሳብ መሰረት በተደረገ ግምገማ በድጋሚ እኩል ቢሆኑ እስከተቻለ ድረስ እኩል የሆኑት ተጫራቾች

በተገኙበት አሸናፊው ተጫራች በእጣ እንዲለይ ይደረጋል:: ሆኖም በመጨረሻው ውድድር እኩል ከወጡት ተጫራቾች መካከል ሴቶች ካሉ ቅድሚያ ለሴቶች ይሰጣል።

7. ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረ ውን አሸናፊ በሚመርጥበት ጊዜ መለኪያው ተለይቶ የሚ ወቅ ስከሆነ ድረስ በ ያንዳንዱ የዕቃ ወይም አገልግሎት መለኪያ የተሰጠውን የነጠላ ዋጋ ወይም ሌሎች የውል ቃሎች ና ሁኔ ዎችን ሳይለውጥ የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ብዛት ወይም መጠን እስከ 20% (ሃያ በመቶ) ድረስ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል::
8. ግዥ ፈጻሚ አካላት የማናቸውም ጨረታ ግምገማ በተጫራቾች የተሰጠው የጨረታው ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻ ቀን ከማለፉ በፊት ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ለተጫራቾች መግለጽ አለባቸው:: ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ግምገማውን በጊዜው ማጠናቀቅ ካልቻሉ ተጫራቾች ዋጋው ፀንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ እንዲያሻሽሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14.7. ንዑስ አንቀጽ 4 እስከ 7 መሠረት መጠየቅ ይገባቸዋል::
9. በጨረ ው አሸናፊ የቀረበው ዋጋ ጨረ ው ከመውጣቱ በፊት ግዥ ፈጻሚው አካል ከገመተው ውጪ በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ከሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል ወጪው ከ ሰበው በላይ የሆነበትን ምክንያት ማጣራት ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ያስፈልግ እንደሆነ መመርመር አለበት::
10. ግዥ ፈፃሚ አካላት በ 6ቱ የግዥ ዘዴዎች አሸናፊ ለመለየት ጨረታ በሚገመግሙበት ወቅት መነሻ የሚሆን የገበያ ዋጋ መረጃ ከንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ወይም ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ወይም ከአገር ውስጥ አምራች ድርጅት ወይም በውጭ አገር ከሚገኝ ሕጋዊ ተቋም ወይም የልማት ድርጅቶች ማግኘት ይኖርባቸዋል።
11. ግዥ ፈጻሚ አካላት የጨረታ ሰነድ በሚገመግሙበት ጊዜ ጨረታው በግዥ ገምጋሚ ኮሚቴው የማይታይ ከሆነ ሁለትና ከዚያ በታች የግዥ ኦፊሰሮች ባሉባቸው መ/ቤቶች የግዥውን አፈፃፀም በድምፅ ለመወሰን እንዲያስችል ከሥራ ሂደቱ ከሚገኙ ኦፊሰሮች በመጨመር ቢያንስ 3 /ሶስት/ ሆነው የጨረታ ሳጥን ከማዘጋጀት እስከ አሸናፊውን መለየት ያለውን ተግባር ለማከናወን የሥራ ሂደቱ ባለቤት ወይም አስተባባሪ መድቦ ማሰረት ይኖርበታል:: በሙሉ ቁጥር የግዥ ዉሳኔ ለሚሰጡ የግዥ ኦፊሰሮች ቡድን እኩል ድምፅ ቢከሰት ለሥራ ሂደቱ ባለቤት ወይም አስተባባሪ ቀርቦ እርሱ የደገፈው ሀሳብ አሸናፊ ይሆናል።
12. የግዥ ኦፊሰሮች ቡድን በማንኛውም የጨረታ ወቅት በዙር የራሳቸውን ሰብሳቢና ፀሐፊ በጋራ እየመረጡ የጨረታ ሂደቱን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።
13. ሙያ የሚጠይቁ ወይም ቴክኒካል በሆኑ ግዥዎች የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገምገም እንዲሁም ከጨረታ በኋላ አቅራቢው ዕቃውን ገቢ በሚያደርግበት ጊዜ በየመስሪያ ቤቱ ያሉ የሚመለከታቸው የቴክኒክ ባለሙያች በደብዳቤ ሙያዊ እገዛ እንዲያደርጉ ሲጠየቁ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸዉ:: ለሚሰጡትም ሙያዊ እገዛ ድጋፉን ለጠየቃቸው አካል በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል:: በመ/ቤቱ ውስጥ የቴክኒክ ባለሙያዎች የሌሉ ከሆነ

በግዥ ወይም ከሌሎች መ/ቤቶች በትብብር ያሉ ባለሙያዎችን ድጋፍ በመጠየቅ በዚሁ አግባብ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

13.16. ልዩ አስተያየት

1. በቀጥታና በፕሮፎርማ ከሚፈጸም ግዥ በስተቀር በማናቸውም ግዥ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 13 መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ መድሐኒትና ሌሎች ዕቃዎች፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ለተደራጁ አካላት፣ በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ለሚከናወኑ የግንባ ዘርፍ እና የምክር አገልግሎት ሥራዎች ልዩ አስተያየት ይደረጋል፡፡
2. በዚህ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፡፡ ይኸውም፡-
   2.1. ለመድሃኒትና ህክምና መሣሪያዎች ግዥ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/
   2.2. ለሌሎች ዕቃዎች ግዥ 15% /አስራ አምስት በመቶ/
   2.3. የግንባታ ሥራ እና ለምክር አገልግሎት 7.5% /ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ/
3. በዚህ ንዑስ አንቀፅ 2 (2.1 እና 2.2) መሰረት የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድሐኒቱን ወይም የህክምና መሳሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ወጭ 35% /ሰላሳ አምስት በመቶ/ እና ከዚህ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት ያለው መሆኑን የሚያስረዳ በታወቀ ኦዲተር የተረጋገጠ መረጃ ከአምራቾች ወይም ከካምፓኒዎች ሲቀርብ ይሆናል፡፡ ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀም "የታከለ ዋጋ" ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጪ አገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጪ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ሲሆን፣ በምርት ላይ የሚከፈሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶችን አይጨምርም።
4. ማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ በንዑስ አንቀጽ 2 (2.3) መሠረት የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲሟሉ ይሆናል።
   4.1. ኩባንያው በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና ዋና መ/ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣
   4.2. ከኩባንያው አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ አብዛኛው ማለትም ከ50% ባላይ በኢትዮጵያውያን የተያዘ ከሆነ፣
   4.3. ከኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል አብዛኛው(50% በላይ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣
   4.4. ከኩባንያው ቋሚ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ 50% ኢትዮጵያዊያን ከሆኑ፣
5. ግዥ ፈጻሚው አካል ተጫራቾች ያቀረቡትን የጨረታ ሰነድ ከመረመረ በኋላ ተፈላጊውን የሚያሟሉ ሆነው የተገኙትን ተጫራቾች በሁለት ምድብ ይከፍላል። በዚህም መሠረት ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው የአገር ውስጥ ተጫራቾች በአንደኛው ምድብ ይመደባሉ፤ ሌሎች ተጫራቾች

በሁለተኛው ምድብ ይመደባሉ፡፡ የጨረታው ግምገማ በሚደረግበት ጊዜም በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የሚገኙ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ የተወሰነው የልዩ አስተያየት መቶኛ እንዲደመርበት ይደረጋል።

6. የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማትን ለማበረታታት ልዩ አስተያየት ይደረጋል። ልዩ አስተያየቱም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 በተገለፀው አግባብ ይፈፀማል፡፡

7. ቢሮውና በተዋረድ ያሉ የገ/ኢ/ልማት መምሪያና ጽ/ቤቶች አግባብ ካላቸው የመንግሥት የበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በደሕንነት ወይም በፀጥታ ጉዳዮች ምክንያት ግዢ በተለየ ዘዴ እንዲፈፀም ውሣኔ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ የዚህ የግዢ ጥያቄ፣ የምርመራና የግምገማ ሂደት በግዥ መመሪያው አንቀጽ 33 በተቀመጠው አግባብ ይፈፀማል፡፡

## 13.17. ከጨረታ ውጪ ስለማድረግ

ከሚከተሉት ጥፋቶችና ምክንያቶች ውስጥ አንዱን የፈፀመ ተጫራች መ/ቤቱ ከጨረታ ውጭ ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.1. በአዋጁ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን እና የዚህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣውን መመሪያ ሲጥስ ወይም በጨረታ ሰነዱ የተመለከቱትን መሰረታዊ ጉዳዮች ሣያሟላ ሲቀር፣

1.2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የንግድ ግንኙነቶች ላለማድረግ ክልከላ ከጣለበት አገር የሚመጣ ዕቃና አገልግሎት ከሆነ፣ ወይም፣

1.3. በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውሳኔ ከዚያ አገር ዕቃዎችንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ማስመጣት ወይም ለዚያ ሀገር ሰዎች ወይም ድርጅቶች ማንኛውንም ክፍያ መፈፀም የተከለከለ ከሆነ፣

1.4. ቀደም ሲል በመንግሥት በወጡ ጨረታዎች የገባውን ግዴታ ሣያከብር በመቅረቱ፤ ስልጣን ባለው አካል የታገደ ከሆነ፣

1.5. የተለየ አስተያየትን ለማግኘት ወይም ጨረታውን ለማሸነፍ ለማንኛውም ባለሥልጣን ወይም ሰራተኛ መደለያ መስጠቱ ወይም መደለያ የመስጠት ሃሣብ ማቅረቡ በአሣማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ፣

1.6. ተወዳዳሪው በጨረታው ሰነድ ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈፀሙ ወይም ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር መመሳጠሩ በአሣማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ፣

1.7. ተወዳዳሪው የመጫረቻ ሰነዱን በጨረታ ሳጥኑ ካስገባ በኋላ እራሱን ከጨረታ ለማግለል ከፈለገና ጨረታው ከመዘጋቱ ቀንና ሠዓት በፊት የማግለያ ሃሳቡን በጨረታ ሳጥኑ ውስጥ ካስገባ፣

## 13.18. የጨረታን መወዳደሪያ ሃሣብ ውድቅ ስለማድረግ

1. በአዋጁ አንቀፅ 18 መሠረት ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ጨረታውን ማለትም የዕቃ፣ የምክርና የሌሎች አገልግሎቶች እና የግንባታ ዘርፍ ስራ አቅርቦት መወዳደሪያ ሃሣብን ውድቅ በሚያደርግበት ጊዜ ውድቅ መደረጉን የሚገልፅ ማስታወቂያ ወዲያውኑ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲደርስ መደረግ አለበት፣

ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ከሚከተሉት በአንዱ ወይንም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ጨረ ንና የመወዳደሪያ ሀሳብን የግዥ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ማድረግ ይችላሉ::

1.1. በግዥ አካሔዱ ላይ ውጤቱን ሊያዛባ የሚችል ስህተት መፈፀሙ ከተረጋገጠ፣

1.2. በስራ ዕቅድ መቀየር ምክንያት ወይም የመሥሪያ ቤቱን ፍላጎቱን ለማሟላት ሌላ የተሻለ አማራጭ በመፈጠሩ ምክንያት ግዥውን ማካሔድ ለግዥ ፈጻሚው አካል የተሻለ ቴክኒካል ወይንም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

1.3. የቀረቡት ተጫራቾች በጨረ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የቴክኒክ ወይም የጥራት መስፈርት የማያሟሉ ሲሆን፣

1.4. በጨረ የቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ በላይ ሲሆን ና ግዥ ፈጻሚው አካል ድጋሚ ጨረ በማውጣት የተሻለ ዋጋ የሚገኝ መሆኑን ሲገምት፣

1.5. በጨረ ው አሸናፊ የሆነው ተጫራች የሰጠው ዋጋ የግዥ ፈፃሚ አካል ለግዥው ከያዘው በጀት በላይ ሲሆን እስከ 20% ቀንሶ የመግዛት ሙብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩነቱን ከሌላ ምንጭ ማሟላት የማይችል ሲሆን፣

1.6. ዕጩ ተወዳዳሪዎች የግዥ አካሔዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፣

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረ ንና የመወዳደሪያ ሀሳብን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ሲሰርዙ ምክንያቱን የሚገልፅ ማስ ወቂያ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ወዲያውኑ ንዲደርስ ማድረግ አለባቸው። ሆኖም የምክንያቶቹን አግባብነት ንዲያስረዱ አይገደዱም።

3. ጨረ ውን ውድቅ የማድረጉ ውሣኔ የተሰጠው ጨረ ው ከመከፈቱ በፊት ከሆነ የመጫረቻ ሰነዶቹ እንደታሸጉ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች መመለስ አለባቸው::

4. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ጨረ ንና የመወዳደሪያ ሀሳብን ውድቅ በማድረጋቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ተጠያቂነት አይኖርባቸውም::

## 13.19. ጨረታን ማፅደቅና አሸናፊን ማሳወቅ

1. በመንግስት መ/ቤቶች የጨረታ ግምገማውን የሚያከናውነው አካል ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ጨረታ ለመገምገም የተቋቋመው ኮሚቴ በተጫራቾች የተሠጠው የጨረታ ዋጋ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ግምገማውን በማጠናቀቅ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ግዥውን ለማፅደቅ ስልጣን ለተሠጠ ው አካል ማቅረብ አለበት::

2. በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥውን እንዲያፀድቅ ሥልጣን የተሰጠው አካል ግዥው የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ሥርዓትን የተከተለ እና የጨረታ ግምገማው በጨረታ ሠነዱ በተገለጸው መሥፈርት መሠረት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል:-

ሀ/ የግምገማ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ በመቀበል ቀጣይ አፈጻጸሞች እንዲከናወኑ መፍቀድ፣

ለ/ ሪፖርቱን ባለመቀበል ግምገማው እንደገና እንዲከናወን ማድረግ፣

3. ግዥውን የሚያፀድቀው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው የግምገማ ሪፖርት ላይ ግምገማውን የሰራው ቡድን ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. በንዑስ አንቀጽ 2 ለ/ ላይ በተገለጸው መሰረት ግዥውን የሚያፀድቀው አካል የቀረበውን የግምገማ የውሳኔ ሃሳብ ያልተቀበለ ከሆነ ምክንያቱን በመግለጽ ከዚህ በፊት ግምገማውን ላከናወነው አካል እንዲመለስ የሚያደርግ ሲሆን ገምጋሚውም ከአፅዳቂው አካል በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ግምገማውን እንደገና አከናውኖ የተስተካከለውን ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተው ቢኖርም ገምጋሚ ባለሙያዎች ወይም ማንኛውም የጨረታ ገምጋሚ የኮሚቴ አባል ግዥውን ከሚያፀድቀው አካል በተሰጠው አቅጣጫ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ የማይስማማ ከሆነ በግምገማ ሪፖርቱ ላይ ያልተስማማበት ሀሣብ ተገልፆ የግዥ አፅዳቂ አካሉ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

6. ግዥ ፈጻሚ አካላት የጨረታው ውጤት በዚህ መመሪያ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት በፀደቀ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራችና በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ሌሎች ተጫራቾች በእኩል ጊዜ በጽሑፍ መግለጽ አለባቸው። ለተሸነፉ ተጫራቾች የሚገለፀው የተሸነፉበትን ምክንያት እና አሸናፊ የሆነውን ተጫራች ማንነት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

7. በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች የሚላከው የአሸናፊነት ደብዳቤ በግዥ ፈጻሚው አካል እና በተጫራቹ መካከል እንደውል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። በግዥ ፈጻሚው አካል እና በተጫራቹ መካከል ውል ሊኖር የሚችለው ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በግዥ ፈጻሚው አካልና በተጫራቹ ሲፈረም ብቻ ነው፡፡

8. ተጫራቹ ውል እንዲፈርም የሚላክለት ማስታወቂያ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

ሀ/ ግዥ ፈጻሚው አካል በተጫራቹ የቀረበውን የመጫረቻ ሐሳብ የተቀበለ መሆኑን፣

ለ/ ውሉ የሚፈጸምበትን ጠቅላላ ዋጋ፣

ሐ/ ተጫራቹ ማስያዝ የሚገባውን የውል ማስከበሪያ መጠን እና የማስረከቢያውን የመጨረሻ ቀን፣

9. በጨረታው አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረታ ማስከበሪያውን በመውረስ በቅድሚያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ገምግሞ ካመነበት በውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች አሸናፊ ማድረግ ይችላል፣ በጨረታው ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ውል

ለመፈራረም ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በመውረስ አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል።

10. የመንግስት መ/ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ ተወዳዳሪዎች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተመላሽ ማድረግ አለበት::

ሀ/ ከአሸናፊ ተጫራቹ ጋር ውል ፈርሞ ተጫራቹ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ያቀረበ ከሆነ፣

ለ/ የተሸናፊ ተጫራች ወይም የጨረታ ማስከበሪያውን የመጠቀሚያ ጊዜ ለማራዘም ፈቃደኛ ያልሆነ ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያ ፀንቶ መቆያ ጊዜ ያበቃ ከሆነ፣

13.20. ውል ማስከበሪያ

1. ለማንኛውም የግዥ ውል ከዋጋ ማቅረቢያ /ፕሮፎርማ/ እና ከኪራይ ግዥ በስተቀር ግዥ ፈጻሚ አካላት የውል ማስከበሪያ መቀበል አለባቸው። ከአሸናፊው የሚቀርበው የዉል ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ ውሉ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን በኋላ ቢያንስ ለተጨማሪ 30 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል::

2. የጨረታው አሸናፊ በጨረታ ማሸነፉ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ከ5 የሥራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጨረታ አሸናፊው የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ባላቸው የዋስትና ዓይነቶች የውሉን ዋጋ 10% /አስር በመቶ/ እንዲሁም ለተሽከርካሪ የኮንትራት ጥገና አገልግሎት 3% /ሶስት በመቶ/ በማስያዝ ውል መፈፀም አለበት። ይህም የውል ማስከበሪያ በገንዘብ ያዥ መያዝ ይኖርበታል።

3. በግዥው አፈፃፀም ላይ አቤቱታ ቀርቦ በመጣራት ላይ ካልሆነ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ከ5 የሥራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተገቢውን የውል ማስከበሪያ ያላስያዘና ውል ያልፈፀመ እንደሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረታ ማስከበሪያ የመውረስ መብት ይኖረዋል፣

በዚህ ንዑስ አንቀፅ ተራ ቁጥር 1 በተመለከተው መሠረት፣

3.1. የሚቀርብ የውል ማስከበሪያ ዋስትና በሲ.ፒ.ኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም ጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል።

3.2. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 3.1 እንደተጠበቀ ሆኖ ለኮንስትራክሽን አገልግሎትና የመድሀኒትና የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ውል ከታወቀ የመድን ድርጅት የሚቀርብ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የውል ማስከበሪያ ተቀባይነት ይኖረዋል፣

3.3. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 3.1 እንደተጠበቀ ሆኖ የምክር አገልግሎት በመስጠት ላይ የተሰማሩ አቅራቢዎች ለሚሰጡት የምክር አገልግሎት እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት የውል ማስከበሪያ የባለሙያ የካሣ መድህን ይሆናል፣

3.4. የመድን አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም በወጣ ጨረታ አሸናፊ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶች ለግዥ ፈጻሚ አካል ለሚሰጡት የመድን ዋስትና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመጠባበቂያ ያስቀመጡት ገንዘብ ለውል ማስከበሪያ እንዲሆን ከፈለጉና በቂ መጠባበቂያ ያላቸው መሆኑን ከባንኩ ማረጋገጫ ካቀረቡ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

4. አንድ አቅራቢ ከግዥ ፈጻሚው አካል ጋር ውል በፈፀመባቸው ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች እንደውሉ ባይፈፅም ለውል ማስከበሪያ ያስያዘው ዋስትና ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል ፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተው ቢኖርም አቅራቢው ውል ከፈፀመባቸው ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ውስጥ፣

5.1. እንደውሉ ዋጋ ዘጠና አምስት በመቶ ያለምንም ችግር ያከናወነና ያስረከበ ከሆነ፣

5.2. ቀሪው አምስት በመቶ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ማቅረብ ያልተቻለው ከአቅም በላይ መሆኑ በአሳማኝ ሁኔታ ከተረጋገጠ፣

5.3. ያልቀረቡት የውሉን ጠቅላላ ዋጋ አምስት በመቶ ግዥዎች በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የሥራ ዕቅድ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ወይም ችግር የማያስከትሉ መሆናቸው ከታመነበት ለውል ማስከበሪያ ከተያዘው አስር በመቶ ዋስትና ውስጥ ገቢ ላልተደረጉት ግዥዎች ዋጋ ተሰልቶ ተመጣጣኙን ገንዘብ በማስቀረት የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ቀሪው የውል ማስከበሪያ ሊመለስ የሚችል ሲሆን፤ ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው የግዥ ፈፃሚው የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ሲወስን ብቻ ይሆናል፡፡

6. በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የተያዘው የውል ማስከበሪያ አቅራቢው የውል ግዴታውን ሙሉ በሙሉ እንዳጠናቀቀ መመለስ ይኖርበታል፡፡

7. ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተዘረዘሩት ቢኖሩም አቅራቢው አሸናፊነቱ ተገልፆለት ቀርቦ ውል እንዲይዝ ትዕዛዝ ሲደርሰው ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ ማቅረብ ከቻለና የግዥ አፈፃፀም ሂደቱ ለ3ኛ ወገን ግልፅ መሆኑን፣ በቀጣይ በምንም ዓይነት መልኩ የቅሬታ ምንጭ የሚሆኑ ምክንያቶች ያለመኖራቸውን ግዥ ፈጻሚው አካል ካረጋገጠና ከወሰነ የውል ስምምነት በመፈፀም ብቻ የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ግዥውን መፈፀም ይችላል።

## 13.21. ውል መዋዋል

1. ማናቸውም ግዥ ፈጻሚ አካላት የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መዋዋል አለበት:: የሚፈፀመው ውልም ከዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) በስተቀር በየደረጃው ባለ የፍትህ ቢሮ አካል ተመርምሮና ታይቶ ውል እንዲወሰድ መደረግ አለበት።

2. ግዥ ፈጻሚው አካል እና በአቅራቢው መካከል ውል ካልተዋዋሉ በስተቀር በጨረታው አሸናፊ መሆኑ በመገለፁ ብቻ ውል እንደተፈፀመ አይቆጠርም::

3. በአቅራቢው እና በግዥ ፈጻሚው አካል መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች መብትና ግዴታ በግልፅ ማመልከት ያለበት ሲሆን የሚከተሉትን ጉዳዮች በተጨማሪነት ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

3.1. በውሉ የሚቀርበው እቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ስራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች አይነትን፣ ጥራትን፣ ብዛትን፣ የሚቀርብበትን አኳኋን ወይንም የማስረከቢያ ጊዜውን፣የሚከፈለውን አጠቃላይ እና የነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣

3.2. አቅራቢው በመጫረቻ ሠነዱ ላይ ያመለከተው የዋጋ ቅናሽ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን እና አፈጻጸማቸውን በግልጽ ያመላከተ መሆን አለበት፣

3.3. ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን እንደ ትራንስፖርት፣ መድህን፣ ትራንዚት እና የመሳሰሉ ተግባራትን የመከታተል እና የመፈፀም ኃላፊነት የማን እንደሚሆኑ መጠቀስ ያለበት ሲሆን ኃላፊነቶቹም በተሻለ ብቃት ሊፈፅማቸው በሚችል አካል እንዲሰሩ መደረግ ይኖርበታል፣

3.4. የውጭ አገር ተጫራች ከጠቅላላው የውሉ መጠን ውስጥ በውጭ አገር ገንዘብ እና በብር ሊከፈለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ድርሻ ተለይቶ መገለጽ ይኖርበታል፣

3.5. በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት አካሄድ፣

3.6. የውል አካል የሆኑ የግዥ ሰነዶች እና የተፈፃሚነት ቅድመ ወሰን ፣

3.7. ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስከበሪያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፣

3.8. አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደው እርምጃ፣

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 /3.8/ መሰረት የሚወሰደው እርምጃ በሚከተለው መሰረት መሆን ይኖርበታል፤

4.1. አቅራቢው በውሉ መሰረት አጠናቆ ባያቀርብ በውሉ በተመለከተው የገንዘብ መጠን ላይ በየቀኑ 0.1% /ዜሮ ነጥብ አንድ በመቶ/ ወይም 1/1000 /አንድ ሺህኛ/ መቀጫ እንደሚከፍል፣

4.2. በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን ዋጋ 10% /አስር በመቶ/ የሚበልጥ መሆን የለበትም፣

4.3. የውሉ አፈፃፀም መዘግየት በሥራው እንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል የመቀጫው መጠን 10% እስከሚሞላ ድረስ መጠበቅ ሳይገደድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን መሠረዝ እንደሚችል፣ የሚገልፅ አንቀጽ ውሉ እንዲይዝ መደረግ አለበት::

5. ግዥ ፈጻሚው አካል በውል ሰነድ ላይ የሚሰፍሩ ኃላፊነቶችን እና ግዴታዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን በመ/ቤቱ ደረጃ ሊከናወኑ የማይችሉ ግዴታዎችን ተቀብሎ ውል መፈረም የለበትም ::

6. የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ ከ5 የሥራ ቀናት በኋላ ባሉት 5 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል::

7. ጨረ ውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል የጨረታውን ውጤት ለተጫራቾች ከገለፀበት ቀን ጀምሮ 5 የሥራ ቀን ከመሙላቱ በፊት የግዥ ውል መፈረም የለበትም።

## 13.22.የቅድሚያ ክፍያ አሰጣጥ እና ዋስትና አቀራረብ

1. በመንግሥት ግዥ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ለዕቃ ግዥ፣ ለግንባታ፣ ለምክር አገልግሎትና ለሌሎች አገልግሎቶች ግዥ እስከ 30% (ሠላሣ በመቶ) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል። ይህም የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ መጠንም በተጫራቾች መመሪያ ላይ መገለፅ ይኖርበታል።
2. አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ከሚጠይቁት የቅድሚያ ክፍያ ጋር እኩል ዋጋ ያለው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከ ወቀ ባንክ የሚሰጥ ሲ.ፒ.ኦ (C.P.O.) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ይህም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና በገንዘብ ያዥ መያዝ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተው ቢኖርም የአገር ውስጥ የግንባታ ኩባንያዎች እና የመድሐኒትና የህክምና መሣሪያዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች በሁኔታ ላይ የተመሠረተ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ከታወቀ የመድን ድርጅት ሊያቀርቡ ይችላሉ።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለግንባታ ዘርፍ ሥራ በተደረገ ውል መሠረት ለሚፈፀም የቅድሚያ ክፍያ የቀረበው ዋስትና የመድን ድርጅት ሲሆን፣ ውል ሰጪው ግዥ ፈጻሚ አካል ና ውል ተቀባይ የሆነው ሥራ ተቋራጭ የቅድሚያ ክፍያውን አጠቃቀም በሚመለከት የተለየ ውል መዋዋል አለባቸው፣ ውሉም የሚከተሉትን ይይዛል፣
   - 4.1. በውሉ መሠረት ለሥራ ተቋራጩ የሚሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ለዚሁ ዓላማ በሥራ ተቋራጩ ስም በሚከፈት እና በአሰሪው መ/ቤትና ተቋራጩ ጣምራ ፊርማ የሚንቀሳቀስ የተለየ የባንክ ሂሣብ ውስጥ እንደሚቀመጥ፣
   - 4.2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4.1 መሠረት በተከፈተው ሂሣብ ውስጥ የተቀመጠው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ወጪ ሊደረግ የሚችለው የግዥ ፈጻሚው አካል ተወካይ ና በሥራ ተቋራጩ የጣምራ ፊርማ ንደሚሆን፣
   - 4.3. በባንክ ሂሣቡ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ለሥራ ተቋራጩ ክፍያ የሚፈፀመው ቀደም ሲል በወሰደው ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሠራ መሆኑ ሲረጋገጥ ንደሆነ፣
   - 4.4. በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለመንገድ ሥራ አገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 50% እንዲሁም ለሕንጻ ሥራ አገር ውስጥ ተቋራጮች እስከ 30% ለመሣሪያ መግዣ ማዋል የሚችሉ መሆኑን የሚገልጹ አንቀጾችን የሚይዝ መሆን አለበት።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4. (4.2) እና (4.4) በተመለከተው መሠረት መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲረዳ የሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ ክፍያ መልክ ከተሰጣቸው ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ለመሣሪያ መግዣ እንዲያውሉ ሊፈቅድ ይችላል፣
   - 5.1. የሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ በወሰደው ገንዘብ የገዛውን መሣሪያ በውሉ መሠረት ፕሮጀክቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለዕዳ መያዣነት የማያውል እና በማናቸውም መልክ ሦስተኛ ወገን የማያስተላልፍ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካቀረበ፣

5.2. የሥራ ተቋራጩ የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚወስደው ገንዘብ የሚገዛቸውን መሣሪያዎች ዓይነት ለአሠሪው መ/ቤት ተቆጣጣሪ መሐንዲስ አቅርቦ መሣሪያዎቹ ለሥራው አስፈላጊ መሆናቸው ከተረጋገጠ፣

5.3. መሣሪያዎቹ ከፕሮጀክቱ ባለቤት ፈቃድ ውጪ ከፕሮጀክቱ ወደ ሌላ ቦታ የማይንቀሳቀሱ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው።

6. በቅድሚያ ክፍያ መልክ በሚከፈል ገንዘብ ለመንገድ ሥራ እንዲሁም ለሕንጻ ግንባታ የሚገዙት ማሽነሪዎች በዚህ መመሪያ አባሪ 4 ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ከሆኑ ብቻ ነው::

7. ተቋራጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 (4.4) በተመለከተው መሠረት በተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የገዛቸውን መሣሪያዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ ካላጓጓዘ በውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚገባው የሚቀጥለው ክፍያ አይፈፀምለትም::

8. ተቋራጩ የወሰደው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየደረጃው በሚዘጋጁት የክፍያ ምስክር ወረቀቶች መሠረት ሊከፈለው ከሚገባው ሂሣብ ላይ እየተቀነሰ እንዲመለስ መደረግ አለበት::

9. ለአቅራቢው የሚከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ታክስን ማለትም ቫትን የመሳሰሉትን ታክሶች በመቀነስ አይሆንም። ሆኖም በውሉ መሰረት አቅርቦቱ ወይም ግንባታው ወይም አግልግሎቱ እንደተከናወነ መከፈል ያለበት የታክስ መጠን እየተሰላ መቀነስ ይኖርበታል።

# ክፍል አራት

# የዓለም አቀፍ ግዥዎች አፈፃፀም

## 14. ዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ

1. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በአዋጁ አንቀጽ 46 እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15. ላይ በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል::

2. በአዋጁ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱት ሌሎች የግዥ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዓለም አቀፍ ግልፅ የጨረታ ዘዴ ግዥ ሊፈፀም የሚችለው የግዥው መጠን፣

   2.1. ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ከብር 50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን) በላይ፣

   2.2. ለዕቃ ግዥ ከብር 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን) በላይ፣

   2.3. ለምክር አገልግሎት ከብር 2,500,000.00 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሽህ) በላይ፣

   2.4. አገልግሎት ግዥ ከብር 7,000,000.00 (ሰባት ሚሊዮን) በላይ ሲሆን ነው::

   2.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከ"2.1" እስከ "2.4" የተመለከቱት የገንዘብ ጣራዎች ቢኖሩም ግዥ ፈጻሚ አካላት ከተመለከተው የገንዘብ ጣራ በታች በሆነ የገንዘብ መጠን የዓለም አቀፍ ጨረታ ግዥን መፈጸም አስገዳጅ ሆኖ ካገኙት የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የማሳመኛ ነጥቦችን በማስቀመጥ በስራ አመራሩ በማስወሰን እራሱ ተግባራዊ ማድረግ ይችላል።

3. በዓለምአቀፍ ግልጽ ጨረታ በሚፈፀም የዕቃ ግዥ ተሳታፊ የሚሆኑ ተጫራቾች ራሳቸው የዕቃው አምራቾች ካልሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በመሥሪያ ቤቶች ሲጠየቁ ከአምራቹ የተሰጣቸውን ውክልና ማቅረብ አለባቸው::

4. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13 ለብሔራዊ ግልጽ ጨረታ ከተገለጸው ዝርዝር የግዥ አፈጻጸም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

   4.1. የጨረታ ጥሪ ማስታወቂያ እና የጨረታ ሠነዱ የሚዘጋጀው በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሆን አለበት፣

   4.2. የጨረታው ጥሪ በቂ የሥርጭት ሽፋን ያለውና የውጭ ተጫራቾችን ለውድድር ሊጋብዝ በሚችል ጋዜጣ ላይ መውጣት አለበት፣

   4.3. ተጫራቾች ተገቢ የመጫረቻ ሠነድ ማዘጋጀት እንዲችሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14.9. በንዑስ አንቀጽ 1 (1.1፣ 1.2፣ 1.3) ላይ በተገለጸው መሠረት በቂ ጊዜ መሠጠት አለበት፣

   4.4. የሚዘጋጀው የፍላጎት መግለጫ የአገር ውስጥ ደረጃን ያሟላና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፣

   4.5. የውጭ አገር ተጫራቾች የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋና የጨረታ ማስከበሪያ በቀላሉ ሊመነዘር በሚችልና በአለም አቀፍ ንግድ በሚሠራበት የገንዘብ ዓይነት መሆን እንደሚገባው፣

   4.6. የግዥ ፍላጎቱን ለማሟላት አሸናፊው የውጭ አገር ተጫራች ከአገር ውስጥ የሚጠቀመው ግብዓት በሚኖርበት ጊዜ ከአጠቃላይ የውሉ ክፍያ በብር ሊከፈል የሚገባው መጠን ለይቶ በዋጋ ማቅረቢያው ሠንጠረዥ ላይ ማመልከት ይኖርበታል::

   4.7. በአለም አቀፍ ግዥ የሚፈፀሙ ውሎች አዋጁን እና የአፈፃፀም ድንጋጌዎችን እስካልተቃረኑ ድረስ አለም አቀፍ ንግድ የሚሰራባቸውን የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ተመርኩዘው መፈፀም አለባቸው፡፡

   4.8. በውሉ በተለዬ ምክንያት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በውል አፈፃፀም ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በኢትዮጵያ ሕግ የሚዳኙ ስለመሆናቸው፣

## 15. ሌሎች ዓለም አቀፍ ግዥዎች

1. በአዋጁ አንቀጽ 46 መሠረት የውጭ ኩባንያዎች ካልተሳተፉበት በቂና ውጤታማ ውድድር ሊኖር አይችልም ተብሎ ሲታመን በአዋጁና በዚህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ለብሔራዊና ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተገለጹት ሌሎች አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ግዥ ፈጻሚ አካላት የሁለት ደረጃን፣ የመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያን፣ ውስን ጨረታና የቀጥታ ግዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም ዓቀፍ ግዥ መፈጸም ይችላሉ::

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በተገለፀው መሰረት ከአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች አለም አቀፍ የግዥ ዘዴዎች ለመጠቀም ለየግዥው ዘዴ የተመለከተውን ሁኔታ በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 ከ2.1 እስከ 2.4 መሠረት የተፈቀደውን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

# የሌሎች የግዥ ዘዴዎች አፈፃፀም

## 16. የውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም

የአዋጁ አንቀጽ 36 እና 37 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤

1. በውስን ጨረታ የሚፈጸም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 እና 14 ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ጨረታ የተፈቀደውን ዝርዝር የአፈጻጸም ሥርዓት ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል::
2. በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፤

2.1 የጨረታ ጥሪው በቀጥታ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች በአድራሻቸው የሚላክ ወይንም በእጅ የሚሰጣቸው ሆኖ

ሀ/ ዕቃው፣ የግንባ ዘርፍ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ ወይም በእጅ መሰጠት ይኖርበታል::

ለ/ በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካ ቢሆንም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3.1 በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ገደብ ውስጥ ከሆነ ተጫራቾች አድልዎ በሌለበት ሁኔታ ካሁን በፊት ያላቸውን አፈጻጸም መሠረት በማድረግ በአቅራቢዎች ዝርዝር ከተመዘገቡት ውስጥ መመረጥ አለባቸው። በመሆኑም ጥሪ የሚደረግላቸው እጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ውጤታማ የሆነ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆን አለበት።

ሐ/ ተሣታፊ እንዲሆኑ ጥሪ የሚደረግላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚመረጡት በወቅቱ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸውንና የሚፈለግባቸውን የመንግሥት ግብር የከፈሉ ሆነው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከተሰጣቸው፣ ከአገልግሎት አሰጣጥና ከዕቃ አቅርቦት ተሞክሯቸው መልካም ዝና ካላቸው መካከል ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ ይኖርባቸዋል::

መ/ ግዥው በሚካሔድበት አካባቢ ውስን አቅራቢዎች ብቻ መኖራቸው ከተረጋገጠ በተለይ ከክልሉ ከተማና ከዞን ከተማ ውጪ ያሉ የክልል ወረዳዎች ቢያንስ 3 እና ከዚያ በላይ አቅራቢዎችን ማሳተፍ አስፈላጊ ነው።

2.2. ግዥ ፈጻሚው አካል ለተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በዕጩ ተወዳዳሪዎች ክፍያ መክፈል አያስፈልግም ብሎ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን አመች በሆነው መንገድ አያይዞ ሊልክ ይችላል ።

2.3. ግዥ ፈጻሚው አካል በውስን ጨረታ የተጋበዙ ተጫራቾችን ማንነት ለሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሳወቅ የለበትም::

2.4. በውስን ጨረታ የሚሳተፉ ተወዳዳሪዎች ተገቢውን የጨረታ ማስከበሪያና አሸናፊ ከሆኑም የውል ማስከበሪያ ማስያዝ አለባቸው።

2.5. በውስን ጨረ የተጋበዙት ተጫራቾች በሙሉ ከጨረታ መቆያ ጊዜ ገደቡ በፊት የመጫረቻ ሠነዳቸውን ካቀረቡ የጨረታ መክፈቻ የጊዜ ገደቡ ስከሚጠናቀቅ መጠበቅ ሳያስፈልግ ግዥ ፈጻሚው አካል ጨረታው እንዲከፈት በመወሰን የመክፈቻ ጊዜውን ለሁሉም ተጫራቾች በማሳወቅ እና እንዲገኙ በመጋበዝ ጨረ ው ንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀፅ 36 መሰረት በውስን ጨረታ የግዢ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው ከዚህ በታች ከ3.1 እስከ 3.3 ከተጠቀሱት ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል ቢያንስ አንዱን ሲያሟላ ብቻ ይሆናል።

3.1. ግልጽ ጨረታ በማውጣት በርካታ የጨረታ ሠነዶችን ለመመርመር እና ለመገምገም የሚጠይቀው ከፍተኛ ወጪና ጊዜ ዕቃው፣ የግንባታ ሥራው ወይም አገልግሎቱ ከሚያወጣው አነስተኛ ዋጋ ጋር የማይመጣጠን እና ጠቅላላ ዋጋው ከሚከተለው የማይበልጥ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::

ሀ/ ለግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ ከብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሽህ ብር)

ለ/ ለዕቃ ግዥ ከብር 600,000.00 ( ስድስት መቶ ሽህ ብር )

ሐ/ ለምክር አገልግሎት ግዥ ከብር 200,000.00 ( ሁለት መቶ ሽህ ብር)

መ/ ለአገልግሎት ግዥ ከብር 300,000.00 ( ሦስት መቶ ሽህ ብር)

3.2. ዕቃው፣ አገልግሎቱ ወይም የግንባታው ዘርፍ ሥራው በባህሪይው ከፍተኛ ደረጃ ውስብስብ ወይም የተለየ በመሆኑ ምክንያት ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን ነው፡፡

3.3. ግዥውን ለመፈጸም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በጨረታው የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ ሲሆን፣

4. በአዋጁ አንቀጽ 36 እና 37 በተገለጸው መሠረት ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም የሚከተሉት ሁኔታዎች በቅደም ተከተል መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

4.1. ግዥ ፈጻሚው አካል የጨረታ ጥሪውን፣ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ መጠን እና አይነት እንዲሁም ሌላ ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመሳተፍ እንዳይችሉ የሚገድብ ሁኔታ በአሰራሩ ወይም በጨረታ ማስታወቂያው እና ሰነዱ ውስጥ አለመኖሩን ማረጋገጥ፣

4.2 ግዥ ፈጻሚው አካል በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ ለግዥው ቢጋበዙ ፈቃደኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲታወቅ፣

4.3 እስከተቻለ ድረስ በመስኩ የተሰማሩት አቅራቢዎች በግልፅ ጨረታ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ያልሆኑበትን ምክንያት በማጣራት ምክንያታቸው ሕጋዊ እና የግዥ ፈጻሚውን አካል ጥቅም ለመጉዳት ያለመ አለመሆኑን ማረጋገጥ ሲቻል፣

5. ግዥ ፈፃሚው አካል በአዋጁ አንቀጽ 37 (3) መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ ቁጥራቸው ውስን የሆኑትን ተጫራቾች በጨረታው ውድድር እንዳይሳተፉ ያደርጋል ብሎ ሲያምን የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ሳያስፈልግ ተጫራቾች በዚህ መመሪያ አባሪ 12 የተመለከተውን የስምምነት ማረጋገጫ ፎርመው ከመጫረቻ ሠነዳቸው ጋር እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል::
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በውስን ጨረታ የሚፈፀም ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 በተመለከተው ሁኔታ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተዘረጋውን ሌሎች የግዥ ሥርዓት ተከትሎ ይፈፀማል።
7. በውስን ጨረታ የሚፈጸም ምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 የተገለጹትን ተጨማሪ አሰራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

## 17. በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀም ግዥ

1. የአዋጁ አንቀጽ 38 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈጻሚ አካላት አስቀድመው በማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም አለባቸው:: ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይንም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው በአባሪ ቁጥር 9 በተመለከተው ዝርዝርና የገንዘብ ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መፈፀም ይችላሉ፡፡
2. በፕሮፎርማ ግዥ ለመፈጸም ሲታሰብ በቅድሚያ ለስራ ሂደት አስተባባሪው ቀርቦ አሳማኝ መሆኑ ተረጋግጦ ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡ ይህም የዋጋ ማቅረቢያ የሚሰበሰበው ለተለያዩ አቅራቢዎች እድል በሚሰጥ አግባብ መሆን ስላለበት የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በተደጋጋሚ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ መሰብሰብና መግዛት የለበትም።
3. ግዥ ፈጻሚው አካል በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚመረጡት በአቅራቢዎች ዝርዝር ከተመዘገቡት መካከል እስከተቻለ ድረስ ቢያንስ ሦስት አቅራቢዎችን ማወዳደር አለበት። ውድድሩንም ፍትሐዊ ለማድረግ፣
   3.1. ግዥ ፈጻሚው አካል በአቅራቢዎች መካከል ልዩነትና አድልዎ በሌለበት ሁኔታ ግዥ መፈፀም ይቻል ዘንድ ህጋዊ የሆኑ አቅራቢዎችን በዙር የመወዳደር ዕድል ማግኘታቸውንና አንድን ወይንም የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ በተደጋጋሚ ለውድድር መጋበዝ አለመቻሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
   3.2. ግዥ ፈጻሚው አካል በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ በተለይ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር መከተል እና በየጊዜው ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡
4. ያንዳንዱ አቅራቢ ንዲያቀርብ የሚፈቀድለት አንድ የመወዳደሪያ ዋጋ ብቻ ሲሆን፣ ያቀረበውን ዋጋ መለወጥ አይፈቀድለትም:: እጩ ተወዳዳሪው በሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ላይ በግዥ ፈጻሚው አካል ና እጩ ተወዳዳሪው መካከል ምንም ዓይነት ድርድር ሊደረግ አይችልም::

5. የዋጋ ማቅረቢያ / ፕሮፎርማ/ አሰባሰቢ ሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ኦፊሰሮች መሆን አለበት።
6. ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት ሊያመጡ የሚችሉ አቅርቦቶች በዋጋ የሚወዳደሩት ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸው አቅርቦቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ የተለየ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በመ/ቤቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ አለበት፡፡
7. በዋጋ ማቅረቢያ ለሚፈፀም ግዥ የሚደረገው የዋጋ ውድድር በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ተመሳሳይ ይዘት ያለው የዋጋ ስሌት መሆን ያለበት ሲሆን ውድድሩ ታክስን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡
8. ግዥ ፈጻሚው አካል በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች የግዥ ኦፊሰሮች የወቅቱን የገበያ ዋጋ ማወቅ እና መ/ቤቱ ዝቅተኛ ብሎ የሚመርጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
9. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ውድድር ተካሂዶ አሸናፊ የሆነው አቅራቢ የሞላው ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር የተጋነነ ሆኖ ከተገኘ ድጋሚ የዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴን በመጠቀም ግዥውን መፈጸም ይኖርበታል።
10. ግዥ ፈጻሚ አካላት ዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብ ለሚፈጽሙት ማናቸውም ግዥ እስከተቻለ ድረስ በቢሮው የተዘጋጀውን የዋጋ ማቅረቢያ መደበኛ የጨረታ ሠነድ መጠቀም ይኖርባቸል፡፡
11. በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ለሚከናወኑ ግዥዎች አቅራቢው የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ ወይም ፕሮፎርማ እና መሥሪያ ቤቱ ለአቅራቢው የግዥ ትዕዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ እንደውል ስለሚቆጠሩ ተጨማሪ ውል መዋዋል አስፈላጊ አይሆንም፡፡
12. በዚህ መንገድ የሚገዙ ግዥዎች ቀደም ሲል የተያዘ የገበያ ጥናት መረጃ እና ግዥው በሚፈጸምበት ወቅት የተገኘ ወቅታዊ ዋጋ መረጃ የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ መሠረት አድርጎ ተፈጻሚ መሆን ያለበት ሲሆን፣ በዚህም ወቅት የተገዛው እቃ የአንዱ ዋጋ፣ጠቅላላ ዋጋ፣ የተገዛበት ድርጅት ስም፣ የግለሰቡ ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ፈርማ፣ ማህተም እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በአጠቃላይ ስለግዥ አፈጻጸሙ 3ኛ ወገን ሊረዳው በሚችል መንገድ ቃለ-ጉባዔ ተይዞ መፈረምና ለኦዲተር ዝግጁ መሆን አለበት።
13. የዋጋ ማቅረቢያን / የፕሮፎርማን/ ግዥ ለመጠቀም ሲባል ግዥ ፈጻሚ አካላት በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይችሉም፡፡

## 18. ቀጥታ ግዢ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ቀጥታ ግዥ ለመፈፀም የሚሰጠው ውሳኔ የሚከተሉትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ቀጥታ ግዥ ለመፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀፅ 40 እና 41 የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ሲያሟላ እና ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲያጋጥም ግዥ ፈጻሚ አካላት ቀጥታ ግዥ መፈፀም ይችላሉ።

ከሆነ በመጀመሪያው ውል ላይ በተመለከተው የዋጋ ማስተካከያ አሰራርና ስሌት መሰረት የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ ግዥው ሊፈጸም ይችላል።

4. ግዥ ፈጻሚው አካል ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚያስፈልገው መለዋወጫ የሚገኘው ቀደም ሲል ዕቃውን ከሸጠው አቅራቢ ብቻ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ለዚህም

   4.1. ግዢው ከሌላ አቅራቢ እንዲፈፀም ቢደረግ የሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዢ ፈፃሚው አካል ከሚጠቀምበት መሣሪያ ወይም አገልግሎት ጋር ተጣጥሞ የማይሄድ መሆኑ በባለሙያ ሲረጋገጥ ፤

   4.2. ግዥ ፈጻሚው አካል በቂ የገበያ ጥናት ማድረግ እና ሌላ የተሻለ አማራጭ ገበያው ላይ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

   4.3. ግዥ ፈጻሚው አካል ለሚጠቀምበት ዕቃ የሚገዛው መለዋወጫ ብዛት፣ ተደጋጋሚነት እና የገንዘብ መጠን አንፃር ወደፊት ሌላ አማራጭ መፈለግ የሚያስፈልገው መሆኑንና አለመሆኑን መወሰን ይኖርበታል፡፡

5. በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 "ቀ" መሠረት በባህላዊ ወይም በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኙ በመሆናቸው በለቀማ ቢገዙ ለመሥሪያ ቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኙ የተረጋገጡ እና ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለጉ ዕቃዎች፣ የአካባቢ ዘር፣ የምግብ እህል፣ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ባህር ዛፍ፣ እንስሳትና የመሳሰሉት ሲሆኑ የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትሎ ሊፈፀም ይችላል፣

   5.1 ግዥውን በባህላዊ ወይም በለቀማ መፈፀም ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ለመ/ቤቱ ኃላፊ ወይም ለዚህ ሥራ በኃላፊው ውክልና ለተሰጠው አካል ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

   5.2 የግዥ ኦፊሰሮች ግዥውን በጋራ በመሆን ማከናወን ያለባቸው ሲሆን ግዥውን ለማከናወን በቂ አቅርቦት የሚኖርበትን ገበያ እና የገበያ ዕለት በመምረጥ ለመ/ቤቱ ያሳውቃሉ፡፡

   5.3 የግዥ ኦፊሰሮች በባህላዊ ወይም በለቀማ ስለሚገዛው ዕቃ በቂ ዕውቀት ካለው ሠራተኛ ወይም ግዥውን ከጠየቀው ሠራተኛ ጋር በጋራ በመሆን በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለውን ወይም ያላቸውን ሻጮች በመምረጥ ዋጋ ተደራድረው ግዥው ይፈፀማል፡፡

   5.4 በግዥው አፈፃፀም ሒደት የተፈፀሙትን ግዥዎች ብዛትና አይነት፣ግብይት የተፈጸመበት ቦታ፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን፣ የሻጮችን ሙሉ ስም እና አድራሻ የሚገልፅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ሻጮች በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ መደረግ ይኖርበታል፣

   5.5 በባህላዊ ወይም በለቀማ የተገዙ ግዥዎች በሚጓጓዙበት ወቅት እንዳይበላሹ እና እንዳይጠፉ በጥንቃቄ መያዝ እና በተቻለ ፍጥነት ለሚመለከተው ገቢ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

   5.6 በባህላዊ ወይም በለቀማ ግዥው የተሳተፉት አጠቃላይ የለቀማ ግዥ አፈፃፀሙን የሚገልፅ ቃለ ጉባኤ በማዘጋጀት ተፈራርመው ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5.7 በባህላዊ ወይም በለቀማ ለሚፈፀም ግዥ አቅራቢዎች በአብዛኛው የታተመ ደረሰኝ ስለማይኖራቸው ወጥና የተሟላ ይዘት ያለው የነጭ ወረቀት ደረሰኝ በአባሪ 5 በተያያዘው ናሙና መሰረት ውል ሰጪ፣ ውል ተቀባይ እና ሦስት እማኞችን በዝርዝር በሚያሳይ መልኩ በማዘጋጀት መጠቀም ይገባል።

6. በአዋጁ አንቀፅ 40 (1) (ቀ) መሰረት ለሚፈጸም ግዥ ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈጻሚው አካል ከአንድ አቅራቢ ጋር ለሚያደርገው ግዥ ሊገዛ የታሰበውን የግዥ አይነት እና መጠን በመግለፅ አቅራቢው ሐሳቡን እንዲሰጥ በደብዳቤ ሊጠይቅ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የሚላከው ደብዳቤ እንደአስፈላጊነቱ ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ እና አቅራቢው የተሟላ ሐሳቡን ዋጋን ጨምሮ ሊሰጥ የሚያስችለውን መረጃ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

7. ግዥ ፈጻሚው አካል ከአቅራቢው በፅሁፍ የቀረበለትን ዋጋን የጨመረ ሐሳብ ተቀብሎ ከመረመረ እና የዚህን መመሪያ እና የአዋጁን አንቀፆች እንደማይጥስ በማረጋገጥ ከአቅራቢው ጋር ዋጋን ጨምሮ ድርድር ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት ድርድር ማድረግ ይችላል።

8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 7 ላይ በተመለከተው መሰረት ድርድር ለማድረግ ግዥ ፈጻሚው አካል ተደራዳሪዎችን መምረጥ፣ የሚደረገው ድርድር በሃላፊው የሚሠጠውን አቅጣጫ፣ የድርድርና አትኩሮት ነጥብ መሠረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

9. በአዋጁ አንቀፅ 40 (1) (ቀ) (ረ) መሰረት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈጻሚው አካል ከአንድ አቅራቢ ጋር ለሚያደርገው ግዥ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተቀመጠውን አሠራር በመከተል የውል ስምምነት መፈረም እና ግዥውን ለመፈጸም የተደረጉ የሰነድና የደብዳቤ ልውውጦች በመረጃነት ለ3ኛ ወገን ግልጽ በሆነ መንገድ መያዝ አለባቸው።

10. በቀጥታ የሚገዛ ማንኛውም ግዥ ውሳኔው በጋራ የግዥ ኦፊሰሮች ቡድን ሆኖ የግዥ አፈጻጸሙ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ሁሉም የሚፈራረሙበት ይሆናል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግዥው እንዲፈጸምለት የጠየቀው አካል እንዲገኝ ማድረግ ይቻላል።

## 18.1. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተተ ግዥ ስለመፈጸም

1. በቦል የተደራጁም ሆነ ራሳቸውን ችለው ያሉ ግዥ ፈጻሚ አካላት በግዥ ዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 2,500.00 ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ወይም በገዞ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከመፍታት ጋር የተያያዙ የቀጥታ ግዥዎችን በቀጥታ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት ለመግዛት ይችላሉ:: ሆኖም በዚህ ዓይነት የሚፈጸመው ጥቃቅን ግዥ ድምር በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከብር 25,000.00 የሚበልጥ ሊሆን አይችልም::

2. በዚህ መንገድ የሚገዙ ግዥዎች ቀደም ሲል የተያዘ የገበያ ጥናት መረጃ እና ግዥው በሚፈጸምበት ወቅት ተሰብስቦ የተገኘ ወቅታዊ ዋጋን የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ መሠረት አድርጎ ተፈጻሚ መሆን ያለበት ሲሆን፣ በዚህም ወቅት የተገዛው እቃ የአንዱ ዋጋ፣ ጠ/ዋጋ የተገዛበት ድርጅት ስም፣ የግለሰብ

ሙሉ ስምና አድራሻ በአጠቃላይ ስለግዥ አፈጻጸሙ 3ኛ ወገን ሊረዳው በሚችል መንገድ ቃለ-ጉባዔ ተይዞ መፈረምና ለኦዲተር ዝግጁ መሆን አለበት።

3. ግዥው ሲፈፀም እስከተቻለ ድረስ በመልካም ስነ-ምግባራቸው ከተመረጡት አቅራቢዎች መካከል በዙር መፈፀም ያለበት ሲሆን በተደጋጋሚ ከአንድ አቅራቢ መግዛት የለበትም፡፡

## 19. በመወዳደሪያ ሃሣብ መጠየቂያ የሚፈፀም ግዥ

1. ግዥ ፈጻሚው አካል የምክር አገልግሎት ግዥን የመወዳደሪያ ሃሣብ በመጠየቅ መፈፀም የሚኖርበት ሲሆን የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 300,000.00 /ሦስት መቶ ሺህ /በላይ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 መሰረት የፍላጎት መጠየቂያ ጥሪ ማካሄድ ይኖርበታል።
2. የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች አመራረጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ይፈፀማል፤
   - **2.1.** በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 መሰረት በወጣው የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጥሪ መሠረት ፍላጎታቸውን ከገለፁ አማካሪዎች ውስጥ የተሻለ ብቃት ያላቸውን በመምረጥ፣ ወይም
   - 2.2. የሚፈለገውን የምክር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ አማካሪዎች ውስን ሲሆኑ እነዚህን አማካሪዎች በሙሉ በመጋበዝ፣ ወይም
   - 2.3. የግዥው ግምታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 300,000.00 (ሦስት መቶ ሺህ) በታች ሲሆን ከአቅራቢዎች ወይም ከአማካሪዎች ዝርዝር ውስጥ በመምረጥ፣
3. የመወዳደሪያ ሐሳብ ለማቅረብ የሚጋበዙት አማካሪዎች ቁጥር እስከተቻለ ድረስ ከሦስት ያላነሰ እና ከሰባት ያልበለጠ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ግዥ ፈጻሚው አካል የመወዳደሪያ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ለተመረጡ አማካሪዎች የጥሪ ደብዳቤ በተመሳሳይ ጊዜ በአድራሻቸው መላክ አለበት፡፡ ለግዥው የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ያለ ክፍያ ሊሰጥ እንደሚገባ መ/ቤቱ ሲያምን ከጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ጋር የጨረታ ሰነዱን ሊልክላቸው ይችላል፡፡
5. ለመወዳደሪያ ሐሳብ መጠየቂያ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ቢሮው ያዘጋጀውን መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም እንዲሁም በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የተቀመጠውን ስርአት በመከተል የሚዘጋጅ መሆን ይኖርበታል፡፡
6. ግዥ ፈጻሚው አካል ከተመረጠው አማካሪ ጋር የሚያደርገው ድርድር መሠረታዊውን የጨረታ ይዘትና የሥራ ጥራት የማይቀይር ሆኖ ስለስራው ይዘት፤ ስለአሰራር ዘዴው፤ በስራው ስለሚሰማራው የሰው ኃይል እና መሳሪያ፤ ስለሪፖርት አቀራረብ እና ይዘት በመሳሰሉት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡
7. በንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት የሚደረገው ስምምነት የግዥ ፈጻሚውን አካል ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጠው መሆን የለበትም፡፡

8. በንዑስ አንቀጽ 9 ስር የተገለጹት የመረጣ ዘዴዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች የጨረታ አፈጻጸም ሂደቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ስር የተገለጹትን የግልጽ ጨረታ አሠራሮች በመከተል የሚፈጸሙ ይሆናል።

9. ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 19(1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 5) በተገለጹት የመምረጫ ዘዴዎች ለሚፈጸሙ የምክር አገልግሎት ግዥዎች የሚቀርበው የመጫረቻ ሰነድ በቴክኒክና በዋጋ ማቅረቢያ ተለይቶ በሁለት ኤንቨሎፕ ታሽጎ መቅረብ ያለበት ሲሆን የሚዘጋጀው የመምረጫ መስፈርት እና የሚደረገው ግምገማ የሚከተለውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል።

## 19.1. በጥራት እና በዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚቀርበውን የመወዳደሪያ ሃሣብ በሚገመግሙበት እና በሚያወዳድሩበት ወቅት እያንዳንዱን የቴክኒክ ሃሣብ የሚገመግሙት የሚከተሉትን መስፈርቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
   1.1. ከሚሰጠው ሥራ በተገናኘ አማካሪው ያለውን ልምድ፣
   1.2. በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበውን የጥናት ዘዴ ደረጃ፣
   1.3. ምክሩ ለሚሰጠው መ/ቤት የሚያስገኘው እውቀት፣
   1.4. የውጭ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሐሳቦች ኢትዮጵያውያን ዜጐች በምክር ሥራው ሂደት በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተሣትፎ፣
2. የቀረበው የቴክኒክ ሃሣብ ብቃት ደረጃ በመቶኛ እንደሚከተለው ይመዘገባል፡፡
   1.1 የአማካሪው ልዩ ልምድ .......................................... ከ5 - 10 ነጥብ
   1.2 ሥራ ላይ ይውላል ተብሎ የቀረበው የምክር ዘዴ...............ከ20-50 ነጥብ
   1.3 በምክር አገልግሎቱ ለሚሣተፉ ቁልፍ ባለሙያዎች............ከ30-60 ነጥብ
   1.4 እውቀትን የማሸጋገር ችሎታ.................................. ከ5-10 ነጥብ
   1.5 የኢትዮጵያውያን ተሣትፎ......................................... ከ5-10 ነጥብ
3. ግዢ ፈጻሚ አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከ2.1 እስከ 2.5 የተመለከተውን የመነሻና የመድረሻ ነጥብ መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ መስፈርት የሚሰጠውን ነጥብ መወሰን የሚገባቸው ሲሆን ፣ ጠቅላላ ድምሩ ከ100% መብለጥ የለበትም ።
4. በቴክኒክ ብቃት ማወዳደሪያ/መመዘኛ/ መስፈርቱ 70% (ከመቶ ሰባ) በታች ያገኙ ተወዳዳሪዎች ውድቅ ተደርገው 70% (ከመቶው ሰባ) እና ከዚህ በላይ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ከተቻለ ተጫራቾች በተገኙበት የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ይከፈታል፡፡
5. በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የማያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት።
6. የዋጋ ማቅረቢያው ሲከፈት ለመገኘት የፈለጉ አማካሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግልጽ ይከፈታል።

7. የምክር አገልግሎት የሚገኘው ከውጭ አማካሪዎች ካልሆነ በስተቀር የአገር ውስጥ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ ለግምገማ ሲባል የአገር ውስጥ ታክስ ይጨምራል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገር ውስጥ እና የውጭ አማካሪዎች የሚያቀርቡት ዋጋ የማጓጓዣ፣ የትርጉም እና የጽህፈት ሥራ ወጪን ይጨምራል፡፡
8. ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተወዳዳሪ ለዋጋ 100 ነጥብ የሚሰጥ ሲሆን ሌሎች ተወዳዳሪዎች ግን እንዳቀረቡት ዋጋ ከፍተኛ ላቀረበ አነስተኛ ነጥብ ይሰጣል።
9. የቴክኒክ ግምገማ 80% (ከመቶ ሰማኒያ) የነጥብ ድርሻ ሲሆን፣ ለዋጋ የሚሰጠው ክብደት 20% /ከመቶ ሃያ/ ነጥብ ይሆናል፡፡
10. ለቴክኒክ ብቃት ደረጃ እና ለዋጋ የተሰጡትን ነጥቦች በማዳመር በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል::
11. በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታ የሚፈፀም የምክር አገልግሎት ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተገለጸውን የግዥ አፈጻጸም ሂደት በተጨማሪነት መሠረት ማድረግ ይኖርበታል::

## 19.2. በሚከናወነው የሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ

1. በሥራ ጥራት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የምክር አገልግሎቱ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ይሆናል፣
   1.1. የምክር አገልግሎቱ ውስብስብና የተለዬ የሙያ ብቃት የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚሁ ግዥ የተሟላ ማጣቀሻ ሠነድ (TOR) ማዘጋጀት የማይቻል ሲሆን ወይም ከአማካሪው የሚገኘውን የምክር አገልግሎት ዓይነት ለይቶ ማወቅ የማይቻል ሲሆን ወይም አማካሪው የራሱን የፈጠራ ችሎታ ተጠቅሞ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የሚኖርበት ሲሆን፣
   1.2. ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን አማካሪዎች ማግኘት አስፈላጊ በሚሆንባቸው እና የወደፊት ውጤታቸው አሳሳቢ የሚሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ሲሆኑ፣
   1.3. የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ምክንያት የሚቀርቡትን ሀሳቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ማወዳደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲታመን፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.12 ተራ ቁጥር 2(2.2) መሠረት የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል::
3. በቴክኒክ ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ያገኘውን ተጫራች ብቻ የዋጋ ፖስታ በመክፈት የጨረታው አሸናፊ አድርጎ በመምረጥ ከተጫራቹ ጋር ዋጋን ጨምሮ በምክር አገልግሎቱ አሰራር እና ውጤት ላይ ድርድር ሊደረግ ይችላል ፡፡
4. ከላይ በአንቀጽ 19.2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በውድድሩ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም በላይ ከሆነና በቴክኒክ ግምገማው ውጤት ሁለተኛ የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ ከመ/ቤቱ የመክፈል አቅም ጋር የሚመጣጠን ከሆነ ግዥውን ሁለተኛ ከወጣው ተጫራች መፈፀም ይቻላል::

5. በጨረታው አሸናፊ ከሆነው ተጫራች ጋር ድርድር ተደርጎ ውል እንደተፈጸመ የሌሎች ተወዳደሪዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ሳይከፈት ለተጫራቾቹ ተመላሽ መደረግ አለበት።

## 19.3. በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ

1. በቁርጥ በጀት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ውስብስብነት የሌለው፣ በትክክል ሊገለፅ የሚችል ሲሆን እና ለዚሁ ተግባር የተፈቀደው በጀት ጣሪያ ያለው ከሆነ ነው።
2. በዚህ መመሪያ 13.12 ተራ ቁጥር 2(2.2) መሠረት የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ ይደረጋል።
3. በቴክኒክ ግምገማው ተፈላጊውን መመዘኛ ማለትም ዝቅተኛውን መስፈርት /Minimum Requiremnt/ ያሟሉት ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል። በእያንዳንዱ ተጫራች ለጨረታው የቀረበውን ዋጋ በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁ መደረግ አለበት።
4. ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ያቀረቡ ተጫራቾች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል።
5. ለጨረታው ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን ያልበለጠ ዋጋ ያቀረበና ከፍተኛ የቴክኒክ ውጤት ያለው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል። እንደአስፈላጊነቱም ዋጋን ያልጨመረ ድርድር ሊደረግ ይችላል።

## 13.4. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሰረተ መረጣ

1. በዝቅተኛ ዋጋ ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው የሚገዛው የምክር አገልግሎት የባለሙያውን ልዩ ችሎታ የማይጠይቅ፣ ውስብስብ ያልሆነና ስታንዳርድ ያለው ወይም በተመሳሳይና ወጥ በሆነ አሠራር ሊከናወን የሚችል ሲሆን ነው።
2. ግዥ ፈጻሚ አካላት በዚህ የመረጣ ዘዴ ተጫራቾችን ለመገምገም ሲፈልጉ ዝቅተኛው የቴክኒክ መመዘኛ ነጥብ መጠን በመወሰን ከአቅራቢዎች ዝርዝር ለተመረጡ ተጫራቾች በሚሰጠው የመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ ላይ በግልጽ ማመልከት አለባቸው።
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.12 ተራ ቁጥር 2 "(2.2)" መሠረት የቴክኒክ ሀሳቦችን የያዙ ፖስታዎች ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈቱ በማድረግ የቴክኒክ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል።
4. በግምገማው ውጤት ለቴክኒክ ብቃት የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ያላሟሉ ተወዳዳሪዎች ከጨረታው ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል።
5. በቴክኒክ ብቃት ግምገማ ለዋጋ ውድድር የሚያበቃቸውን ዝቅተኛ ውጤት ያላመጡ ተጫራቾች የዋጋ ፖስታ ሳይከፈት እንዲመለስ መደረግ አለበት።

6. በቴክኒክ ግምገማ ውጤታቸው ለዋጋ ውድድር ያለፉት ተወዳዳሪዎች የዋጋ ፖስታ ተጫራቾች በተገኙበት እንዲከፈት ይደረጋል:: በተጫራቾች ለጨረታው የቀረበው ዋጋ በመክፈቻው ሥነ ሥርዓት ላይ የተገኙ ተጫራቾች እንዲያውቁት መደረግ አለበት::
7. በቴክኒክ ግምገማ ለብቃት ማረጋገጫ የተቀመጠውን ዝቅተኛ መሥፈርት ካሟሉት ተወዳዳሪዎች መካከል አነስተኛ ዋጋ የሠጠው ተጫራች የውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል::

## 19.5. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሰረተ መረጣ

1. በአማካሪዎች ብቃት ላይ የተመሠረተ መረጣ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ለአማካሪው የሚሰጠው ሥራ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት እና ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ ከሥራው ጋር የማይመጣጠን ሲሆን ነው::
2. ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው የምክር አገልግሎቱ ወጪ ከብር ሃምሳ ሺህ የማይበልጥ በሚሆንበት ጊዜ ብቻ ነው::
3. ለዕጩ ተወዳደሪዎች የሚዘጋጀው ማጣቀሻ ጽሁፍ ወይም ቢጋር አማካሪው ያለውን የሥራ ልምድና የብቃት ደረጃ እንዲገልጽ የሚጠይቅ መሆን አለበት::
4. ከአቅራቢዎች ዝርዝር ወይም ግዥ ፈጻሚው አካል ያለውን መረጃ በመጠቀም በውድድሩ እንዲሳተፉ ከመረጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሚከናወን ግምገማ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዕጩ ተወዳዳሪ የቴክኒክና የዋጋ ማቅረቢያ ሐሳቡን በአንድ ላይ እንዲያቀርብ በማድረግና በመደራደር በሚደረስበት ስምምነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል::
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት የሚደረገው ስምምነት የግዥ ፈጻሚውን አካል ጥቅም የሚጎዳ ወይንም ለተመረጠው አማካሪ ከሌሎች ተጫራቾች አንፃር ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስጠው መሆን የለበትም ።

## 19.6. አንድ አማካሪ የሚመረጥበት ሁኔታ፣

ግዥ ፈፃሚ አካላት የምክር አገልግሎት ግዥን ከአንድ አማካሪ ለመፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 40 እና 41 እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

# 20. የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ ጨረታ

1. ግዥ ፈጻሚው አካል የሚገዛው የምክር አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ ከብር 300,000 .00 (ከሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚበልጥ ሲሆን በምክር አገልግሎቱ አቅርቦት ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ የግልፅ ጨረታ ጥሪ ማውጣት አለበት::
2. ለፍላጎት መግለጫ የሚደረገው የጨረታ ጥሪ እንደ ሁኔታው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13.2. ወይም በአንቀፅ 13.2 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተመለከተውን ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን

3.5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3.3 መሰረት የሚከናወነው ግምገማ ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የቀረበውን ሐሳብ በመመርመር ለሁለተኛው ዙር ጨረታ የሚያገለግለውን የፍላጎት መግለጫ እና በጨረታው ሊሳተፉ የሚገባቸውን ተጫራቾች መለየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በግምገማው ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ከሁሉም ወይም ከተወሰኑ ወይም ከአንድ ከተለየ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር ግዥ ፈጻሚው አካል ውይይት ሊያደርግ ይችላል፡፡

ለ/ ከላይ በፊደል 'ሀ' ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት እጩ ተወዳዳሪዎች የሰጡትን ሐሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና በተሻለ የዳበረ ሐሳብ ለማመንጨት ያለመ ሊሆን ይገባል፡፡

ሐ/ ከላይ በፊደል 'ሀ' ላይ በተገለፀው መሰረት የሚደረገው ውይይት ግዥ ፈጻሚው አካል በሁለተኛው ዙር ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ማሟላት የሚገባቸውን እንዲያሟሉ ለማድረግ ነው።

3.6. በሁለተኛው ዙር የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በግልፅ ጨረታ የተገለፀውን አሠራር መከተል የሚኖርበት ሲሆን በተጨማሪም የጨረታ ዋስትና መጠን ተሰልቶ ለሁለተኛው ዙር ጨረታ እንዲሳተፉ የተመረጡት ዕጩ ተወዳዳሪዎች እንዲያቀርቡ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡

3.7. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3.6 ላይ በተገለፀው መሰረት በመጀመሪያው ዙር ተቀባይነት ያገኙ ዕጩ ተወዳዳዎች ለሁለተኛው ዙር የጨረታ ውድድር በደብዳቤ እንዲጠሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.8. እንደአስፈላጊነቱ ግዥ ፈጻሚው አካል ከደብዳቤ ጥሪው ጋር ለሁለተኛው ዙር የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ለዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊልክ ወይንም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው እንዲወስዱ ሊያደርግ ይችላል።

3.9. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3.8 ላይ በሰፈረው መሰረት ለዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፈው ጥሪ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ ሊያመለክት ይገባል፡፡

4. በሁለት ደረጃ ጨረታ አሸናፊውን ተጫራች ለመወሰን ግምገማ እና ውድድር የሚደረገው በጨረታ ሠነዱ በተዘረዘሩት ነጥቦች መሠረት ይሆናል፡፡

5. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚው አካል በጨረታው ግምገማ ከፍተኛ ውጤት ካመጣው አቅራቢ ጋር ከዋጋ በስተቀር በሌሎች ጉዳዩች ላይ ድርድር ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 21.1. በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ግዥ ፈጻሚ አካላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 በተመለከተው መሠረት በሁለት ደረጃ ጨረታ ግዢን ለመፈፀም የሚችሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

1. ለሚገዙት እቃዎችና አገልግሎቶች በቂ ዝርዝር ማዘጋጀት በመ/ቤቱ ደረጃ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት ባህሪያቸውን ለይቶ ለማሣየት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ እና ግዥ ፈጻሚው አካል የግዢ ፍላጎቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማሟላት የሚያስችል መፍትሄ ለመፈለግ፣

ሀ. ፍላጎቱን ለማሟላት የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ናቸው በማለት ጨረታን፣ የእቃና የአገልግሎት አቅርቦት መወዳደሪያ ሃሣብን በሥራ ላይ ማዋል ሲፈልግ፡፡

ለ. በሚገዙት እቃዎችና አገልግሎቶች ባህሪይ ወይም ተፈጥሮ ምክንያት ከአቅራቢዎች ወይም ሥራ ተቋራጮች ጋር ድርድር ማድረግ ሲያስፈልግ

ሐ. መጠናቸው በገበያ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ማምረትን የሚጨምር ወይም የምርምር እና የልማት ወጪዎችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈጻሚው አካል የምርምር፣ የሙከራ ጥናት እና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ውል መፈፀም ሲፈልግ፡፡

2. ጨረታ እንዲወጣ ተደርጐ ተጫራቶች ያልቀረቡ እንደሆነ ወይም የቀረቡት ተጫራቾች ውድቅ ሲደረጉ እና መ/ቤቱ ሌላ ጨረታ ቢወጣ ውጤት መገኘቱ አጠራጣሪ ነው ብሎ ሲያምን፡፡

## 22. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ

የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ አስፈላጊ የሚሆነው የሚፈጸመው ግዥ ውስብስብ ሲሆን ነው ፤ ስለሆነም አፈጻጸሙ በሚከተለው አኳኋን በመከተል መፈጸም አለበት።

1. ግዥ ፈጻሚው አካል ግዥው ከሚኖረው የተለየ ባሕርይ አንፃር በመጀመሪያ የተወዳዳሪዎችን ብቃት በቅድሚያ ግምገማ ማድረግ አለብኝ ብሎ ሲያምን እንደ ግዥው አይነት የብሔራዊ ግልፅ ጨረታ ወይንም የአለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ የሚያስፈልጋቸው ግዥዎች ከሚከተሉት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱን የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል ፡-
   - 2.1. በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ወይም በባህርይው ውስብስብ የሆነ የዲዛይን፣ የማምረትና የተከላ ሥራ በአንድ ድርጅት መጠናቀቅ ያለበት የግንባታ ወይም የማምረቻ መሳሪያ ወይም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግዥ ሲሆን፣ ወይም
   - 2.2. የሚቀርበው ዕቃ ወይም መሣሪያ ጥራትና ጠቀሜታ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው እና የተከላ አገልግሎትን ያካተተ ሲሆን፣ ወይም
   - 2.3. የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ግዥ በመሆኑ ብቃታቸው በቅድመ ብቃት ምዘና የሚረጋገጥ ተጫራቾች ብቻ በውድድሩ ተካፋይ መሆን እንደሚገባቸው ሲታመንበት፣
3. በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚዘጋጀው የጨረታ ጥሪ ብቃት ያላቸውን ተጫራቾች ለመምረጥ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ጨረታ ጥሪ መሆኑ መገለፅ ይኖርበታል።
4. የቅድመ ብቃት ግምገማ ለማድረግ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በቢሮው የተዘጋጀውን የቅድመ ብቃት መምረጫ መደበኛ የጨረታ ሠነድ እንደመነሻ አድርጎ በመጠቀም ይሆናል:: የቅድመ ብቃት መምረጫ መሥፈርቱ እንደግዥው ባህርይና ዓይነት ሊለይ የሚችል ቢሆንም ተወዳዳሪ ድርጅቶቹ እንዲያቀርቡ የሚጠየቁት መረጃዎች የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል::

4.1 በተመሳሳይ ሥራ ወይም ዕቃ ማምረት ላይ ድርጅቱ ያለው ልምድ፣

4.2 ድርጅቱ ሥራውን ወይም ዕቃውን ለማምረት የሚያስችል ተመጣጣኝ የሰው ኃይል፣ ማሽነሪ፣ የማምረቻ መሣሪያ ብዛት እና ኢንፍራስትራክቸር ሁኔታ፣

4.3 ድርጅቱ አሁን በመሥራት ላይ ያለው የግንባታ ሥራ ወይም በማምረት ላይ ያለው ዕቃ ብዛት፣

4.4 ድርጅቱ የውል ግዴታውን ለማጠናቀቅ በቂ የገንዘብ አቅም እና መልካም ዝና ያለው መሆኑን፣

5. የሚከናወነው የተጫራቾች ግምገማ ለቅድመ ብቃት ማረጋገጫ በግዥ ፈጻሚው አካል የተዘጋጀውን መሥፈርት መሠረት በማድረግ ይሆናል::

6. ለቅድመ ብቃት ውድድሩ ያመለከቱ ተጫራቾች በሙሉ የግምገማ መሥፈርቱን እስከአሟሉ ድረስ ምንም ዓይነት የቁጥር ገደብ ሳይደረግ በሚቀጥለው ውድድር እንዲሳተፉ መደረግ አለበት::

7. ግዥ ፈጻሚ አካላት በቅድመ ብቃት ውድድር የሚሳተፉ ድርጅቶች በሽርክና ወይም በጋራ መወዳደር እንደሚችሉ ሊፈቅዱ ይችላሉ::

8. የቅድመ ብቃት ውድድሩን በግል ያለፉ ተወዳዳሪዎች በግዥ ሂደት የሚኖረውን ውድድር እንደማያጣብብ በግዥ ፈጻሚው አካል ካልታመነ በስተቀር በጋራ ወይም በሽርክና የመጫረቻ ሠነዱን እንዲያቀርቡ መፈቀድ የለበትም::

9. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 8 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ወይም በሽርክና ለቅድመ ብቃቱ ውድድር ቀርበው ይህንኑ መሰረት በማድረግ በግምገማው ለሚቀጥለው ጨረታ ያለፉና የተመረጡ ተጫራቾች በግል በጨረታው እንዲወዳደሩ አይፈቀድላቸውም::

10. የቅድመ ብቃቱ ግምገማ ውጤት እንደታወቀና በግዥ ፈጻሚው አካል ተቀባይነት እንዳገኘ በጨረታው እንዲሳተፉ ለተመረጡትና ላልተመረጡት ተጫራቾች ውጤቱ ለሁሉም በእኩል ሁኔታ ሊገለጽላቸው ይገባል::

11. ድርጅቱ በጨረታው ግምገማ አሸናፊ ለመሆን ቢችልም ለቅድመ ብቃት ውድድር የተሰጠው መረጃ የተሳሳተ ከሆነ ወይም በቅድመ ብቃት ውድድሩ ወቅት የነበረው ብቃት አሁን ባለመኖሩ ውሉን በሚጠበቅበት ሁኔታ ለመፈጸም አለመቻሉ በበቂ ሁኔታ ከተረጋገጠ ግዥ ፈጻሚው አካል ድርጅቱ ውሉን እንዲፈርም ሳይፈቅድ ይችላል::

12. በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ውድድሩ ተቀባይነት ላገኙት ተጫራቾች በዚህ መመሪያ ለብሔራዊ ወይም ለዓለም አቀፍ ግልፅ ጨረታ የተመለከተውን ስርአት በመከተል የጨረታ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለተጫራቾች በአድራሻቸው ሊላክላቸው ወይም ከመ/ቤቱ ቀርበው እንዲወስዱ ተደርጎ ቀሪ የግዥ አፈፃፀም ስርአት በዚህ መመሪያ የተደነገገውን አሠራር ተከትሎ ይፈፀማል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ግዥ

### 23. ልዩ ከፍተኛ ግዥ

1. የክልሉ መንግስት ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ይረዳል ወይም የተለየ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ሲታመንና በዚህም መሠረት የክልሉ መንግስት አስፈላጊው እንዲፈጸም ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ልዩ ግዥ በማዕከል ሊፈፀም ይችላል።
2. ልዩ ክልላዊ ጥቅም የሚኖራቸውን ግዥዎች እንዲፈጽም በክልሉ መንግስት የሚቋቋመው አካል ግዥውን በልዩ ሁኔታ እንዲፈጽም በክልሉ መንግስት ካልታዘዘ በስተቀር የአዋጁን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጠብቆ ግዥውን ተፈፃሚ ማድረግ ይኖርበታል።

## 24. በግዥ ፈጻሚ አካላት በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ልዩ ግዥ

1. የልዩ ግዥ አፈጻጸም አዋጁን እና ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ ለግዥው በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል።
2. በሁሉም ወይም በተወሰኑ መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለግ የዕቃ ወይም የአገልግሎት አቅርቦት የኮንትራት ግዥ የሚፈፀመው የማዕቀፍ ስምምነትን መሠረት በማድረግ ሲሆን የሚከተሉትን አሠራሮች ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል።
   2.1 በዚህ መመሪያ ክፍል 7 ላይ የተመለከተውን መሠረት በማድረግ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል በቂ እና ግልፅ የሆነ የውስጥ አደረጃጀት በመፍጠር የጨረታ ሰነድ የማዘጋጀት፣ የመገምገም፣ የማፅደቅ እና ውል የማስተዳደር ስራዎች በተለያዩ ቡድኖች (አካላት) እንዲፈፀሙ ያደርጋል፣
   2.2 ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጨረታ ዝግጅት እና ግምገማ ወቅት የሙያ ድጋፍ ከመንግስት መ/ቤቶች ሊጠይቅ እና ሊያገኝ ይችላል።
3. በሁሉም ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚፈለጉ ተመሳሳይ ግዥዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው በሚከተሉት እና ይህንን መመሪያ ተከትሎ አሰራሩን ለማስፈፀም በሚወጡት ሰነዶች መሰረት ይፈፀማል።
   3.1 ቢሮው በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በመለየት ዝርዝር ያወጣል፣ ዝርዝሩንም በየጊዜው ያዳብራል፣ ለግዥ ፈጻሚ አካላት እና ልዩ ግዥ ለማስፈጸም ለተቋቋመው አካል ያሳውቃል፣
   3.2 እያንዳንዱ ግዥ ፈጻሚ አካል በተላለፈለት ዝርዝር መሰረት አመታዊ የግዥ ፍላጎቱን ልዩ ግዥ ለሚፈፅመው አካል እንዲያሳውቅ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ (ማሳወቅ) አለበት፣
   3.3 ልዩ ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የሁሉንም የግዥ ፈጻሚ አካላትን ፍላጎት በማሰባሰብ የግዥ እቅድ ያዘጋጃል፣ ያዘጋጀውን እቅድ በዚህ መመሪያ መሠረት ለቢሮው እና ግዥው ለሚመለከታቸው ግዥ ፈጻሚ አካላት ያሳውቃል።
4. ልዩ ግዥ እንዲፈፅም የተቋቋመው አካል ለግዥው የሚፈረመውን የውል አይነት እና ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ይወስናል።

4.1 በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ግዥ የሚፈጽመው አካል የሚከተሉትን ተጨማሪ ዝርዝሮች ያካተተ የግዥ ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፣

ሀ/ የማስታወቂያ ጥሪ የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ለመፈራረም እንዲቻል መሆኑን፣

ለ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚፈፀመው ግዥ ዓይነት፣ ግምታዊ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቆይበትን ጊዜ፣

መ/ በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙትን ግዥ ፈጻሚ አካላት ብዛት፣

4.2 ልዩ ግዥ በሚፈጽመው አካል ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ መደበኛ የጨረታ ሰነድ በመጠቀም የሚዘጋጅ ሆኖ የሚከተሉትን እንዲያካትት መደረግ አለበት፣

ሀ/ የሚገዛውን ዕቃ ዝርዝር እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የግዥ መጠን እና የርክክብ ሁኔታ፣

ለ/ የማስረከቢያ ቦታ እና እስከተቻለ ድረስ ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ፣

ሐ/ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚጠቀሙ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣

መ/ ግዥው የዋጋ ማስተካከያ የሚፈቅድ ከሆነ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሁኔታ እና አፈፃፀሙን፣

ሠ/ የግዥው ውል ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣

5. በአዋጁ አንቀፅ 48 ላይ በተገለፀው መሰረት ለማዕቀፍ ስምምነት በወጣ ጨረታ አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ ጋር እስከ 2/ሁለት ዓመታት/ ሊደርስ የሚችል ውል የሚፈረም ሲሆን የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የሚከተሉትን እና ሌሎች ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንደግዥው ሁኔታ እና እንደአስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ከሆኑ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች ጋር በደረጃቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተመሳሳይ የሆነ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈርም ይችላል፣

5.1 የሚፈለገው የግዥ መጠን እና የተመረጠው አቅራቢ አቅም ከሚፈለገው አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን ሲሆን፣ ወይም

5.2 በገበያው ላይ ያሉ ተመሳሳይ አቅራቢዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑና የግዥ ዕድሉን ለብዙ አቅራቢዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ወይም

5.3 የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በመሆኑ ምክንያት ግዥውን በቀረበው ዋጋ በቶሎ ማጠናቀቅ ሲያስፈልግ፣

6. የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5 ላይ በተገለጸው መሰረት በአሸናፊው ዋጋ እንዲያቀርቡ በደረጃቸው ቅደም ተከተል ሌሎች ተጫራቾችን ለውል ስምምነት ሲጋብዝ የሚጋብዛቸውን አቅራቢዎች ቁጥር እንደ ግዥው ሁኔታ አይቶ ይወስናል:: በዚህ መሰረት የሚፈፀም ውል፣

6.1. በአሸናፊው ዋጋ ለማቅረብ ፈቃደኛ ከሆኑ አቅራቢዎች ጋር ይፈራረማል፣

6.2 አሸናፊው ድርጅት ለውል ስምምነት እና ምርጫ በሚኖራቸው ጉዳዮች ላይ የምርጫ ቅድሚያ እንዲያገኝ ይደረጋል፣

6.3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5 ላይ የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ከጨረታው ዋና አሸናፊ ጋር የሚፈረመው የግዥ መጠን ከጠቅላላው ግዥ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) ያነሰ መሆን የለበትም::

7. የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም የተቋቋመው አካል የመንግሥት መ/ቤቶችን ወክሎ አጠቃላይ የውል ስምምነት የሚፈርም ሲሆን ስምምነቱም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተገቢ ናቸው የሚባሉ ሁኔታዎችን በግልፅ እንዲያካትት መደረግ አለበት፣

  7.1 በውል ስምምነት አስተዳደር ወቅት በማዕቀፍ ስምምነቱ የሚጠቀሙ የመንግሥት መ/ቤቶችን ዝርዝር፣ የማዕቀፍ ስምምነቱን የሚፈርመውን እና የሚያስተዳድረውን አካል እንዲሁም የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢዎች የሚኖራቸውን ኃላፊነት እና ግዴታ

  7.2 እንደ አስፈላጊነቱ አሸናፊው ድርጅት አቅርቦቱን ከዞን እስከ ወረዳ ለማድረስ እታች ድረስ በመውረድ የማከፋፈያና ማቅረቢያ ቦታ ሊያዘጋጅ እንደሚገባው፣

  7.3 በማዕቀፍ ስምምነቱ የግዥ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብ የሚደረግበትን፣ ክፍያ የሚፈፀምበትን እና ክትትል እና ግምገማ የሚደረግበትን ስርአት፣

  7.4 አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የሚፈቱበትን ስርአት፣

8. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 7 እና በአዋጁ እንዲሁም ልዩ ግዥ እንዲፈጽም ኃላፊነት በተሰጠው አካል የማቋቋሚያ ደንብ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል በማዕቀፍ ስምምነት አስተዳደር ወቅት የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

  8.1 የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በውሉ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ይከታተላል፤

  8.2 ለማዕቀፍ ስምምነቱ ተፈፃሚነት የተያዘውን የውል ማስከበሪያ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፤ በውሉ መሰረት አለመፈፀሙን ሲያረጋግጥም እንደአስፈላጊነቱ በመውረስ ገንዘቡን ለመንግስት ገቢ ያደርጋል። አቅራቢው የፈፀመውን ጥፋት በሚመለከትም ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል፣

  8.3 በማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው እና በግዥ ፈጻሚው አካል መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን በውይይት ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤

  8.4 በጋራ ስምምነት ላይ በተመሠረተ መንገድ በማዕቀፍ ስምምነቱ ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልግ ይህንኑ ይፈፅማል፤

  8.5 በውል አፈፃፀም ወቅት ለግዥ ፈጻሚ አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤

  8.6 የማዕቀፍ ስምምነቱ ሲጠናቀቅ የውል አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ የውል ማስከበሪያው እንዲለቀቅ ያደርጋል።

9. የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የሚፈጽመው አካል ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማዕቀፍ ስምምነቱን ሊሰርዝ ይችላል።

  9.1. የማዕቀፍ ስምምነቱ አቅራቢ በውሉ መሰረት ግዴታውን አለመወጣቱ ሲታወቅ፣

  9.2. የግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ ፍላጎት በግልጽና በታወቀ ምክንያት ሲለወጥ፣

  9.3. የተደረገው የማዕቀፍ ስምምነት ዋጋ፣ ሌሎች ሁኔታዎች እንዲሁም የገበያው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የመንግስት መ/ቤቶችን ሊጎዳ የሚችል ሰፊ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣

  9.4. በዚህ ንዑስ አንቀፅ 9.2 እና 9.3 መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት እንዲቋረጥ ሲወሰን፣ የማዕቀፍ ስምምነቱ የሚቋረጥበትን ምክንያት እና ተፈፃሚ የሚሆንበትን ቀን በመግለፅ የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በጽሑፍ መስጠት አለበት፣

9.5. የቅድሚያ ማስጠንቀቂያው ጊዜ እስከሚጠናቀቅ በውሉ ላይ የተገለፁት መ/ቤቶች ግዥያቸውን ከሌላ አቅራቢ መፈፀም አይችሉም።

10. ግዥ ፈጻሚ አካላት የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል የተላለፈላቸውን የማዕቀፍ ስምምነት ቅጂ በመጠቀም በውሉ ላይ የተገለፁትን አቅርቦቶች ለመግዛት የሚያስችል የግዥ ትዕዛዝ ለማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ያስተላልፋሉ። ግዥ ፈጻሚው አካል ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽም ከተቋቋመው አካል ጋር በመመካከር ከአቅራቢው ጋር ተጨማሪ የተናጠል ውል መፈረም ይችላል።

11. የግዥ ትእዛዙ ወይም ተጨማሪው የተናጠል ውል በአጠቃላይ ውሉ ውስጥ የተካተቱ መሰረታዊ የሆኑ ዋጋ እና ሌሎች የውል ሁኔታዎችን አይለውጥም፣ ሆኖም ግዥ ፈጻሚው አካል በሚከተሉት እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ጋር የተናጠል ውል ሊፈፅም ይችላል፦

11.1. ዕቃው የሚቀርብበትን እና ክፍያ የሚፈፀምበትን ጊዜ ለማሳጠር፣

11.2. በአንድ የግዥ ትዕዛዝ የሚቀርበውን ዕቃ ብዛት ለመወሰን፣

11.3. ዕቃው የሚቀርብበትን ቦታ ለማሳወቅ ወይም ለመቀየር፣

12. ግዥ ፈጻሚው አካል ከላይ በንዑስ አንቀፅ 11 በተገለፀው መሰረት የፈፀመውን የተናጠል ውል ቅጅ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ እንዲፈጽምና እንዲያስተዳድር ለተቋቋመው አካል መስጠት አለበት።

13. በማዕቀፍ ስምምነት አፈፃፀም ወቅት ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

13.1 የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡት በማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ለሚፈፅመው አካል የገለፁትን ፍላጐት መሠረት በማድረግ ግዥው በማዕቀፍ ስምምነት የተፈፀመውን ዕቃ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ፣

13.2 በማዕቀፍ ስምምነቱ ውስጥ የተገለፁ ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚፈፀሙ ግዴታዎች በስምምነቱ መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ፣

13.3 በውሉ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮችን የማዕቀፍ ስምምነት ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በጋራ በመሆን ለመፍታት ጥረት ማድረግ፣

13.4 የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው በዋና ዋና የውል ጉዳዮች ማለትም የዕቃ ጥራት እና መጠን ማጓደል፣ የማቅረቢያ ጊዜ አለመጠበቅ፣ በአስተሻሸግ እና በመሳሰሉ የፈፀማቸውን ጥፋቶች የማዕቀፍ ስምምነቱን እንዲያስተዳድር ለተቋቋመው አካል በወቅቱ በጽሑፍ ማሳወቅ፣

13.5 በማዕቀፍ ስምምነት ለተካተቱ ፍላጎቶቻቸው የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጡበትን ጊዜ እና እንዲቀርብላቸው የሚፈልጉትን የአቅርቦት መጠን መወሰንና ስለዝርዝር አፈፃፀሙ ልዩ ግዥ የሚፈጽመውን አካል ማማከር፣

14. የማዕቀፍ ስምምነትን እንዲያስተዳድር የሚቋቋመው አካል የግዥ ፈጻሚ አካላት ሥራ እንዳይጓተት የማዕቀፍ ስምምነት በወቅቱ መፈረም የሚኖርበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በወቅቱ የማዕቀፍ ስምምነት ሊፈረም አለመቻሉን ካረጋገጠላቸው ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚኖራቸውን ፍላጎት በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎችን በመጠበቅ መግዛት ይችላሉ፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የእራሳቸው የሥራ ውጤት ባልሆነ በሽቀጣ ሸቀጥ ወይም የፋብሪካ ውጤቶችን የማቅረብ ፈቃድ የተሠጣቸው ከሆነ እንደማንኛውም ነጋዴ ልዩ አስተያየት ሳይደረግላቸው በግዥ መመሪያው መሠረት ይስተናገዳሉ፣

4. ለተቋማቱ የሚሰጠው ቅድሚያ ክፍያ ግዥ ፈጻሚው አካል ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው በጋራ በሚንቀሳቀስ ባንክ ሒሳብ ገንዘቡን ተቀማጭ በማድረግ ከውሉ ጋር ለተገናኙና አስፈላጊ ለሆኑ ወጭዎች እየታመነበትና ቀደም ሲል በወሰዱት ገንዘብ ተገቢውን ሥራ የሰሩ መሆኑ እየተረጋገጠ ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል።

5. ተቋማቱ በጨረታው ወቅት እንዲወዳደሩ በየደረጃው ከሚገኝ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የብቃት ማረጋገጫ መረጃ እና ልዩ አስተያየት ድጋፍ እንዲደረግላቸው የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

6. በግለሰብ ደረጃ እና በማኅበራት የተደራጁ ተቋማት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ የሚቀር ግብርን ( withholding tax ) ግዥ ፈፃሚ አካላት ማስከፈል ይጠበቅባቸዋል፣

7. ተቋማቱ ግዥ ፈጻሚ አካላት በሚፈጽሟቸው ግዥዎች በጨረታ ሲወዳደሩ ከሌሎች ተጫራቾች በተለየ ሁኔታ የሚከተሉት ድጋፎች ይደረግላቸዋል፡፡

   7.1. ለጨረታ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ በነፃ ያለክፍያ እንዲሰጣቸው የሚደረግ ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያም እንዲያስይዙ አይጠየቁም፣

   7.2. የውል ማስከበሪያና የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ተቋማቱን ከአደራጃቸው አካል በሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል።

   7.3. በጥ/አነ/ን/ሥራዎች ተደራጅተው በጨረታ ውድድር ላይ ሲሳተፉ የሚወዳደሩባቸው የዕቃዎች፣ አገልግሎቶች እና የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች የጥራት ደረጃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች በተለየ ተወዳድረው ካገኙት ነጥብ ላይ 7 (ሰባት) ነጥብ ተጨምሮላቸው ውድድሩ ውጤት እንዲሰላ ይደረጋል፡፡ በዚህ አግባብ ተሰልቶም ነጥባቸው ከሌሎች ጋር እኩል ከሆነ ቅድሚያ ለእነዚህ ተቋማት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

   7.4. ለግብርና ግብዓት የሚመረቱ ቴክኖሎጂዎችን ማለትም ቢቢኤም (BBM) ዘመናዊ ቀፎ፣ ታይሪጀር፣ ጋቢወን ወዘተ እንዲሁም በከተሞች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የድንጋይ ንጣፍ ስራዎች ወይም የኮብል ድንጋይ ስራዎች በጥናት በሚወሰን ቁርጥ ዋጋ መሠረት በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለተደራጁ አካላት ይሰጣል።

   7.5. ተቋማቱ ቅድሚያ ክፍያ ከአሸነፉበት ጠቅላላ የግዥ ዋጋ እስከ 30% (ሰላሳ በመቶ) ሊያገኙ የሚችሉት ተቋማቱን አደራጅቶ ፈቃድ ከሰጣቸው በየደረጃው ከሚገኝ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የሚፈቀደውን ገንዘብ መጠን በመጥቀስ በሚሰጥ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ ይሆናል፡፡

7.6. ተቋማቱ የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ የሚሆኑት የሚወዳደሩበት የግዥ መጠን እስከ ብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሽህ ብር) ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ብር 100,000.00 / አንድ መቶ ሺህ / እና በላይ ለሆነ ግዥ ተቋማቱ እንደማንኛውም አቅራቢ የቫት ተመዝጋቢ መሆን አለባቸው፡፡

7.7. በግንባታ ሥራዎች ልዩ አስተያየት የሚደረግላቸው በደረጃ 9 እና 10 የግንባታ ሥራዎችን በተሰጣቸው ፈቃድ ላይ ሆነው ሲወዳደሩ ብቻ ነው።

7.8. የሚወዳደሩበት ጨረታ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሽህ ብር) በላይ በሚሆንበት ጊዜ ልዩ አስተያየት ተጠቃሚነታቸው ቀርቶ እንደማንኛውም አቅራቢ የመወዳደር መብታቸው ብቻ የተጠበቀ ይሆናል።

## 25.1 የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በግዥ ላይ ለመሣተፍ ማሟላት የሚገባቸው ሠነዶች

1. በመንግስትም ሆነ በግል ድርጅቶች የተገኘ የሥራ ልምድ ማቅረብ የሚችሉ፣ ወይም
2. ከቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶች የተገኘ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፣ ወይም
3. ከአንድ ጊዜ በላይ በሚደረግ በጨረታ የመሳተፍ ሂደት ከመጀመሪያው ከግዥ ፈጻሚ አካላት ወይም ከአሰሪው የመልካም ሥራ አፈጻጸም ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ፣
4. በየደረጃው ከሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲዎች በጨረታ ወቅት ያሉበትን ሁኔታ የሚጠቅስ የድጋፍ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ ፣
5. የተሰጠን ፈቃድ ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት በውክልና አሳልፈው ያልሰጡ፣
6. የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ የሚሆኑት ከተቋቋሙ ጀምሮ ለ5 ዓመታት ብቻ ይሆናል። ግዥ ፈፃሚ አካላትም በሚያወዳድሩበት ጊዜ ከተቋቋሙ ስንት ዓመት እንደሆናቸው ከአደራጃቸው አካል መረጃ እንዲያመጡ ማድረግ አለበት።

## 25.2. በየደረጃው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲዎች በተቋማት ግዥ ተሳትፎ ስለሚኖራቸው ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ቅድሚያ ክፍያው ለተባለው ዓላማ መዋሉን የመከታተል፣
2. በተደረገላቸው ድጋፍ በቂ ካፒታል ወይም አቅም መፍጠር የቻሉትን ተቋማት በመከታተልና በመለየት ይደረግላቸው የነበረው ድጋፍ እንዲነሳ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የማሣወቅ ፣
3. በግዥ ፈጻሚው አካል እንዲሰጥ ለተፈቀደው የቅድሚያ ክፍያ መጠን የድጋፍ ደብዳቤ መፃፍ፣
4. ለተቋማቱ የተፈቀደውን የልዩ አስተያየት ድጋፍ የማያከብሩ የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች ሲያጋጥሙ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤቶች ማሳወቅ፣

5. ግገር ፈፃሚ አካላትም የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ተቋማት በሥራ አፈጻጸማቸው ችግር ሲፈጥሩ ከማስረጃ ጋር ፊታዱን ለሰጣቸው ለጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤትና ለቢሮው የማሣወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
6. ተቋማቱ ያለዋስትና የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ በውላቸው መሰረት በአግባብ ባለመፈፀማቸው ግገር ፈፃሚ አካላት ሲያሳውቁ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ፣
7. ከግገር ፈፃሚ አካላት ማስረጃ የቀረበባቸው የልዩ አስተያየቱ ተጠቃሚ ተቋማት በሌሎች ግገሮች እንዳይሣተፉ የሚደረጉ ሲሆን በሕግም ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

25.3. ተቋማቱን ከአቅራቢነታቸው ስለሚያሰርዙ ጥፋቶች

የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ከፈፀሙ ከአቅራቢነታቸው እንዲሰረዙ የሚደረግ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በህግም ተጠያቂ ይሆናሉ።

1. በቂ ምክንያት ሳይኖር በውል መሠረት ዕቃና አገልግሎት አለማቅረብ፣
2. ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ ያልጠበቀ ዕቃና አገልግሎት ማቅረብ፣
3. የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያው በውላቸው መሠረት አለማዋል፣
4. በመንግስት በኩል የሚደረጉ ድጋፎችን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ መሆኑ በበቂ መረጃ ሲረጋገጥ፣

# ክፍል ሰባት

# ሥልጣንና ኃላፊነት

## 26. ግዥ ፈፃሚ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች

### 26.1. የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ስልጣን እና ኃላፊነት

1. ከአቅራቢዎች በግዥ ዙሪያ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል። ይህም በክልል ደረጃ በደጋፊ የሥራ ሂደት ከታየ በኋላ በዚህ ውሳኔ የማይረካ አቅራቢ ከሂደቱ በላይ ላለ የተቋሙ መሪ፣ በዞንና ወረዳ በሥራ ሂደቱ ውሳኔ ያልረካ አቅራቢ ለዞኑ ገን/ ኢ/ል/መምሪያ፣ ለወረዳው ጽ/ቤትና ለከተማ አስተዳደሩ ገንዘብና አካባቢ ል/ጽ/ቤት በማቅረብ ውሳኔ ሊያገኝ ይችላል፣
2. መ/ቤቶች ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር እንደ የግብርና ቢሮ፣ የትምህርት ቢሮና የመሳሰሉት መ/ቤቶች በተለየ ሁኔታ ከመሣሪያዎችና ግብአቶች አቅርቦት ጋር የተያያዙ የግዥ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥ እንዲፈጽሙ ኃላፊነት ተሰጥቷል። በመሆኑም የመሥሪያ ቤት ኃላፊዎች እነዚህ የሥራ ሂደቶች

የሚያከናውኗቸው ግዥዎች የክልሉን የግዥ መመሪያ ተከትለው መፈጸም እንዳለባቸው ክትትል የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

3. የግዥ ጨረታን ገምግሞ የውሳኔ ኃሳብ የሚያቀርብ ከተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ እንደ መ/ቤቱ ስፋት ከ3-5 አባላት ኮሚቴ ያቋቁማል። ከነዚህም መካከል የኮሚቴ ሰብሳቢና ጸሐፊን ይሰይማል።

4. የገንዘብ መጠናቸው ከብር 100,000.00 /መቶ ሽህ ብር/ በላይ የሆኑ ግዥዎች በግዥ ጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴው ተረጋግጠው የሚቀርቡ የጨረታ ሀሳቦችን መርምሮ የማጽደቅ ኃላፊነት የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ነው፡፡

5. በክልል ደረጃ በፑል አገልግሎት ለሚያገኙ መ/ቤቶች ከብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሽህ ብር / በላይ የሆነ ግዥ የሚፀድቀው በእያንዳንዱ የፑል ተጠቃሚ መ/ቤት ኃላፊ ሲሆን በዞን፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ በገንዘብና ኢ/ል/ መምሪያ እና ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም እርሱ በወከለው ኃላፊ ይጸድቃል።

## 26.2. የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም ሌሎች ግዥ እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች ኃላፊነት

የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 27.1 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠቀሰው ግዥ እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደቶች የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል።

1. የጨረታውን ውጤት የጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች እና በጨረታው ተሳታፊ ለሆኑት ለሁሉም ተጫራቾች የተሸነፉበትን ምክንያት በመጥቀስ በእኩል ጊዜ በጽሁፍ የመግለጽ፣
2. በግዥ ሥራ ውስጥ በሚስጥርነት ሊጠበቅ የሚገባውን በተጫራቾች የቀረበውን መረጃ ለሌላ አካል አለመግለጽ፣
3. የአቅራቢዎችን የመወዳደሪያ ሃሣብ በጨረታ ሰነዱ አስቀድሞ በተዘጋጀው መስፈርት መሠረት ገምግሞ ውሣኔ የመስጠትና የውሳኔ ኃሳብ የማቅረብ፣
4. አግባብ ሆኖ ሲገኝ የሚከተሉትን እርምጃዎች የመውሰድ፣
   4.1 ከሚከተሉት ምክንያቶች በስተቀር ከተወሰነው ጊዜ በላይ ጨረታው እንዲራዘም ተጫራቾች የሚያቀርቡት ጥያቄ በበቂ ምክንያት ተደግፎ ሲቀርብ ከግዥ ጨረታን ገምጋሚ ኮሚቴ ጋር በመምከር ጨረታውን የማራዘም፡፡
      ሀ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.9 መሠረት ተጫራቾች የጨረታውን መወዳደሪያ ሠነድ ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ ያልነበራቸው መሆኑ ፣
      ለ/ ብሔራዊ በዓል ባልሆኑ ቀናት የመ/ቤቱ ሠራተኞች ያለመኖር ፣
      ሐ/ በታወቀ የመገናኛ ችግር ምክንያት ጨረታው ስለመውጣቱ ያለመስማት ፣
   4.2. በአሳማኝ ምክንያትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ የግዥ ጨረታን ገምጋሚ ኮሚቴ ጋር በመምከር በሚከተሉት ምክንያቶች ጨረታው እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል።

ሀ/ ተጫራቾች የግዥ አዋጁንና የዚህን መመሪያ አንቀፆች ወይም በጨረታው ሠነድ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ያላከበረ ከሆነ፣

ለ/ ቀደም ሲል በተሳተፈበት የመንግሥት ጨረታ የገባውን ግዴታ ያልፈፀመን ፣

ሐ/ የተጠየቀውን የጨረታ ማስከበሪያ ያላስያዘን ፣

መ/ የጨረታውን ሂደት ለማዛባት የሞከረ፣

ሠ/ የማጭበርበር ድርጊት የፈፀመን ማንኛውንም ተጫራች ከጨረታው ውጪ ማድረግ፣

5. የቀቅም ግጭት የማይፈጥር እስከ ሆነ ድረስ የማንኛውንም ጨረታ ቴክኒካዊ ሁኔታ ለመመርመር የቴክኒክ ባለሙያዎችን መጠቀም ይችላል። እነዚህ ባለሙያዎች ከሚከተሉት ማንኛውም ሊሆኑ ይችላሉ።

5.1. ጨረታውን ካወጣው የግዥ ፈጻሚ መ/ቤት፣

5.2. ሙያው ካላቸው ከሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች፣

5.3. በሚመረመሩት ጉዳዮች ልዩ ሙያ ያለው አማካሪ ወይም የግል ኩባንያ፣

6. እስከ ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ድረስ የሆነን የጨረታ ሂደት የማጽደቅ ኃላፊነት በግዥ ኦፊሰሮች ወይም ፈጻሚዎች ሲሆን በእነርሱ የጸደቁ ግዥዎችም ውል የሚይዘው ግዥውን ያጸደቀው የግዥ ኦፊሰር ወይም ፈጻሚ ይሆናል፤

7. ለጥናት የሚያስፈልጉን መሰረታዊ መረጃዎች ማለትም የዕቃውን ወይም የአገለግሎትን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መግለጽ እየቻለ መረጃውን ለመሥጠት ፈቃደኛ የማይሆን አቅራቢ ሲያጋጥም በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች አማካኝነት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው እንዲሁም በግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት እንዲደርስ ማድረግ አለባቸው፣

## 26.3. የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት / አስተባባሪ ወይም ግዥ እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደት ባለቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. እያንዳንዱ የሥራ ሂደት በዕቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም ወጪ ላደረገው ገንዘብ ተመጣጣኙን ዋጋ ማግኘቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

2. ከብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር / በላይ እስከ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሽህ ብር/ የሆኑ ግዥዎችን በግዥ ኦፊሰሮች ወይም ፈጻሚዎች የሚቀርብ የጨረታ ሀሳብን መርምሮ የማጽደቅ ስልጣን የግዥ፣ ፋይናንስና፣ ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ወይም ግዥ እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደት ባለቤት ይሆናል።

3. የገንዘብ መጠናቸው ከብር 100,000.00 /መቶ ሽህ ብር/ በላይ የሆኑ ግዥዎችን ይከታተላል፣ የበላይ ኃላፊውንም ያማክራል።

4. በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እና በግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ወይም ግዥ እንዲፈጽሙ በተፈቀደላቸው ሌሎች የሥራ ሂደት ባለቤቶች የጸደቁ ግዥዎችን ውል የሚይዘው የሥራ ሂደት ባለቤቱ ወይም አስተባባሪው ይሆናል።
5. የግንባታ ውልን በሚመለከት ውል የሚይዘው አሰሪው ሴክተር መ/ቤት ሲሆን ሥራው በውሉ መሰረት መሰራቱን የሚከታተለውና የሚያረጋግጠው በአሰሪው ሴክተር መ/ቤት ለዚህ ስራ የተመደበው የምህንድስና ባለሙያ ሲሆን ሴክተር መ/ቤቱ ባለሙያ ከሌለው በኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ባለሙያ ይሆናል። የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ክፍያውን ለመፈጸም እንዲያስችለው የውል ስምምነቱ ኮፒ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡ የሥራ ሂደቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አፈፃፀሙን በማጣራት ክፍያ ሊፈፅም ይችላል።
6. በውሉ መሠረት አገልግሎቱን ሳያጠናቅቅ የቀረን ወይም አሸናፊ መሆኑ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ ከ5 የሥራ ቀናት በኋላ የግዥ ውል ያልፈረመ እንዲሁም ከውል በመነጨ የዋስትና ግዴታውን ባልተወጣ አቅራቢ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ከማደረግም በተጨማሪ ለወደፊቱ መ/ቤቱ በሚያወጣው ጨረታ ላይ ለ1 ጊዜ እንዳይሳተፍ ማድረግ ይችላሉ። ይህንንም እርምጃ ለቢሮው ወይም ለዞንና ወረዳ ጽ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አቅራቢ በድጋሚ በሌላ መ/ቤት ተመሳሳይ ችግር ቢፈጥር በማንኛውም የመንግሥት ግዢዎች ላይ ለወደፊት እንዳይሣተፍ እስከማገድ የሚደርስ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ግዥ ፈጻሚ አካላት ጉዳዩን ከማስረጃ ጋር ለቢሮው፣ ለዞንና ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያና ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. በክልሉ ያሉ ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ አፈፃፀም ሪፖርትና መረጃ የቢሮው ግዥና ንብረት አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት በሚያዘጋጀው ቅፅ መሰረት በወቅቱ ሞልተው የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው።

### 26.4. የቢሮው የግዥና ንብረት አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነቶች

1. በመንግስት ግዥ መርሆዎችና አፈጻጸሞች ላይ በክልል፣በዞንና በወረዳ ለሚገኙ ግዥ ፈጻሚ አካላት የምክር አገልግሎት ይሰጣል ፣
2. የክልሉን የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረቂቅ አዋጅ ማዘጋጀት ይህም በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ የአዋጁ ማስፈጸሚያ የሆኑትን መመሪያዎችና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ በማስተቸትና ገንቢ አስተያየቶችን ተቀብሎ አዳብሮ የተሟላ አድርጎ በማውጣት ግዥ ፈጻሚ አካላት በሥራ ላይ እንዲያውሉት ያደርጋል ።
3. በየደረጃው ከሚገኙ ግዥ ፈጻሚ አካላትና ከአቅራቢዎች በግዥ መመሪያው ላይ አስተያየቶችን በማሰባሰብ መመሪያዎች ችግር ፈች መሆን እንዲችሉ አዳዲስ የማሻሻያ ኃሳቦችን በማካተት አዳብሮ የተሟላ አድርጎ በማውጣት ግዥ ፈጻሚ አካላት በሥራ ላይ እንዲያውሉት ማድረግ ፣

4. በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣ የግዥ አፈጻጸሙ በክልሉ የግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት መሆኑን ይከታተላል፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማለትም የስልጠናና የሙያ ድጋፍ ያደርጋል።

5. መደበኛ የጨረታ ሰነዶች፣ ለአሰራር የሚያግዙ ቅጾች እና ሌሎች ለግዥ አፈጻጸም አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች ማዘጋጀት፣ ሥራ ላይ እንዲውሉና ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

6. ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች ውጭ ማለትም መደበኛ ያልሆኑ የግዥ አፈጻጸም ጥያቄዎች ከግዥ ፈጻሚ አካላት ሲቀርቡ የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ አሳማኝ ምክንያቶች መቅረባቸውን ሲያምንበት ሊፈቅድ ይችላል።

7. በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ ፍላጐት ያላቸው አቅራቢዎች የሚመዘገቡበትን የተቀላጠፈ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገብ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ ይመዘግባል፣ የምዝገባውን ዝርዝር ያሰራጫል፣

8. ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል ወይም አቅራቢ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጁ እና ይህ መመሪያ ከሚፈቅደው ውጭ ትክክል ባልሆነ መንገድ ግዥ ስለመፈጸሙና ወይም በግዥ አፈጻጸም አካሄዱ ስለመመሳጠሩ ጥቆማ የቀረበ እንደሆነ ከግዥ አፈጻጸም ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣ ሠነዶችን፣ መዝገቦችና ሪፖርቶች እንዲቀርቡለት ሊያዝ ይችላል።

9. በግዥ አፈጻጸም ሂደት ዙሪያ ከአቅራቢዎችና ከግዥ ፈጻሚ አካላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ በዚህም ወቅት ቅሬታው ክብደት የሚሰጠው ከሆነ በአስቸኳይ ወደ ቦታው በመሄድ አጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

10. በክልል፣ በዞንና በወረዳዎች የሚገኙ ግዥ ፈጻሚ አካላት የግዥ አፈጻጸማቸውን የሚያሳይ ሪፖርትና መረጃ እንዲያቀርቡ ሊያዝ ይችላል፤

11. የግዥና ንብረት አስተዳደር ጉዳዮችን በሚመለከት በክልል፣ በዞን በወረዳና በከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የግዥ፣ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደቶች አሰራርና አደረጃጀትን ማጠናከር እንዲሁም የሙያና ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።

12. በውሉ መሰረት አገልግሎቱን ሳያጠናቅቅ የቀረን ወይም አሸናፊ መሆኑ ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ የግዥ ውል ያልፈረመ እንዲሁም ከውል በመነጨ የዋስትና ግዴታውን ባልተወጣ እንዲሁም በመንግስት ግዥ ላይ የማጭበርበር ተግባር የፈጸመን አቅራቢ እንደ ጥፋቱ ክብደት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ወይም ከ2 ዓመት ላላነሰ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊደርስ በሚችል ቅጣት በማንኛውም የመንግስት ግዥ ላይ እንዳይሳተፍ ሊያግድ ይችላል፡፡

13. ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ይከታተላል፣ ይፈጽማል፣ያስፈጽማል።

# ክፍል ስምንት

# የቴክኒክ ድጋፍ

## 27. ስለ ተሽከርካሪ የግዥ ሂደትና ስለሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ

1. የተሽከርካሪ ግዥ የሚፈፀመው የክልሉን የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና ይህን የግዥ መመሪያ መሠረት በማድረግ ይሆናል።
2. የተሽከርካሪ ግዥ የሚፈፀመው በክልሉ መንግሥት ሲወሰን በተጠቃለለ ሁኔታ ወይም ባለበጀት መ/ቤቶች ከተለያዩ ምንጮች በሚያገኙት በጀት በሚቀርብ የተናጠል ጥያቄ ሊሆን ይችላል፡፡ የመንግሥት የተሽከርካሪ ግዥ የሚፈፀመው በክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ይሆናል። ስለአፈጻጸሙ ዝርዝር መመሪያ በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ይወጣል፣
3. ከስራቸዉ ባህሪና ስፋት አንጻር ተሽከርካሪ ለማስተዳደር ራሱን የቻለ የስራ ሒደት በተደራጀባቸዉ የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አፈጻጸም ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም በሚያስገኝ መልኩ የተሽከርካሪ ግዢ በራሳቸዉ ሊፈጸም ይችላል፣ ይህን ለማከናወን የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣
4. የተሽከርካሪ ግዢ ጥያቄ በተናጠል ሲቀርብ የተጠቃለለ ግዢ ከሚኖረዉ የላቀ ጠቀሜታ አንጻር ከ20 ቀን ባልበለጠ ተቀራራቢና ተመሳሳይ ጊዜ ዉስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በማሰባሰብ በአንድ ላይ ግዢ የሚከናወን ሲሆን የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ የተሽከርካሪን ዝርዝር እና የግዥውን ጨረታ ሰነድ ያዘጋጃል፣ተጫራቾች እንዲወዳደሩ ይጋብዛል፣ የሚቀርቡ የመወዳደሪያ ሃሣቦችን ይገመግማል፣ የሚመለከተው ግዥ ፈጻሚ አካል ውሉን መፈፀም እንዲችል ለጨረታው አሸናፊና ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተዘጋጀውን ዝርዝር እና የመሸጫ ዋጋ ያሣውቃል፤ ግዥ ፈጻሚ አካሉም በተላለፈለት መሰረት ውሉን ይዋዋላል፤ የተሽከርካሪውን ዋጋ ይከፍላል፡፡
5. በመ/ቤቶች የተናጠል ጥያቄ ሳይሆን በተጠቃለለ ሁኔታ የተሽከርካሪ ግዢ በሚፈጸምበት ጊዜ የክልሉ ንግድና ትራንስፖርት ቢሮ አጠቃላይ የተሽከርካሪ ፍላጎት መረጃ ማሰባሰብ፣ ግዢን ማቀድና የግዢ ዘዴን መምረጥ የጨረታ ሠነድ ማዘጋጀት፣ የጨረታ ጥሪ ማድረግ፣ የመወዳደሪያ ሃሳቦችን ገምግሞ አሸናፊውን መለየትና ማሳወቅ፣ ከአሸናፊ አቅራቢዎች ጋር ውል መፈፀም ፣ የግዢ ሂደቱን መፈፀምና ማስፈፀም፣ ለተሽከርካሪ ግዥ የተያዘው በጀት መሠረት በማድረግ ክፍያውን ለአቅራቢው ድርጅት መፈፀም፣ ተሽከርካሪዎቹ አገር ውስጥ ሲገቡ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ ግዢው ለተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ማሠራጨት ተግባራትን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡
6. ግዥ እንዲፈጸምለት የሚፈልገው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ አስቸኳይ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት የተሽከርካሪው ግዥ መዘግየት በመ/ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን

ሲያምንበትና በሚፈለገዉ ጊዜና ሁኔታ በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ሊፈጸምለት እንደማይችል ሲያረጋግጥ ስለግዥው ከንግድና ትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠዉ ሃሣብና ፈቃድ መሰረት ግዢውን በራሱ ሊፈጽም ይችላል።

7. የተሽከርካሪ ጥገና በሚከተለው ሁኔታ ይፈፀማል።
   - 7.1. ተሽከርካሪዎችን ለማስጠገን በግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት የኮንትራት ጨረታ በማውጣት የጥገና ተቋማትን በማወዳደርና አሸናፊው ተቋም ጋር ውል በመያዝ ይከናወናል፤
   - 7.2. ለማወዳደሪያ የሚሆነውን የቴክኒካል ሠነድ (ስፔሲፊኬሽን) እና በውሉ ውስጥ መካተት የሚኖርባቸውን ቴክኒካል ጉዳዮችን የንግድና ትራንስፖርት ቢሮ አዘጋጅቶ ለግዥ ፈጻሚ አካላት የሚያስተላልፍ ሲሆን፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በግምገማ ወቅት አስፈላጊውን ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፣
   - 7.3. የመለዋዎጫ ግዥን በተመለከተ የመለዋወጫ ህጋዊ አቅራቢ የሆኑ አቅራቢዎችን በማወዳደር በኮንትራት በመያዝ ወይም በተናጠል ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡ ግዥው በአቅራቢውና የተሽከርካሪ እንክብካቤ ባለሙያ ወይንም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ባለሙያዎች በማረጋገጥ ይፈጸማል፡፡
   - 7.4. የተገዙ መለዋዎጫዎች በትክክል ስለመገጠማቸውና የጥገና ስራዉ ብቁ ስለመሆኑ በየደረጃው በሚገኙ የተሽከርካሪ እንክብካቤ ባለሙያ ወይንም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ ባለሙያዎች መረጋገጥ ይኖርበታል፣
   - 7.5. አሽከርካሪው ኃላፊነት ወስዶ ተሽከርካሪው በወቅቱ ተጠግኖ እንዲወጣ ግፊት ያደርጋል፣ ይከታተላል፤ በተጨማሪም ጥገናው ተፈጽሞ በባለሙያ ርክክብ ሲፈጸም ሪፖርት ያደረገው ችግር በትክክል የተቀረፈ መሆኑን አረጋግጦ ይረከባል።
   - 7.6. በጥገና አገልግሎት ግዥ ለሚነሱ ቅሬታዎች በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ተመርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።
   - 7.7. ዝርዝር የተሽከርካሪ ጥገናና የመኪና አስተዳደር መመሪያዎች በቢሮው እና በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ በጋራ ተዘጋጅተው ይወጣሉ።

## 28. ለግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ግዥ ለመፈጸም የሚደረግ ውድድርና ግምገማ

ግዥ ፈጻሚ አካላት የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን ግዥ ለመፈጸም በሚያደርጉት ሂደት ሊከተሏቸው ከሚገቡት መስፈርቶች መካከል የቴክኒክ ብቃት መመዘኛ አንዱ ነው፤ ስለሆነም

1. በግንባታው ዘርፍ ብቃት ያላቸውን ተጫራቾች ለመለየት በቴክኒክ መመዘኛ ወቅት አግባብነት ያለው መስፈርት በማዘጋጀት ውድድር ሊካሄድ ይገባል። የቴክኒክ መስፈርቶች ሲዘጋጁ (ሲቀመጡ) በግልጽና በማያሻማ መልኩ የመንግስትን ጥቅም የሚያስጠብቁ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት፤

2. በዚህ ውድድር ወቅት የጨረታ ሰነዱን የሚያዘጋጀው አካል ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልውን ደረጃ በመለየት /ከደረጃ አንድ እስከ አምስት/ እንደ ፕሮጄክቱ ይዘት ይመጥነዋል የሚባለው ዝርዝር የቴክኒክ መስፈርቶች ከ100% በመመዘን 70% እና ከዚያ በላይ ያመጡትን ተወዳዳሪዎችን ለቀጣይ የዋጋ ውድድር እንዲያልፉ መደረግ አለበት። ከደረጃ ስድስት እስከ አስር ያሉትን በተመለከተ ደረጃው የሚጠይቀውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መስፈርት ካሟሉ በቀጥታ በአቀረቡት ዋጋ ብቻ በማወዳደር አነስተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ ይሆናል፡፡
3. ይህ 70% እና ከዚያ በላይ የመጣ የቴክኒክ ነጥብ በዋጋ ላይ ለመወዳደር የሚያስችል ነጥብ እንጂ የዋጋ ውድድር ላይ የሚደመር አይደለም። ስለሆነም በቴክኒክ ማለፋቸው ከተረጋገጡ ተጫራቾች ወስጥ  በዋጋ ውድድር ወቅት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ተወዳዳሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል።
4. በጨረታው ወቅት ብቃት ያላቸውን ተጫራቾች ለመለየት በጨረታ ሠነዱ የሚካተቱ በማወዳደሪያነት በማስቀመጥ ለግምገማ የሚረዱ የቴክኒክ መስፈርቶችና ነጥቦች በኢንደስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ከተዘጋጀው ዝርዝር መመሪያ ስለሚገኝ መጠቀም ያስፈልጋል።

## 28.1. ለግንባታ ዘርፍ ውሎች ስለሚደረግ የቴክኒክ ድጋፍ

1. የክልሉ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና የዚህ መመሪያ አንቀፆች ለግንባታ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡
2. ከአሸናፊው ተቋራጭ ጋር የግንባታ ውል የሚይዘው አሰሪው መ/ቤት ይሆናል። ሆኖም ግን ተገቢውን ክትትል ለማድረግና ክፍያ ለመፈፀም የውሉ ኮፒ ክፍያ ለሚፈጽመው ለገ/ኢ/ል/መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ወይም ለከተማ አስተዳደር ገንዘብና አካባቢ ል/ጽ/ቤት ሊደርስ ይገባል።
3. በግዥ ፈጻሚ አካላት የሚከናወን የግንባታ ዘርፍ ሥራ በተገባው ውል መሠረት የጥራት ደረጃው፣ የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር የማድረግና በበላይነት የመቆጣጠር ኃላፊነት በየደረጃው የሚገኙ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ተዋረድ መ/ቤቶቹ ናቸው።
4. ጨረታውን የሚያወጣው የግንባታ ፕሮጀክት ባለቤት መ/ቤቶች የራሳቸው መሀንዲስ ወይም አማካሪ የሌላቸው ከሆነ ከጨረታው መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ፣ በጨረታ ሰነድ የቴክኒክ ግምገማ፣  የመሬት ዝግጅትና ከመሬት በታች የቦታው ሁኔታን፣ የግንባታው ደህንነት ክትትል እንዲሁም የመጨረሻ የሥራ ርክክብ ላይ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና በተዋረድ ያሉ መምሪያዎች ድጋፍ መጠየቅ አለበት፤
5. ማንኛውም የግንባታ መሐንዲስ ወይም አማካሪ ያለው መ/ቤት የህንፃ ግንባታ፣ የድልድይ አዲስም ሆነ ጥገና እንዲሁም የግንባታ ማስፋፊያ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት በራሱ ባለሙያ የሰራውን ወይም በአማካሪ ድርጅት ያሰራውን ዲዛይንና የሥራ ዝርዝር ለኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ተዋረድ መ/ቤቶች በማቅረብ በስታንዳርዱ መሰረት ስለመሰራቱ እንዲመረመርና እንዲፀድቅ

ማስደረግ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ የኢንደስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና በተዋረድ የሚገኙ መምሪያዎች ግዥ ፈጻሚዎች በሚያደርጉት የግንባታ ጨረታ ግምገማ ወቅት እና በግንባታ የመጨረሻ ርክክብ ወቅት መገኘት አለብን ብለው ካመኑ መገኘት ይችላሉ፡፡

6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው ቢኖርም የውኃና የመንገድ ግንባታ ስራዎችን በሚመለከት ዲዛይን የማዘጋጀት፣ የማጽደቅና ክትትል የማድረግ የውኃ ሀብት ልማት ቢሮና የክልሉ የገጠር መንገድ ባለስልጣን ኃላፊነት ነው።

7. በግንባታ ዘርፍ ሥራ ግዥ አፈጻጸም በሚነሱ ቅሬታዎች በየደረጃው በሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና አካላቱ የሚታዩ ይሆናል፡፡

8. የመንግስት የግንባታ ግዥ አካላት ያልተጠናቀቁና ርክክብ ያልተደረገባቸውን ግንባታዎች እንዲሁም አዲስ የግንባታ ውሎችን በሚይዙበት ጊዜ በአባሪ 6 እና 7 በተያያዘው ፎርም መሠረት በመሙላት በየደረጃው ላለ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ወይም መምሪያ ማሳወቅ አለባቸው።

## 28.2. የግንባታ ዘርፍ ሥራዎች ክፍያ የምስክር ወረቀት

1. ለግንባታ ዘርፍ ስራ ክፍያ የሚፈፀመው የስራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሐንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ ይሆናል።
2. አማካሪ መሐንዲሱ የክፍያ ምስክር ወረቀት ከሥራ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ በቀረበለት በ7 (ሰባት) ቀናት ውስጥ የምርመራውን ሥራ ማጠናቀቅ ይኖርበታል ።
3. የክፍያ ምስክር ወረቀት በአማካሪ መሐንዲሱ ተረጋግጦ በቀረበ በ7 (በሰባት) ቀናት ውስጥ የመንግስት መ/ቤቱ ተገቢውን ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ መፈፀም አለበት ።
4. በአንድ የግንባታ ፕሮጀክት ውል መሰረት ከተያዘውና በስምምነት ከተደረሰበት ውጭ የለውጥ ሥራ /Variation/ ለሚጠይቅ የገንዘብና የጊዜ መጠን ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና በተዋረድ ባሉ መምሪያዎች ሲታመንበት ከአሰሪው መ/ቤት ጋር በመመካከር እስከ 10% የለዉጥ ሥራ ውል ከአሰሪው መ/ቤት ጋር በቅድሚያ ውል ተይዞ ክፍያ ሊፈጸም ይችላል። የለዉጥ ስራዉ ከ10% በላይ ከሆነ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና ተዋረድ መ/ቤቶቹ ጋር በመመካከር በጋራ ሲታመንበት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተውን ተግባራዊ ለማድረግ ፤
   5.1. ግዥ ፈጻሚው አካል በተጨማሪነት እንዲሰሩ የታሰቡት ስራዎች በመጀመሪያው ውል ውስጥ መካተት ይገባቸው የነበሩ እና ስራዎቹን ነጣጥሎ ማሰራት ለአፈፃፀም አስቸጋሪ ወይም የመ/ቤቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፣
   5.2. በተጨማሪነት የሚታዘዙት የግንባታ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ሊገኝ የሚችል ከሆነ የተጨማሪው ስራ በመጀመሪያው ውል ውስጥ ባለው ነጠላ ዋጋ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን የነጠላ ዋጋው በመጀመሪያው ውል ውስጥ የማይገኝ ከሆነ

በድርድር ስምምነት ላይ የሚደረስበት ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን መ/ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

6. አማካሪ ማሐንዲሱ የክፍያ ምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ከቀረበለት በኋላ ያለበቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው ጊዜ ያሳለፈ እንደሆነ በመዘግየቱ ምክንያት ተቋራጩ በግዥ ፈጻሚው አካል ላይ ለሚያቀርበው ማንኛውም ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ አማካሪ ማሐንዲሱ ኃላፊነት ይኖርበታል። ሆኖም የአማካሪ ማሐንዲሱ ኃላፊነት ለአገልግሎቱ ከሚከፈለው ዋጋ ሊበልጥ አይችልም።

7. ግዥ ፈጻሚው አካል ያለበቂ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በአማካሪ መሐንዲሱ በቀረበለት ማረጋገጫ መሠረት ክፍያ ባይፈጽም ተቋራጩ በውሉ መሠረት ለሚያቀርበው ተጨማሪ የክፍያ ጥያቄ ኃላፊነት ይኖረዋል ።

8. ለማናቸውም የግንባታ ዘርፍ ሥራ በክፍያ ምስክር ወረቀት መሠረት ከሚፈጸመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለሥራ ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% (አምስት በመቶ) እየተቀነሰ በመያዣ መልክ (Retention) ጊዜያዊ ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ አንስቶ ለአንድ አመት ተይዞ ይቆያል። የመጨረሻ ርክክብ ላይ የግንባታው ደህንነት ተረጋግጦ ለተቋራጩ የሚሰጥ ይሆናል።

# ክፍል ዘጠኝ

# የውል አስተዳደር

## 29. ውልን ተፈፃሚ ስለማድረግ

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ የግዥ አፈጻጸሙን ውጤታማ ለማድረግ ሲባል ግዥውን በውሉ መሠረት ተፈጻሚ ለማድረግ የተጠናከረ ክትትል ማድረግ አለባቸው። አፈጻጸሙም በሚከተለው ሁኔታ መሆን አለበት፤

1.1. ግዥ ፈጻሚ አካላት የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የውል ስምምነቶች በፍጥነት ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

1 .2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1.1 የሰፈረውን ተግባራዊ ለማድረግ ውሉ እንደሚያስቀምጠው ቅድመ ሁኔታ ግዥ ፈጻሚው አካል የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ይኖርበታል።

ሀ/ ውሉ ቅድሚያ ክፍያ እንዲፈፀም የሚያዝ ከሆነ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና አቅራቢው እንዲያስይዝ በማድረግ የቅድሚያ ክፍያውን በአስቸኳይ መክፈል፣

ለ/ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ሊከፈትላቸው ለሚገባ ግዥዎች ተገቢው ፎርማሊቲ መሟላቱን በማረጋገጥ ሌተር ኦፍ ክሬዲቱን በፍጥነት መክፈት፣

ሐ/ ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያግዙ በግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ ከላይ በፊደል ሀ እና ለ ከተቀመጡት በተጨማሪ በመሥሪያ ቤቱ ሊፈፀሙ የሚገባ ተግባራትን በውሉ መሰረት ማከናወን

1.3. ግዥ ፈጻሚ አካላት ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ በአቅራቢው ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመለየት አቅራቢው በውሉ መሰረት ተግባራቱን በወቅቱ መፈፀሙን ተከታትለው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

1.4. ግዥ ፈጻሚ አካላት የውሉ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው ውሉ ተፈፃሚ መሆን የጀመረበትን ቀን መዝግበው መያዝ እና እንደ አስፈላጊነቱም አቅራቢው እንዲያውቀው ማድረግ ይኖርባቸዋል

## 30. የውል አፈፃፀምን መከታተል

1. የውል አፈፃፀምን የሚከታተለው ግዥ ፈጻሚው አካል አቅራቢው በውሉ መሰረት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት በውሉ ላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ የሚገኙ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል።

2. ግዥ ፈጻሚው አካል በውል ስምምነቱ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የውል አስተዳደር ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል:-

   2.1. ተከታታይ ክፍያዎችን በወቅቱ በመፈፀም፣

   2.2. አቅራቢው የውል ግዴታውን እየተወጣ እንደሚገኝ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በወቅቱ በመስጠት፣

   2.3. አቅራቢው የውል ግዴታውን መወጣት እንዲችል ሕጋዊ የሆነ እገዛ ማድረግ፣

3. በውል አፈፃፀም ወቅት እንደ ሁኔታው የውል ማሻሻያ ማድረግ የሚቻል ሲሆን የሚደረገው የውል ማሻሻያም የግዥ ፈጻሚውን አካል ጥቅም የሚጎዳ እና በጨረታው ከተወዳደሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች አንፃር ለአቅራቢው የተለየ ጥቅም የሚያሰጥ መሆን የለበትም፡፡

4. በውል አፈፃፀም ክትትል ወቅት ግዥ ፈጻሚ አካላት በተለይ የሚከተሉትን መፈፀም አለባቸው።

   4.1. ሌተር ኦፍ ክሬዲት የውል ስምምነቱን ሁኔታዎች ጠብቆ በወቅቱ መክፈት፣

   4.2. ተቀባይነት የሚኖራቸውን የሌተር ኦፍ ክሬዲት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀብሎ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፣

   4.3. ተገቢው አገልግሎት ከመገኘቱ በፊት የውል ማስከበሪያ፣ የሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የዋራንቲ መጠቀሚያ ጊዜዎች እንዳያልፉ ጥንቃቄ እና ክትትል ማድረግ፣

   4.4. የግንባታ ስራዎች በተያዘላቸው ጊዜ ገደብ ውስጥ መገንባታቸውን፣ የዕቃ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች በውሉ ጊዜ ውስጥ መከናወናቸውን ክትትል መደረጉን እና ሪፖርት መቅረቡን መከታተል፣

4.5. ግዥ ፈጻሚው አካል ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ምንም ዓይነት የይገባኛል ጥያቄዎች እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

5. ግዥ ፈጻሚ አካላት በውል አፈፃፀም ወቅት ከሦስተኛ ወገን የሚገኙ አገልግሎቶችን መለየት እና አገልግሎቶቹ የውል አፈፃፀሙን በሚያግዝ መልኩ መሰጠታቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

## 31. ውል ማጠናቀቅ

ግዥ ፈጻሚ አካላት ከአቅራቢዎች ጋር የተፈረሙ ውሎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ተገቢውን ዕልባት በወቅቱ አግኝተው ውል መዘጋቱን ማረጋገጥ አለባቸው፣ ለዚህም

1. አቅራቢው በውል ስምምነቱ መሰረት የሚገባውን የግንባታ ዘርፍ ስራ፤ ዕቃ፤ የምክር ወይንም ሌሎች አገልግሎቶች ማቅረቡን ማረጋገጥ
2. በውሉ መሰረት የተያዙ ዋስትናዎች ፤ ዋራንቲዎች ተገቢው ክትትል የተደረገባቸው እና አስፈላጊ በሆነ ወቅት ወሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን
3. በውሉ መሰረት ለአቅራቢዎች ሊከፈል የሚገባ ክፍያ የተጠናቀቀ መሆኑን ለተከፈሉ ክፍያዎች ሁሉ በውሉ መሰረት አገልግሎት መገኘቱን
4. ከሶስተኛ ወገን ማለትም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች፤ ከአጓጓዦች፤ ከጉምሩክ ባለስልጣን፤ ከጉምሩክ አስተላላፊዎች፤ ከባንክ እና ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የተያያዙ ግዥ ፈጻሚው አካል ጥቅሞች መከበራቸውን እና የግዥ ፈጻሚውን አካል ግዴታዎች የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ፣
5. ግዥ ፈጻሚው አካል ከአቅራቢው እና ከሦስተኛ ወገን ጋር ያሉ ያልተጠናቀቁ ሒሳቦችን በመዝጋት እንደአስፈላጊነቱ የውል አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አስር

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 32. መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን መመርመር፣

1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ማለትም የግዥ፣ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት ወይም ሌሎች ግዥ እንዲፈጽሙ የተፈቀደላቸው የሥራ ሂደቶች በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻጸም ስርዓቶች ሊጠበቅ ያልቻለ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 8 በፊደል ሀ ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት ለቢሮው እና በተዋረድ ላሉ መምሪያና ጽ/ቤቶች እንዲሁም የከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ጥያቄያቸውን አቅርበው ሲፈቅድላቸው ብቻ ነው፡፡ ሆኖም በዞን፣ በወረዳ እና የከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ጥል ደረጃ

ጥያቄዎችን መርምሮ ማፅደቅ ያለበት ከጠያቂው የሥራ ሂደት ባለቤት ወይም አስተባባሪ ወጭ ባለት የማኔጅመንት ኮሚቴ የጋራ ውሳኔ ይሆናል።

2. ግዥ ፈጻሚ አካላት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 በተገለጸው መሠረት ለሚያቀርቡት የልዩ ፈቃድ ጥያቄ የወሰዱት አማራጭ ከወጪ፣ ከጥራት፣ ከጊዜ እና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በተያየዘ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ያካተተ መግለጫ አግባብ ካላቸው ደጋፊ ሰነዶች ጋር ለቢሮ ወይንም ጥያቄው ለሚቀርብለት በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤቶች ወይም የከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ማቅረብ አለባቸው። ይህም፣
   - 2.1 ለመጠቀም እንዲፈቀድላቸው የሚያቀርቡት የግዥ ዘዴ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለፁትን የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች /መስፈርቶች/ ያላሟላ ሲሆን፣
   - 2.2 በመመሪያው የተቀመጡትን የጨረታ ደንቦች ሊጠብቅ ያልቻለን ማንኛውንም የግዥ አፈፃፀም፣
   - 2.3 ከፍተኛ ነጥብ ላመጣው ተጫራች ሳይሆን ግዥው ለሌላ አቅራቢ መሥጠት ሲያስፈልግ ነው፣
3. በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የገንዘብና ኢ/ል/መምሪያዎችና ጽ/ቤት እንዲሁም የከተማ የገንዘብና አካባቢ ኢኮኖሚ ልማተ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በተይዩ ካሉ ከሌሎች ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች /ለምሳሌ ከክልል ተጠሪ መ/ቤቶችና ተቋማት/ የሚቀርቡላቸውን መደበኛ ያልሆኑ የግዥ ሂደቶችን በመመርመር የሚያሳምኑ ሁኔታዎች መኖራቸውን በጥልቀት በማጤን ከማኔጅመንት ጋር በመሆን ውሳኔ ይሰጣሉ።

## 33. የግዥ ሰነዶች

1. ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 11 የተዘረዘሩትን እና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የግዥ ሰነዶች ይዘው ማቆየት ይኖርባቸዋል::
2. የግዥ ሰነዶች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ ላይ ለፋይናንስ ሰነዶች የቆይታ ጊዜ ከሚገለፀው እኩል የቆይታ ጊዜ ይኖራቸዋል::

## 34. የአቅራቢዎች ምዝገባ እና በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

### 34.1. የአቅራቢዎች ምዝገባ

1. የአቅራቢዎችን ዝርዝር በመረጃነት የመያዝ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።
   - 1.1. ግዥ ፈጻሚ አካላት ተገቢ የሆኑ አቅራቢዎችን በአፋጣኝ እንዲለዩ ለማስቻል፣

1.2. ብቃት ያላቸውን አቅራቢዎች በመምረጥ ረገድ የሚደረገውን ማጣራት ለማጠናከር፣

1.3. ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተመጣጣኙን ለማስገኘት እንዲቻል ከአቅራቢዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራርን ለመተግበር እንዲቻል፤

1.4. በግዥ ሥርዓት አፈጻጸም ግድፈት የፈጸሙ አቅራቢዎችን መዝግቦ ለማሳወቅ፣

2. በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ በመሆኑ

2.1 በመንግሥት ግዥ መሳተፍ የሚፈልጉ አቅራቢዎች ቢሮው ባዘጋጀው ድህረ ገጽ በቅድሚያ ራሳቸውን መመዝገብ ወይም በግንባር ቀርበው መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣

2.2 ከላይ በንዑስ አንቀጽ "2.1" ላይ የተገለጸው ቢኖርም በሪል ስቴት ያልተሠማሩ የቤት አከራዮች በአቅራቢዎች ዝርዝር ባይመዘገቡም ለቤት ኪራይ በወጣ ጨረታ መሳተፍ ይችላሉ፣

34.2. በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1. አቅራቢው የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልፅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣
2. የምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ ስለተሰማራበት የሙያ ዘርፍ በሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣
3. በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሥራ ተቋራጭነት ሥራ እንዲሠራ በክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮና ሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት የተሠጠውን ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ፣
4. የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ ከንግድና ትራንስፖርት ቢሮ የተሠጠ ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ፣
5. መድሐኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንና ሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት የተሠጠውን ማስረጃ ማሟላት አለባቸው።

# ክፍል አስራ አንድ

## በግዥ ሥርዓት ስለሚጠበቅ ሥነ-ምግባር፣ ዉይይት እና አቤቱታ

## 35. ከግዥ ባለሙያ የሚጠበቅ ሙያዊ ስነ-ምግባር

በአዋጁ አንቀጽ 9.1. ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ከመንግስት ግዥ አፈጻጸም ጋር ግንኙነት ያለው ሠራተኛ ወይም ሃላፊ ተግባሩን በተሟላ የሙያ ሥነ ምግባር መፈጸም ይኖርበታል:: ለዚህም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

1. በመንግስት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተገናኘ የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም መልኩ ራሱን ወይም ቤተሰቡን ሊጠቅም የሚችል መሆኑን ሲረዳ ከሥራው ጋር የተገናኘ የጥቅም ግጭት መኖሩን በጽሑፍ በማሳወቅ ከግዥ ሂደቱ ሥራ ራሱን ማግለል ይኖርበታል::

2. ግዥ ፈጻሚው አካል ከማንኛውም ምንጭ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ የተሳተፈ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከሚሰራው ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ሲደርሰው፣

   2.1. ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በቀረበው የጥቅም ግጭት ጉዳይ ላይ አስተያየቱን በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

   2.2. ከላይ በተ.ቁጥር 2.1 በተሰጠው የጽሑፍ አስተያየት እና ተገቢ ነው ብሎ ባመነባቸው መንገዶች ተጨማሪ መረጃ በማሰባሰብ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከያዘው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት እንዳለው ወይም እንደሌለው ይወስናል::

   2.3. ከላይ በተ.ቁጥር 2.2 ላይ በተቀመጠው መሠረት የግዥ ፈጻሚው አካል ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ከሚሰራው የግዥ ሥራ ጋር በተያያዘ የጥቅም ግጭት መኖሩን ሲያረጋግጥ፤

      ሀ/ ሠራተኛውን ወይም ኃላፊውን ከሂደቱ እንዲገለል ያደርጋል::

      ለ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው በሂደቱ ተሳትፎባቸው ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደገና እንዲታዩ ያደርጋል::

      ሐ/ ሠራተኛው ወይም ኃላፊው የጥቅም ግጭቱን ያላሳወቀው ከግንዛቤ ጉድለት ነው ብሎ ካላመነ በስተቀር በሠራተኛው ወይም በኃላፊው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል::

3 በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚሳተፍ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች እኩል የመወዳደርና ውል የመፈፀም ዕድል እንዳያገኙ የሚያደርግ ማንኛውንም ተግባር መፈፀም የለበትም:: ለዚህም፣

   3.1 በጨረታ ጥሪ ሁሉም ዕጩ ተወዳዳሪዎች በቂ መረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ የሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ በጨረታው ለመሳተፍ እና ተመራጭነት ሊያገኝ የሚችል የመጫረቻ ሰነድ ለማዘጋጀት የሚያስችል የተሟላ እና ግልፅ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ፣

   3.2 በጨረታ ሰነዱ የተገለጸው ማንኛውም የመወዳደሪያ መስፈርትም ሆነ የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር የተወሰነ ዕጩ ተወዳዳሪን ሊጠቅም በሚችል መልኩ አለመዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

   3.3. የጨረታው ውጤት ለሁሉም ተሳታፊዎች መገለጹን ማረጋገጥ፣

   3.4 በኮንትራት ሰነድ ዝግጅት ለአቅራቢዎች የሚሰጠው ኃላፊነት ግዴታቸውን ሆነ ብሎ ለማቅለል ወይም ለማክበድ ያላለመ እና እስከተቻለ ድረስ ተመሳሳይ ውል ለሚፈርሙ አቅራቢዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው ውል ሆኖ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

   3.5 በውል አፈጻጸም ወቅት ክፍያን፣ ቁጥጥርን፣ የመረጃ ልውውጥን እና የመሳሰሉት ተግባራት በእኩልነት ለሁሉም አቅራቢዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

4. በመንግሥት ግዥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞች እና ኃላፊዎች በግዥ ሥራቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ወይም ሊያሳድር የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ

ከሦስተኛ ወገን መቀበል የለባቸውም። ለዚህ ንዑስ አንቀፅ አፈፃፀምም የመንግሥት ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

4.1. የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ በተለይ ለመንግሥት መ/ቤቱ ዕጩ አቅራቢ ከሆነ ድርጅት አለመቀበል፣

4.2. የሥራ ዕድል ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አለመቀበል፣

4.3. በግል በሚደረግ ግዥ ላይ ለመ/ቤቱ ዕጩ አቅራቢ ከሆነ ድርጅት የተለየ የዋጋ ቅናሽ ወይም አገልግሎት አለመቀበል፣

4.4. በሥራው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል የግብዣ ፕሮግራም አለመቀበል፣ ሆኖም ጉዞን ያላካተተ እና ጋባዡ ከመ/ቤቱ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ጋር የማይገናኝ ግብዣ ሲሆን ሊቀበል ይችላል።

4.5. ከላይ በንዑስ ቁጥር 4.1 ላይ የተቀመጠው ቢኖርም ሠራተኛው ወይም ኃላፊው ዕጩ አቅራቢው ለማስታወቂያነት አገልግሎት የሚያዘጋጃቸው የውስጥ እሴት እንጂ የገበያ ዋጋ የሌላቸው በነጻ የሚታደሉ ስጦታዎችን መቀበል ይችላል።

5. የመ/ቤት ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስራ አጋጣሚ የተመለከታቸውን የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የታሰቡ የሙስና ተግባራትን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ የሚኖርበት ሲሆን ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸምም፣

5.1 የሚያደርገው ጥቆማ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ፣

5.2 እራሱን የታሰበውን የሙስና ተግባር ሊደግፍ ከሚችል ማንኛውም ተግባር መጠበቅ ይኖርበታል።

6. የመ/ቤቱ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ከግዥ ሥራ ጋር በተገናኘ ያወቃቸውን የባለ በጀት መ/ቤቱን ወይም የዕጩ ተወዳዳሪውን ወይም የአቅራቢውን ሚስጥራዊ መረጃ መጠበቅ ይኖርበታል። ለዚህም፣

6.1 ውድድርን ሊገድብ የሚችል ወይም ለተወዳዳሪዎች ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም የሚያስገኝ ወይም የመ/ቤቱን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መረጃ በልዩ ሁኔታ በመ/ቤቱ ኃላፊዎች ካልተፈቀደ ለማንኛውም አካል አለመስጠት፣

6.2 ግዥ ፈጻሚው አካል በውል አፈጻጸም ወቅት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የመ/ቤቱን ውሳኔ እና መረጃ መጠበቅ፣

6.3 የዕጩ ተወዳዳሪዎችን መረጃ እና የግምገማ ሂደት ውጤቱ በመ/ቤቱ ከመገለጹ በፊት ለማንኛውም አካል አለማሳወቅ፣

## 36. በመንግስት ግዥ ከሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚጠበቅ ሥነ ምግባር፣

በመንግሥት ግዥ የሚሳተፉ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥነ-ምግባር መርሆዎች መከተል አለባቸው:-

1. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ በመንግሥት ግዥ ሥራ ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ለተሰማራ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ራሱ ወይም በሦስተኛ ወገን በኩል ስጦታ መስጠት የለበትም።

2. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አቅራቢ የመንግሥት መ/ቤቱ በግዥ አፈጻጸም ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ለሚወስደው ውሳኔ የሚረዳ ዕጩ ተወዳዳሪው ወይም አቅራቢው የሚያውቀውን መረጃ ለመንግሥት መ/ቤቱ መግለጽ አለበት።
3. ግዥ ፈጻሚው አካል በሚያደርገው የግዥ አፈጻጸም በመስኩ ከተሰማራ ሌላ ተወዳዳሪ ጋር በመነጋገር ዋጋ መስጠት ወይም ላለመስጠት፣ መ/ቤቱን ሊጎዳ የሚችል መረጃ መለዋወጥ ወይም በግዥ አፈጻጸሙ ለመሳተፍ የሌላ ተወዳዳሪን ሰነድ ወይም መረጃ መጠቀም የለበትም።
4. በመንግሥት ግዥ አፈጻጸም የተመለከተውን የሙስና ተግባር ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ እና የሙስና ተግባሩ ተባባሪ ሆኖ መገኘት የለበትም።

## 37. ከተጫራቾች ጋር ስለሚደረግ ውይይት

1. በግዥ ሂደት በማናቸውም ደረጃ ከአቅራቢዎች ጋር ውይይት ሊደረግ የሚችለው የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ይሆናል፡፡ በግዥ ፈጻሚ አካላትና በአቅራቢዎች መካከል የሚደረጉ ውይይቶች በሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሆናሉ፡፡ እነዚህም ፣
   1.1. በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ወይም፣
   1.2. በሁለት ደረጃ ጨረታ በሚሆንበት ጊዜ ጨረታው በሚያካትታቸው የግዥ ዓይነቶች ላይ ድርድር ለማድረግ፣
2. በጨረታው ሰነድ ላይ በግልጽ ስላልተመለከቱ ጉዳዮች ግዥ ፈጻሚ አካላት ማብራሪያ መስጠት አለባቸው፡፡ አቅራቢዎች የተፈለጉትን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች መረዳት በሚያስቸግራቸው ጊዜ ጨረታውን ያወጣው መ/ቤት ግልጽ ሊያደርግለት ይችላል፡፡ ጨረታውን ያወጣው መ/ቤት በጨረታው የተሣተፉ አቅራቢዎች ሁሉ ተጨማሪው መረጃ በትክክል እንዲደርሳቸው ማድረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተፈቀደው መሠረት ካልሆነ በስተቀር
   3.1 ጨረታው ከተዘጋ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ላይ ለውጥ እንዲያደርጉ መጠየቅ ወይም መፍቀድ አይቻልም፡፡
   3.2 ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የመወዳደሪያ ሃሣብን ለመገምገም በሚያስችሉ ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ከመጠየቅ በስተቀር ተጫራቶች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሣብ ውስጥ ዋጋውን ወይም ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለውጡ መጠየቅ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡
   3.3 ስለጨረታው የሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄም ሆነ ለጥያቄው የሚሰጥ መልስ በሁሉም ተጫራቾች እንዲታወቅ ሆኖ በፅሁፍ መሆን አለበት፡፡
4. በጨረታው አሸናፊ የመወዳደሪያ ሃሣብ ውስጥ የቀረበው ዋጋ ጨረታው ከመውጣቱ በፊት በመ/ቤቱ ከተገመተው ወጪ በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ከሆነ ግዥ ፈጻሚው አካል ወጪው ከታሰበው በላይ የሆነበትን ምክንያት ማጣራት እና አዲስ የጨረታ ማስታወቂያ ማውጣት

ያስፈልግ እንደሆነ መመርመር አለበት፡፡ ከዚህ በላይ ከተደነገገው በአማራጭ ጨረታውን ያወጣው መ/ቤት የተሻለ ዋጋ ለማግኘት የሥራውን ሥፋት በመቀነስ እና ወይም ተጫራቹ በውሉ መሠረት ያለበትን ኃላፊነት በማሻሻል ከአሸናፊው ተጫራች ጋር ድርድር ማድረግ ይችላል፡፡ ሆኖም የሥራውን ሥፋት በመቀነስ ወይም የውሉን ሰነድ በማሻሻል የሚደረግ ማስተካከል የሚፈፀመውን ግዥ ወይም አገልግሎት ወይም ግንባታ የተሟላ እንዳይሆን የሚያደርገው ከሆነ ጨረታውን በመሠረዝ አዲስ ጨረታ መውጣት አለበት፡፡

5. ግዥ፣ ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር የዞን፣ የከተማ አስተዳደርና የወረዳዎች ሥራ ሂደት ከተጫራቾች ጋር የሚደረገውን ውይይት ቃለ ጉባኤ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 38. የዕጩ 38. የዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም አቅራቢዎች አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል በዚህ መመሪያ የተመለከተውን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ምክንያት ጉዳት ወይም ኪሣራ ደርሶብኛል ወይም ሊደርስብኝ ይችላል የሚል ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ከዚህ በታች በተመለከቱ ምክንያቶች ግን አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም።
    - 2.1. በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጁ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ በተወሰነው የግዢ ዘዴ ምርጫ ላይ፣
    - 2.2. በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 13 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13.16 መሰረት ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች፣ ምርቶችና እና የግንባታ ዘርፍ ስራዎች በተሰጠ ልዩ አስተያየት፣
    - 2.3. በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ጨረታን፣ የመጫረቻ ሰነድን ወይም የዋጋ ማቅረቢያን ውድቅ ለማድረግ በተሰጠ ውሳኔ፣
    - 2.4. መስሪያ ቤቱ የግምገማውን ውጤት ወይም ለቀረበለት አቤቱታ ውሳኔ በጽሁፍ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 /አምስት/ የስራ ቀን ካለፈ::
    - 2.6 በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጠው የቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎ በተቀመጠው የመፈራረሚያ ጊዜ መሰረት ውል ከተፈረመ አቤቱታ ማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ናቸው።
3. እጩ ተወዳዳሪው ወይም ተጫራቹ አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት ሲያቀርብ ለመሥሪያ ቤቱ ያቀረበውን አቤቱታ የሚያሳይ ደብዳቤ፣ በመንግስት መስሪያ ቤት ለአቤቱታው ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ የውሳኔውን ቅጂ፣ የአቤቱታውን ጭብጥና፣ ተያያዥ ማስረጃዎችን በአባሪነት ማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል።

## 39. አቤቱታ ስለሚመረመርበት ሁኔታ

1. በጨረታ ግምገማ ውጤት ቅር የተሰኘ ማናቸውም ተጫራች ውጤቱ በተገለፀበት በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ጨረታውን ላወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ሊያቀርብ

ይችላል፡፡ አቤቱታ የቀረበበት መ/ቤትም ምላሹን በቀረበለት በ4 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው መልስ መስጠት አለበት፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች የቴክኒክና የዋጋ የመጫረቻ ሰነዳቸውን በተለያየ ሁለት ኤንቬሎፕ እንዲያቀርቡ በተደረገበት ጨረታ፣

2.1. ማንኛውም ተጫራች የቴክኒክ ግምገማው አፈፃፀም የግዥ አዋጁን፣ የአፈፃፀም መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን መሠረት አድርጎ አልተከናወነም የሚል ቅሬታ ካለው፣ ቅሬታውን በ4 የሥራ ቀን ውስጥ ማቅረብ እንደሚችል የመንግሥት መ/ቤቱ የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾች በሚያሳውቅበት ደብዳቤ ላይ ማመልከት ይኖርበታል።

2.2. የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የተሰጠው ውሳኔ የግዥ አዋጁን፣ መመሪያውን እና የጨረታ ሰነዱን የጠበቀ አለመሆኑን ማረጋገጥ የሚችል ተጫራች የኃላፊውን ውሳኔ ባወቀ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት ሊያቀርብ ይችላል።

2.3. የመንግሥት መ/ቤቱ የዋጋ መወዳደሪያ ኃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሊከፍት የሚችለው የቴክኒክ ግምገማ ውጤቱን ለተጫራቾቹ ካሳወቀ 4 ቀናት በኋላ ይሆናል። ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን በሚመለከት ለቀረበው አቤቱታ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት በተገቢው ጊዜ ውስጥ በየደረጃው ለሚገኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት አቤቱታ የቀረበ ከሆነ መ/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዋጋ መወዳደሪያ ኃሳብ የያዘውን ኤንቨሎፕ ሳይከፍት እንደታሸገ ማቆየት ይኖርበታል።

2.4. አቤቱታ የቀረበበት ማናቸውም ግዥ የሚጣራው ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ፣ አዋጅና መመሪያ መሠረት በማድረግ ብቻ ይሆናል።

3. የግገር ፈፃሚው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በሰጠው ምላሽ ያልረካ አቤቱታ አቅራቢ ለሚከተሉት በማቅረብ ውሳኔ ሊያሰጥ ይችላል።

3.1. በክልል ደረጃ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣

3.2. በዞኑ ገንዘብና ኢ/ ልማት መምሪያ መልስ ያልረካ አቅራቢ ቅሬታውን ለክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ

3.3. በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ በሚገኙ ገንዘብና ኢኮኖሚ (አካባቢ) ልማት (ጽ/ቤት) በተሰጠው ምላሽ ያልረካ አቅራቢ ቅሬታውን ለዞኑ ገ/ኢ/ል/መምሪያ ማቅረብ ይችላል፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከተውን ተፈፃሚ ለማድረግ እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ዞን ገ/ኢ/ል መምሪያ/ጽ/ቤት የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖራቸዋል።

4.1. ማንኛውም ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ተጫራች ወይም ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ህግ ከሚያዘው ውጭ ስለመፈጸሙ ወይም ግዥ በትክክል ስላለማከናወኑ ወይም የግዥውን አመራር በትክክል ስላለመፈጸሙ ወይም የጥቅም ግጭት ወይም የሙስና ተግባር ስለመፈጸሙ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ከግዥው ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ ሰነዶች፣ መዝገቦችና መግለጫዎች ከመንግሥት መ/ቤቱ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪው እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣

4.2. በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ግዥ ፈጻሚው አካል ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁፍ ማስታወቂያ መላክ፣

4.3. የቀረበው አቤቱታ በቢሮው ወይም በሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝር የቴክኒክ ምርመራ ተደርጎበት ሪፖርት እንዲቀርብለት የማድረግ፣

4.4. የመንግሥት መ/ቤቱ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ስራውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የማስተላለፍ፣

4.5. የመንግሥት መ/ቤቱ ከህግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን የማድረግ፣

4.6. ተገቢ ሆኖ ካላገኘው የተጫራቹን ወይም የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ የማድረግ፣

4.7. አቤቱታው በየደረጃው ላለው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት የቀረበው የመንግሥት መ/ቤቱ ለአቤቱታው ምላሽ ከሰጠ በኋላ 5 የሥራ ቀናት አልፎ ከሆነ ወይም አቤቱታው በመጀመሪያ ለመንግሥት መ/ቤቱ ያልቀረበ ከሆነ አቤቱታውን ውድቅ የማድረግ

5. አቤቱታውን ባቀረበው ተጫራች እና ጨረታውን ባወጣው መ/ቤት በጋራ ስምምነት ካልተደረሰ በስተቀር እንዳግባብነቱ ቅሬታው የቀረበለት በየደረጃው ያለ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መ/ቤት አቤቱታው በቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ የተሰጠውን ምላሽ፣ ማስረጃዎችን፣ ሰነዶችን እና መግለጫዎችን ከመንግሥት ግዥ ህጉ አኳያ በመመርመር ውሣኔውን በፅሁፍ መስጠት አለባቸው።

6. አቤቱታው የቀረበው በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከሆነ አቤቱታ ለቀረበበት ግዥ ፈጻሚ አካል አቤቱታ የቀረበበት መሆኑንና ከግዥው አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ሰነዶችንና መግለጫዎች እንዲልክ እና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ቀጣይ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊልክ ይችላል፣

7. አቤቱታውን የሚያጣራው ቢሮው ከሆነ ቅሬታው የቀረበበት አካል አቤቱታውን ለማጣራት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ጥያቄ በቀረበለት እስከ 3ኛው ቀን ተፈላጊውን መረጃ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እና መምሪያዎች ግዥ ፈጻሚው አካል በወቅቱ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ አቤቱታ በቀረበበት ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ላይ በአካል በመገኘት ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

9. የቀረበውን አቤቱታ በመመርመር የሚሰጥ ውሣኔ ምክንያቱንና እና አቤቱታው በሙሉ ወይም በከፊል ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ ማመላከት አለበት፡፡

10. እንዳግባብነቱ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ዞን ለቀረበለት የይግባኝ አቤቱታ ውሣኔውን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያልሰጠ እንደሆነ አቤቱታውን ያቀረበው ተጫራች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 45 መሠረት በፍ/ቤት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡ ክሱ እንደቀረበ እንዳግባብነቱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ዞን ገ/ኢ/ል መምሪያ አቤቱታውን ለመስማት ያላቸው ሥልጣን ይቋረጣል፡፡

11. በግዢ መመሪያው አንቀጽ 44 መሠረት ክስ ካልተመሠረተ በስተቀር እንዳግባብነቱ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም ዞን መምሪያ የሚሰጡት ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

12. በቢሮውና በመምሪያዎች በተሰጠው ውሳኔ የማይረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል።

## 40. አቤቱታ የሚጣራበት ሥርዓት የሚመራባቸው ደንቦች

ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል ወይም በየደረጃው ያሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ተቋማት በቀረበው አቤቱታ ላይ የሰጧቸው ውሣኔዎች ግልባጮች ውሣኔው በተሰጠ በ5 ቀናት ውስጥ እንዳግባብነቱ አቤቱታውን ላቀረበው ተጫራች እና ወይም ጨረታውን ላወጣው የግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት እንዲደርሱ መደረግ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የተሰጠው ውሣኔ ለሕዝብ ክፍት መደረግ አለበት፡፡ ይሁን እንጅ መገለፁ ከህግ ተቃራኒ፣ የሕግን አፈፃፀም የሚያሰናክል፣ የህዝብን ጥቅም ያልጠበቀ የተሣታፊዎችን የንግድ ጥቅም የሚጐዳ ወይም ውድድርን የሚያደናቅፍ ከሆነ ማናቸውም መረጃ ለሕዝብ ክፍት መሆን የለበትም፡፡

## 41. የግዥ አፈፃፀም ሥርዓትን ስለማገድ

1. አቤቱታው ፍሬ ነገር ያለው ከሆነ እና የያዘው መግለጫ እውነት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ እንዲሁም አቤቱታው ተቀባይነት የሚያገኝ መሆኑ ሲገመት እና የእገዳው ውሣኔ መተላለፍ ጨረታ ያወጣውን መ/ቤት እና የሌሎችን አቅራቢዎች ጥቅም የማይጐዳ ሲሆን ከዚህ በላይ በግዢ መመሪያው በተመለከተው መሠረት በተገቢው ጊዜ ውስጥ አቤቱታ ቀርቦ ጉዳዩ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ጨረታው ታግዶ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡
2. የግዥው ውል ከተፈረመ በኋላ ክብደት የሚሰጠው አቤቱታ የቀረበ ሲሆን እና ይህም አቤቱታ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ጨረታውን

ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል የግዥውን አፈፃፀም ጉዳይ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ታግዶ እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

3. ጨረታውን ያወጣው ግዥ ፈጻሚ አካል በአስቸኳይ መሟላት ያለበትን የመንግሥት ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግዢው አፈፃፀም መቀጠል እንደሚገባ ካረጋገጠ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው እገዳ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት በግዥ ፈጻሚ አካላት የሚተላለፍ ማናቸውም ውሣኔ እንዲሁም ለውሣኔው መሠረት የሆኑት ምክንያቶች እና ሁኔታዎች የግዢውን አፈፃፀም ሥርዓት የሚያሣዩ ሰነዶች አካል ሆነው መመዝገብ አለባቸው።

# ክፍል አስራ ሁለት

# ለቢሮው የሚቀርብ የጥፋተኝነት ሪፖርት የሚታይበት ሥርዓት

## 42. የጥፋተኝነት ሪፖርት  አቀራረብና የማጣራት ሥርዓት አፈፃፀም

ቢሮው በአዋጁ አንቀጽ 56 እና 58 መሠረት ግዥ ፈጻሚ አካላት በተጫራቾች ወይም በአቅራቢዎች ላይ የሚያቀርቡትን የጥፋተኝነት ሪፖርት በሚከተለው ሁኔታ አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል::

1. ማንኛውም ግዥ ፈጻሚ አካል በመንግሥት ግዥ የተሳተፈ ማንኛውም ተጫራች/አቅራቢ የተሳተፈበት ግዥ የሚመራበት ሕግ ከሚያዘው ውጭ መፈፀሙን፣ ውል ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ ማጭበርበሩን፣ የሀሰት ሰነድ ማቅረቡን፣ መመሳጠሩን፣ የሙስና ተግባር መፈፀሙን ወይም የገባውን የውል ግዴታ ባለመፈፀሙ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ማረጋገጥ ከቻለ በጥፋት ፈፃሚው ላይ የጥፋተኛነት ሪፖርት ለቢሮው ሊያቀርብ ይችላል::
2. ግዥ ፈጻሚው አካል በተጫራቹ ወይም አቅራቢው ላይ የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቢሮው ሲያቀርብ የአቤቱታውን ጭብጥ የሚገልጽ መግለጫ፣ ግዥ የተካሄደባቸውን ሰነዶች ቅጂና ሌሎች ጉዳዩን ለማጣራት የሚረዱ ተያያዥ ማስረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል::
3. ቢሮው ሪፖርት ለቀረበበት ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የቀረበበትን የጥፋተኝነት ሪፖርት ፍሬ ሀሳብ በመግለጽ በበኩሉ ያለውን ማስረጃ እና ማብራሪያ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቢሮው እንዲያቀርብ የጽሑፍ ማስታወቂያ መላክና አፈፃፀሙን መከታተል ይኖርበታል::
4. ቢሮው ከግዥ ፈጻሚው አካል እንዲሁም ከተጫራቹ ወይም ከአቅራቢው የቀረቡለትን መግለጫና ማስረጃዎች ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ፣ ከጨረታ ሰነዱና ከግዥ ውሉ አኳያ በማጣራት የጥፋተኝነት ሪፖርቱ በቀረበ በ 5 /በአምስት/ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ሪፖርት ላቀረበው መ/ቤት እና

የጥፋተኝነት ሪፖርት ለቀረበበት አቅራቢ ወይም ተጫራች እንዳስፈላጊነቱም ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት መላክ አለበት፡፡

5. በቢሮው የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 5.1፣ 5.2፣ ወይም 5.3 ላይ ከተመለከቱት መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

5.1. ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የግዥውን ግምገማ ውጤት ሆን ብሎ ለማዛባት ወይም ለማስለወጥ በጨረታው ሂደት ወይም በውል አስተዳደር ወቅት ከዚህ በታች ከ5.2 እስከ 5.7 የተገለጹትን መፈፀሙ ከተረጋገጠ እንደነገሩ ሁኔታ ከ2 /ሁለት ዓመት/ ላላነሰ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት በሚያወጣው የግዥ ጨረታ ላይ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

5.1.1. የሙስና ተግባር ማለትም በግዥ ሙያ ላይ ለተሰማራ ባለሙያ ወይም ኃላፊ ጉቦ ወይም ማባበያ ወይም ማንኛውንም ዋጋ ያለውን ነገር መስጠቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣

5.1.2. የማጭበርበር ማለትም ሀሰተኛ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ሰነድ ማቅረቡ ወይም በቢሮው ታግዶ እያለ የእገዳው ጊዜ ሳይጠናቀቅ በሌላ ጨረታ ላይ ተካፍሎ መገኘቱ ወይም ከውል ውጭ ጥራት የጎደለውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የግንባታ ስራ ወይም የምክር አገልግሎት ዕውነተኛ ወይም ትክክለኛ አስመስሎ ማቅረቡ ሲታወቅ፣

5.1.3. ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ተመሳጥሮ ዋጋ በመወሰን ለሌሎች ተጫራቾችና መ/ቤቱ ከነጻ ውድድር ማግኘት የሚችሉትን ጥቅም ማሳጣቱ ሲረጋገጥ፣

5.1.4. ከመ/ቤት ሰራተኞች ወይም ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር ከውሉ ውጭ የሆነ ዕቃ ወይም አገልግሎት ወይም የምክር አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ማቅረቡ ሲረጋገጥ፣

5.1.5. በግዥ ስራ ላይ የተሰማራን ባለሙያ ወይም ኃላፊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መጉዳቱ ወይም ለመጉዳት ማስፈራራቱ (መዛቱ) ወይም ማስገደዱ ሲረጋገጥ፣

5.1.6. ቀደም ሲል በቢሮው የተጣለበትን ቅጣት ከፈጸመ ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 2 /ሁለት ዓመት/ ውስጥ ሌላ እገዳ የሚያስከትል ጥፋት መፈጸሙ ሲታወቅ፣

5.2. ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ እንደ ጥፋቱ ክብደት እየታየ ከ6/ ስድስት /ወር ላለነሰና ከ2/ሁለት ዓመት/ ለማይበልጥ ጊዜ በማንኛውም የመንግሥት ግዥ ጨረታ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ከአቅራቢነት መዝገብ ይሰረዛል፡፡

5.2.1. በገባው ውል መሠረት አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን ባለማጠናቀቁ ወይም አቅርቦቱን ጀምሮ በማቋረጡ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ የገንዘብ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ወይም የጥቅም ማጣት ካስከተለ፣

5.2.2. በጨረታ ውድድሩ አሸናፊ መሆኑ በጽሁፍ ተገልጾለት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት መ/ቤቱ ግዥውን ከሌላ ተጫራች በመፈጸሙ በመንግሥት መ/ቤቱ ላይ ኪሳራ ወይም የሥራ መጓተት ካስከተለበት፣

5.2.3. ከዚህ ቀደም (ከ3 ዓመት ወዲህ) ሌላ ጥፋት ፈጽሞ በቢሮው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት የነበረ ሆኖ አሁን የቀረበበት ሪፖርት ሌላ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ የግዥ አፈጻጸም ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ፣

5.3. ማንኛውም ተጫራች ወይም አቅራቢ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

5.3.1. ውል ገብቶ አቅርቦቱን ወይም አገልግሎቱን ወይም የምክር አገልግሎቱን ወይም የግንባታ ሥራውን በውሉ በተቀመጠው ጊዜ ሳይሆን ዘግይቶ በማቅረቡ ምክንያት በመ/ቤቱ ሥራ ላይ ችግር በመፍጠሩ፣

5.3.2. ግዥ ለሚፈጽም ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ፕሮፎርማ እንዲሰጥ ተጠይቆ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ፣

6. ቢሮው ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5.1 እና 5.2 መሠረት የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ ለሁሉም በክልሉ ለሚገኙ ግዥ ፈጻሚ አካላት እና ለሚመለከታቸው እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡ በቢሮው ድረ-ገጽ ላይም ውሳኔው እንዲሰፍር ይደረጋል፡፡

7. ቢሮው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ የሚሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት መ/ቤቶች ተጫራቹ ወይም አቅራቢው በፈጠረው ችግር ምክንያት የደረሰባቸውን ኪሣራ በግዥ ውላቸው እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## 43. ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች

1. ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ደርሷል የሚባለው አቅራቢው ድንገት ደራሽ በሆነ ሁኔታ የውል ግዴታውን እንዳይፈፅም ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ባጋጠመው ጊዜ ነው።
2. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ነው ሊያሰኙ የሚችሉ ምክንያቶች ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፣
   - 2.1 ውል እንዳይፈጸም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፣
   - 2.2 እንደ መሬት መናወጥ፣መብረቅ፣ማዕበል እና የመሳሰሉት የተፈጥሮ መቅሰፍቶች
   - 2.3 የጠላት፣ የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ጦርነት፣
   - 2.4 ውል የገባው ወገን መሞት ወይም ባልታሰበ ሁኔታ የሚደርስበት ከባድ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም፣
   - 2.5 በፍትሐብሔር ሕግ የተዘረዘሩ ሌሎች ከአቅም በላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ።
3. ግልፅ የሆነ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ተደርገው ሊቆጠሩ አይችሉም፣
   - 3.1. በተዋዋይ ፋብሪካ ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት በአንደኛው ቅርንጫፍ መ/ቤት ውስጥ የተደረገ የሰራተኛ አድማ ወይም የመ/ቤቱ መዘጋት፣
   - 3.2. ለውሉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች ዋጋ መወደድ ወይም መርከስ፣
   - 3.3. ተዋዋዩ ያለበትን የውል ግዴታ አፈፃፀም ወጭ የሚያከብድበት የአዲስ ህግ መውጣት፣

## 44. አቤቱታን በፍርድ ቤት ስለማየት

ጨረታውን ባወጣው መ/ቤት ወይም በየደረጃው ላለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች እና ከተማ አስተዳደሮች ውሣኔ ቅር የተሰኘ ተጫራች ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

# ክፍል አስራ ሦስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 45. የተሻሩ መመሪያዎች

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የግዢ መመሪያ መስከረም 2001 ዓ/ም ከነማሻሻዎቹ እና የከተማ አስተዳደር የግዥ መመሪያ ቁጥር 4/1998 ከነማሻሻያዎቹ ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

## 46. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሊሻሻል ይችላል ፡፡

## 47. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

1. ይህ መመሪያ ከመስከረም 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ መመሪያዉ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኂላ ያለ መብት ወይም ግዴታ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በክልሉ ገንዘብ ቢር ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ባሕር ዳር

# አባሪዎች

# ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ

| ተ. ቁ | የሚገዛው ዕቃ፣ አገልግሎት ወይም የግንባታ ሥራ ዓይነት | ግዥው የሚፈፀምበት የገንዘብ ምንጭ | | | | የግዥው ምድብ* | ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት** | | የተመረጠው የግዥ ዘዴ*** | የግዥው ዓይነት**** | ግዥውን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከመንግሥት ግምጃ ቤት | ከውስጥ ገቢ | ከብድር | ከዕርዳታ | | መደበኛ በጀት | ካፒታል በጀት | | | ጨረታ የሚወጣበት/ ጥሪ የሚካሄድበት ጊዜ | ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ | |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

* ዕቃ፣ የምክር አገልግሎት፣ አገልግሎት እና የግንባታ ሥራ ተብሎ ይገለፅ፣

** የገንዘቡ ዓይነት በኢትዮጵያ ብር ወይም በሌላ አገር ገንዘብ መሆኑ ይገለፅ፣

*** እንደ ሁኔታው ግልፅ ጨረታ፣ የሁለት ደረጃ ጨረታ፣ የመወዳደሪያ ሃሳብ በመጠየቅ የሚፈፀም ግዥ፣ ውስን ጨረታ፣ በዋጋ ማቅረቢያ የሚካሄድ ግዥ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈፀም ግዥ ተብሎ ይገለፅ፣

**** ብሔራዊ /አገር ውስጥ/ ወይም ዓለም አቀፍ ግዥ ተብሎ ይገለፅ።

## ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልዩ አስተያየት የሚደረግባቸው የሥራ ዓይነቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የሥራዎች ዝርዝር | ተ.ቁ | የሥራዎች ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| 1 | በምግብ ዝግጅት<br>➢ ማር አጣርቶአሽጎ መሸጥ<br>➢ ደረቅ እንጀራ ጋግሮ መሸጥ<br>➢ ወተትና የወተት ተዋጽኦ<br>➢ የባልትና ዉጤቶች<br>➢ ዳቦ፣ድፎ ዳቦ፣አመባሻ መጋገር መሸጥ | 5 | ጨርቃ ጨርቅ አልባሳት<br>✓ ሽመና<br>✓ ልብስ ስፌት<br>✓ ሹራብ ስራ<br>✓ ፈትል ስራ<br>✓ ህትመትና አስሮ ማቅለም (የጨርቅ የከር) |
| 2 | ዕደ ጥበብ<br>➢ ሸክላ ስራ<br>➢ ጥልፍ<br>➢ ስጋጃ ስራ<br>➢ ቆዳና ቆዳ ዉጤቶች<br>➢ አለላ ስፌት<br>➢ ቅርፃ ቅርፅ<br>➢ ዲዛይን ስራ<br>➢ ጭራና ገመድ ስራ<br>➢ ሳረ ሰራዎች<br>➢ የፕላስቲክ ዉጤቶች ስራ<br>➢ ሰንደል ሰራ<br>➢ ሻማ ስራ<br>➢ ላፒዳሪ | 6 | ✓ የከተማ ግበርና<br>✓ የሀር ምርት<br>✓ የበግ ማድለብ<br>✓ የወተት ከብትእርባታ<br>✓ አነስተኛ የጎሮ ተክል<br>✓ የንብ እርባታ<br>✓ የዶሮ እርባታ<br>✓ በሬ ማድለብ |
| 3 | ማዘጋጃ ቤታዊ አገለግሎት<br>➢ የቀልዝ ስራ<br>➢ ደረቅ ቆሻሻ | 7 | ኮንስትራክሽን ዘርፍ<br>✓ የግንባታ ሥራ<br>✓ ሣኒቴሪ ሥራ<br>✓ ኤሌክትሪክ ሥራ<br>✓ ብሎኬት ሥራ<br>✓ የጠጠር ምርት ሥራ<br>✓ ፕሪካስት ቢም<br>✓ ቀለም ቅብ |
| 4 | እንጨትና ብረታ ብረት<br>✓ እንጨት ሥራ<br>✓ ብረታ ብረት ሥራ<br>✓ ቀርቀሃ ሥራ<br>✓ ሰፋ ሥራ | 8 | የኮምፒዩተር ጥገና ሥራ |
| | | 9 | ኢንፎርሜሽን ኮሙኒካሽን ቴክኖሎጂ /IT/ |

# በቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ለመንገድ ሥራና ለህንፃ ግንባታ የሚገዙ ማሽነሪዎች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ለመንገድ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች | ለሕንጻ ሥራ ተቋራጭ የተፈቀዱ ማሽነሪዎች |
|---|---|---|
| 1 | ቡል ዶዘር | አክስካቫተር |
| 2 | ፍሮንት ኢንድ ሎደር | ሃይድሮሊክ ብሬከር |
| 3 | ሞቶር ግሬደር | ክሬን |
| 4 | ትሬንች አክስካቫተር | ታወር ክሬን |
| 5 | ባክሆይ | ዶዘር |
| 6 | ግሪድ ሮለር | ትራክ ሚክሰር |
| 7 | ቫይብራቶሪ ሮለር | ሎደር |
| 8 | ወተር በውሰር | ዳምፕ ትራክ |
| 9 | ዳምፕ ትራክስ | ስካፎልዲንግ |
| 10 | ትራክ ዊዝ ትሬለር | ሮርምወርክ |
| 11 | ሎቤድ ሀኡሊንግ ትራክ | ፍሮንት ኤንድ ዳምፐር |
| 12 | ቢቱመን ዲስትሪቢውተር | ኮምፓክተር/ሮለር |
| 13 | ስቴሽነሪ ሂተር | ባክሆ |
| 14 | ፔቨር ፎር ቤዝ ኮርስ | ክሬሸር |
| 15 | አስፓልት ፔቨር | ጀኔሬተር |
| 16 | ስልፍ ፕሮፒልድ ቺፕ ስፕረደር | ትራክ ዊዝ ትሬለር |
| 17 | ሚካኒካል ብሩም | |
| 18 | ታንደም ሮለር | |
| 19 | ቫይብሬቲንግ ሮለር | |
| 20 | ፖድ ፉት ሮለር | |
| 21 | ፕኒውማቲክ ታየር ሮለር | |
| 22 | አስፓልት ፕላንት | |
| 23 | ክራሺንግ እና ስክሪኒንግ ፕላንት | |
| 24 | ዋጎን ድሪል | |
| 25 | ኮምፕሬስር | |
| 26 | ክሬን | |
| 27 | ኮንክሪት ሚክሰር | |
| 28 | ጀነሬተር | |
| 29 | የኮንሰልታንቶች መቆጣጠሪያ ተሽከርካሪ | |

